ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲና
ፌደራል ምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ቢሮ

# የሴፍቲኔት ጥናት
# የመረጃ አሰባሰብ መመሪያ

ግንቦት 2000

## ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲና

## ፌደራል ምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ቢሮ

# የሴፍቲኔት ጥናት

# የመረጃ አሰባሰብ መመሪያ

**ግንቦት 2000**

## ማውጫ

1. መግቢያ ........ 3

2. ጽንሰ ሃሳቦችና ፍችዎቻቸው ........ 4

3. በጥናቱ ስለሚሸፈኑ ቤተሰቦች አጭር መመሪያ ........ 10

4. የቅጽ ምዋ 2000/2 አሞላል ........ 14

5. የቅጽ ምዋ 2000/3 አሞላል ........ 22

6. የቅጽ ምዋ 2000/4 አሞላል ........ 41

7. የቅጽ ምዋ 2000/5 አሞላል ........ 45

8. የቅጽ ምዋ 2000/6 አሞላል ........ 63

9. የቅጽ ምዋ 2000/7 አሞላል ........ 76

10. የቅጽ ምዋ 2000/8 አሞላል ........ 98

11. የቅጽ ምዋ 2000/9 አሞላል ........ 132

12. ዕዝል 1 የቁመትና የክብደት ልክቶሽ(Antropometrics) ........137

13. ዕዝል 2 ዋና ዋና ታሪካዊ ድርጊቶች ዝርዝር ........ 149

14. ዕዝል 3 የቋንቋ ዝርዝርና ኮድ ........ 152

<u>የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲና የምግብ ዋስትና</u>

<u>ማስተባበሪያ ቢሮ የምግብ ዋስትና ጥናት(Panel Survey)</u>

<u>የመረጃ ሰብሳቢዎች መመሪያ</u>

<u>መግቢያ</u>

በኢትዮጵያ በተለያዩ አካባቢዎች የሴፍትኔትና ሌሎች የምግብ ዋስትና ፕሮግራሞች በመከናወን ላይ ይገኛሉ። እነዚህ ፕሮግራሞች በህብረተሰቡ ውስጥ ምን ያህል እንደሚታወቁና ምን ጥቅም እንደሰጡ ወይም ምን ያህል ውጤታማ እንደሆኑ ለማወቅ እንዲሁም ለወደፊቱ የሕዝቡን ምግብ ዋስትና ለማሻሻል ምን መደረግ እንዳለበት የሚጠቁም መረጃ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲና በምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ቢሮ ትብብር ይህ የምግብ ዋስትና ጥናት በአራቱ ክልሎች በናሙና በተመረጡ የቆጠራ ቦታዎች (በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ትግራይ) ለሁለተኛ ጊዜ ይካሄዳል።

ይህንንም ጥናት ለማድረግ የሚያስችሉ መጠይቆች የተዘጋጁ ሲሆን ለእነዚህ መጠይቆችም የአሞላል መመሪያ ተዘጋጅቷል። በመሆኑም በዚህ መመሪያ የተሰጡትን ማብራሪያዎች በአግባቡ መከተል አስፈላጊ ይሆናል።

<u>መጠይቆች</u>

በመግቢያው ለተጠቀሰው ጥናት በአጠቃላይ ስባት መጠይቆች ተዘጋጅቷል። እነዚህም :-

1. ቅፅ ምዋ2000/2 - ለጥናቱ በተመረጡ ቤተሰቦች ውስጥ የሚገኙ የቤተሰብ አባላትንና ዲሞግራፊያዊ ባህሪያትን መመዝገቢያ
2. ቅፅ ምዋ2000/3 - የመሬት አጠቃቀም ሰብል ምርትና ሽያጭ መመዝገቢያ
3. ቅፅ ምዋ2000/4 - የእርሻ መሣሪያዎች ፣ የቤት ውስጥ ቁሳቁስና የቤት እንስሳት መመዝገቢያ
4. ቅፅ ምዋ2000/5 - ከግብርና ውጪ የሚገኝ ገቢንና ብድርን መመዝገቢያ
5. ቅፅ ምዋ2000/6 - ሴፍቲኔትንና ሌሎች የምግብ ዋስትና ፕሮግራሞችን ሁኔታ መመዝገቢያ
6. ቅፅ ምዋ2000/7 - የቤተሰብ ፍጆታና ወጪ መመዝገቢያ
7. ቅፅ ምዋ2000/8 - የጤና፣የበሽታና የችግርን ሁኔታ መመዝገቢያ
8. ቅፅ ምዋ2000/9 - የህፃናት ቁመትና ክብደት ልክቶሽ መመዝገቢያ ናቸው።

## ጽንስ ሃሳቦችና ፍችዎቻቸው

መረጃዎች ደረጃቸውና ጥራታቸው ተጠብቆ እንዲሰበሰቡ ለማድረግ አንድ ዓይነት ጽንስ ሐሳብና ፍች መጠቀም ያስፈልጋል። ለምግብ ዋስትና ጥናት የምንጠቀምባቸው ዋና ዋና ጽንስ ሃሳቦችና ፍችዎቻቸው ከዚህ በታች ቀርበዋል። መረጃ ሰብሳቢዎችም ሆኑ ሌሎች በጥናቱ የሚሰማሩ ሁሉ መመሪያውን በዝርዝር መገንዘብና መረጃዎቹ በመመሪያው መሠረት መሰብሰባቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል።

### 1. ቤተሰብ

ቤተሰብ ማለት በአንድ ቤት ወይም በተቀራረቡ ቤቶች ውስጥ አብረው የሚኖሩትንና ምግባቸውን በአንድ ላይ አብስለው በአንድነት የሚመገቡትን ሰዎች ያጠቃልላል። የቤተሰብ አባላት በሥጋ ወይም በጋብቻ የሚዛመዱትንና የማይዛመዱትን ሊያጠቃልል ይችላል። በሥጋ ወይም በጋብቻ የሚዛመዱት ባል፣ሚስት፣ልጆች፣የባል ወይም የሚስት አባት፣እናት ፣እህት፣ ወንድም … ወዘተ ናቸው። በሥጋ ወይም በጋብቻ የማይዛመዱ ሌሎች የቤተሰብ አባላት ለምሳሌ በቤት ሠራተኝነት ፣በዘበኝነት የሚያገለግሉ ግለሰቦች ከቤተሰቡ ጋር አብረው የሚኖሩና የሚመገቡ ከሆነ እንደቤተሰብ አባል ይቆጠራሉ።

የቤተሰብ አባላት ብዛት ሊለያይ ይችላል። ይኸውም አንድ ሰው ብቻውን እንደአንድ ቤተሰብ ሊቆጠር ይችላል ወይም ሌሎች ሰዎች እንደዘበኞች ፣ጥገኞች፣… ወዘተ ከላይ ከተጠቀሱት ጋር የሚኖሩና በአንድነት የሚመገቡ ከሆነ እንደ አንድ ቤተሰብ ይቆጠራሉ። ነገር ግን ከጥናቱ በፊት ቤተሰቡን ትቶ በእንግድነትወደ ሌላ ቤተሰብ ሔዶ ለስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ ከተቀመጠ አሁን ለሚገኝበት ቤተሰብ እንግዳ መሆኑ ቀርቶ የቤተሰብ አባል ይሆናል ማለት ነው።
ጋብቻው በአንድ ሚስት ብቻ የተመሠረተ ከሆነ ቤሰተሰብ ባልን፣ ሚስትን ፣ልጆችን ፣ የጉዲፈቻ ልጆችን፣ ሌሎች ዘመዶችንና ዘመድ ያልሆኑትን (የቤት ሠራተኞችን …ወዘተ) ሊያጠቃልል ይችላል። ነገር ግን ጋብቻው ከብዙ ሚስቶች ጋር የተመሠረተ ከሆነ ( ከአንድ በላይ ሚስቶች ካሉት) የሰውዬው ሚስቶች ከነልጆቻቸውና ዘመዶቻቸው… ወዘተ በአንድ ቤት ወይም በተቀራረቡ ቤቶች የማይኖሩና ምግባቸውንም በአንድነት አብስለው የማይበሉ ከሆነ ባልየው አሁን በሕይወት ካሉት ውስጥ በቅድሚያ ካገባት ሚስቱ ጋር እንደ አንድ ቤተሰብ ተቆጥሮ ሌሎች የሰውዬው ሚስቶች የየራሳቸው ቤተሰብ እንዳላቸው ሆነው ይወሰዳሉ።

### 2. መደበኛ የቤተሰብ አባል

አንድ ሰው መደበኛ የቤተሰብ አባል ነው የሚባለው ቢያንስ ስድስት ወር ሙሉ ያለማቋረጥ ከቤተሰቡ ጋር የኖረ እንደሆነ ነው። ከቤተሰቡ ጋር ለዘለቄታው ለመኖር የመጡ ሁሉ ከቤተሰቡ ጋር መኖር ከጀመሩ ስድስት ወር ባይሞላቸውም እንደቤተሰቡ

መደበኛ አባል ይቆጠራሉ:: ከስድስት ወር በታች ከቤተሰቡ ለጊዜው ተለይተው የቆዩ የቤተሰብ አባላት የዚሁ ቤተሰብ አባል ሆነው መቆጠር አለባቸው :: ነገር ግን ከቤተሰቡ ተለይተው ከሄዱ ስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ የሆናቸው ወይም ከስድስት ወር በላይ ለመቆየት አቅደው የሄዱ ከቤተሰቡ ከወጡ ስድስት ወር ባይሞላቸውም እንደቤተሰቡ መደበኛ አባል አይቆጠሩም::

<u>የሚከተሉት የቤተሰብ አባላት እንደመደበኛ የቤተሰብ አባል መቆጠር ይኖርባቸዋል::</u>

ሀ. ጥናቱ በሚካሄድበት ጊዜ ከቤተሰቡ ጋር ቢያንስ ለስድስት ወር የኖሩ ሁሉ፣

ለ. ከቤተሰቡ ጋር መኖር ከጀመሩ ስድስት ወር ባይሞላቸውም ከቤተሰቡ ጋር ለስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ ለመቆየት ዕቅድ ያላቸው ሁሉ ለምሳሌ ባል አግብታ ከወላጆቿ ቤት ወደ ባሏ የሄደች ስድስት ወር ባይሞላትም የባሏ ቤተሰብ መደበኛ አባል ትሆናለች ማለት ነው:: እንዲሁም ሥራ አግኝቶ ለዘለቄታው ለመኖር ወደ ሌላ ቤተሰብ የሄደ ስድስት ወር ባይሞላውም በጥናቱ ጊዜ የተገኘበት ቤተሰብ አባል ይሆናል፣

ሐ. የቤት ሠራተኞች አብዛኛውን ጊዜ ከቤተሰቡ ጋር የሚያድሩና ሌላ መኖሪያ የሌላቸው ሁሉ፣

መ. ጥናቱ በሚካሄድበት ጊዜ ከስድስት ወር ሳነስ ከቤተሰቡ ለጊዜው የተለዩ ለምሳሌ በዕረፍት ላይ ያሉ ፣ ለዓመት በዓል ወደ ሌላ ቦታ የሄዱ፣ ታመው ሆስፒታል የገቡ ፣ ዘመድ ለመጠየቅና ከሥራቸው ጋር በተያያዘ ጉዳይ ወደ ሌላ ቦታ ለጊዜው የሄዱትን አባላት ሁሉ ያጠቃልላል፣

ሠ. ሌላ መኖሪያ ሥፍራ የሌላቸውና ጥናቱ በሚካሄድበት ወቅት ከቤተሰቡ ጋር የሚኖሩ አባላት ሁሉ ለምሳሌ የተለያዩ ቤቶችን እያቀያየሩ የሚኖሩና መደበኛ መኖሪያ የሌላቸው ግለሰቦች በጥናቱ ወቅት በሚገኙበት ቤተሰብ እንደመደበኛ አባል ተቆጥረው ይመዘገባሉ፣

ረ. ተማሪዎች ከቤተሰቦቻቸው፣ ከወላጆቻቸውና ከመደበኛ መኖሪያቸው ተለይተው በመደበኛ ትምህርት ቤቶች፣በኮሌጆች፣ በዩኒቨርሲቲዎች፣ ... ወዘተ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙ በሙሉ ትምህርታቸውን በሚከታተሉበት አካባቢ (ከተማ) መደበኛ ነዋሪዎች ሆነው መቆጠር አለባቸው:: በአዳሪ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች እንዲሁም ከወላጆቻቸው ተለይተው ቤት ተከራይተው ወይም ከዘመድ ተጠግተው እየኖሩ የሚማሩ ተማሪዎች ምንም እኳን በየሣምንቱ ወይም በየአሥራ አምስት ቀኑ ስንቅ ለማምጣት ወይም ወላጆቻቸውን ለመጠየቅ ወደ ቤተሰቦቻቸው ቢሄዱም በሚኖሩበት አካባቢ መደበኛ የቤተሰብ አባል ሆነው መቆጠር

አለባቸው ። ነገር ግን ከመደበኛ መኖሪያቸው በየቀኑ ወደ ትምህርት ቤት እየተመላለሱ የሚማሩ ተማሪዎች ሁሉ የሚኖሩበት ቤተሰብ መደበኛ አባል ሆነው መቆጠር አለባቸው።

3. <u>የቤተሰብ ኃላፊ</u>

የቤተሰብ ኃላፊ ማለት የአንድ ቤተሰብ መደበኛ አባል የሆነ/ች በቤተሰቡ አባላት እንደ ኃላፊ የሚቆጠር / የምትቆጠር ማለት ነው። ከአንድ በላይ ሚስቶች ያሉት ሰው ሚስቶቹ በተለያየ ቤተሰብ የሚኖሩ ከሆነ እሱ የቤተሰብ ኃላፊ ሆኖ የሚመዘገበው አሁን በሕይወት ካሉት ውስጥ <u>በቅድሚያ ካገባት (አንጋፋ) ሚስቱ</u> ጋር ይሆናል። ለሌሎቹ ሚስቶች ግን የቤተሰብ ኃላፊ ማን እንደሆነ ተጠይቆ ይመዘገባል። ይህም የሚሆነው ባልየው በሚያሸማ መልኩ ከሁሉም ሚስቶቹ ጋር የሚኖር ከሆነ ነው።

4. <u>ፓርስል</u>

ፓርስል ማለት የአንድ ይዞታ አካል ሆኖ <u>ከይዞታው ውጭ በሆኑ እንደ መሬት ፣ውሀ፣መንገድ፣ደንና በመሳሰሉት ሙሉ በሙሉ የተከበበ መሬት ነው።</u> አንድ ፓርስል <u>አንድ ማሣ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ማሣዎች /መሬት አጠቃቀም ሊይዝ</u> ይችላል። በተጨማሪም በአንድ ፓርስል የተለያዩ ሰብሎች ሊዘሩ ይችላሉ።

5. <u>ማሣ</u>

ማሣ ማለት <u>በአንድ የሰብል ዓይነት ወይም በድብልቅ ሰብሎች የተያዘ አንድ ሙሉ ፓርስል ወይም የአንድ ፓርስል ክፋይ ወይም አካል ነው።</u>

6. <u>ሌላ የመሬት አጠቃቀም</u>

በሰብል ከተያዙ ማሣዎች ውጭ ያሉት የመሬት አጠቃቀሞች (ለምሳሌ፡- እዳሪ፣ በደን ፣በግጦሽ...ወዘተ የተያዘ) በጥቅል የሚጠሩበት ነው።

7. <u>የመኸር ሰብል</u>

ለዚህ ጥናት የመኸር ሰብል ማለት ከመስከረም <u>1 እስከ የካቲት 30 የሚሰበሰብ ማንኛውም ጊዜያዊ ሰብል ነው።</u> የሰብሉ የዘር ወቅት ግን ከተጠቀሰው ጊዜ ውጭ ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል።

**8. <u>የበልግ ሰብል</u>**

ለዚህ ጥናት የበልግ ሰብል ማለት ከላይ ከተጠቀሰው የመኸር ጊዜ ውጪ ( ከመጋቢት 1 - ጳጉሜ 5) የሚሰበሰብ ማንኛውም ጊዜያዊ ሰብል ነው።

<u>ማስታወሻ</u>

የመኸርና የበልግ ሰብሎች ከላይ በተጠቀሱት ጊዜያት ውስጥ በዝናብ፣በውሃ ሸሸ፣በመስኖ... ወዘተ የሚመረቱ ሰብሎችን እንደሚያጠቃልሉ መገንዘብ ያስፈልጋል። ይሁንና ቋሚ ሰብሎች የመኸርና በልግ ተብለው እንደማይከፋፈሉ ማስታወስ ይገባል።

**9. <u>የዘር ዓይነት</u>**

የዘር ዓይነቶች በሁለት ይከፈላሉ። እነርሱም በአካባቢ ከሚመረተው ሰብል ገበሬዎች ለዘር የሚጠቀሙበትና ከፍ ያለ ምርት የሚያስገኝ ጥራት ያለው የተሻሻለ / ምርጥ / ዘር ናቸው።

በኢትዮጵያ አብዛኛውን ጊዜ የተሻሻለ ወይንም /ምርጥ ዘር/ የሚቀርበው <u>በኢትዮጵያ ምርጥ ዘር ድርጅት በኩል ነው።</u> በተጨማሪም መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ለምሣሌ <u>ከግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ፣ከዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ምርጥ ዘር ሊገኝ ይችላል።</u>
<u>ምርጥ ዘር የምንለው ለአንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ ለማዋል በቀጥታ ከላይ ከተጠቀሱት ምንጮች የተገኘውን ብቻ ነው።</u>

**10. <u>ፀረ -ተባይ</u>**

ፀረ ተባይ ማለት ሰብልን በመብላት ምርት እንዲቀንስ ወይም እንዲጠፋ የሚያደርጉ ተባዮችን ለማጥፋት የሚጠቅም ማንኛውም ዓይነት የኢንዱስትሪ ውጤት የሆነ መድኃኒት ነው። ለምሳሌ ፀረ-ተምች፣ፀረ-አንበጣ...ወዘተ።

**11. <u>መስኖ</u>**

መስኖ ማለት ምርትን ለማምረት ወይም ለመጨመር ሆን ተብሎ በሰው ሠራሽ ዘዴ ማለትም በቦይ፣በቦቴ፣ውኃ በማጋዝ ፣በኩሬ፣ ውሃ በማቆርና በመሳሰሉት በመጠቀም ማሣው በቂ ውሃ እንዲያገኝ ማድረግ ነው። ሆኖም በዝናብና በጎርፍ መጥለቅለቅ የሚገኘው ውኃ እንደመስኖ ውሃ አይቆጠርም።

**12. <u>ዕድሜ</u>**

አንድ ሰው ከተወለደበት ጊዜ ጀምሮ ጥናቱ እስከሚካሄድበት ቀን ድረስ ያለው የዓመት ብዛት ነው።

የቤተሰብ አባላትን ዕድሜ በትክክል ለማወቅ ከሚያስችሉ ዘዴዎች አንዱ ከቤተሰቡ አባላት መካከል የአንዱን ዕድሜ በትክክል በማወቅ የሌሎችን ዕድሜ ለመገመት ማስቻሉ ነው:: በተለይ የሥጋ ዝምድና ያላቸው አባላት በስንት ዓመት እንደሚበላለጡ ስለሚታወቅ የአንዱን ዕድሜ ማወቅ የሌላውን ዕድሜ ለማስላት ያስችላል :: በተጨማሪም አንዳንድ ሴቶች ዕድሜያቸውን በትክክል ባያውቁም ካገቡ በኋላ ለስንት ዓመት በትዳር ላይ እንደቆዩ ስለሚያውቁ ሲያገቡ የስንት ዓመት ዕድሜ እንደነበራቸው በመጠየቅ አሁን ያላቸውን ዕድሜ ማወቅ ይቻላል :: በትዳር ላይ ስንት ዓመት እንደቆዩ የሚገልጸው መረጃም የልጆቻቸውን ዕድሜ ለማወቅ ያስችላል:: በተጨማሪም አንዳንድ የቤተሰብ አባላት ዕድሜያቸውን ከአንዳንድ ካለፉና ከሚታወሱ ድርጊቶች ጋር በማነጻጸር መናገር ይችሉ ይሆናል:: እነዚህ ድርጊቶች ከተፈጸሙ ስንት ዓመት እንዳለፈ ማወቅ የአባላቱን ዕድሜ ለማወቅ ይረዳል:: በዚህ መመሪያ መጨረሻ ዕድሜን በስሌት ለማወቅ እንዲረዳ አንዳንድ ታሪካዊ ድርጊቶች የተፈጸሙበትን ጊዜ የሚገልጽ መረጃ ተዘርዝሯል:: ብዙ ግለሰቦች ዕድሜያቸውን በዜሮ ወይም በአምስት በሚያልቁ አሀዞች መናገር ስለሚቀላቸው ትክክለኛውን ዕድሜ ለማወቅ ተገቢውን ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል::

**13. <u>ኩንታል</u>**

ኩንታል ማለት መቶ ኪሎ ግራም የሚመዝን ክብደት ማለት ነው::

**14. <u>ሄክታር</u>**

ሄክታር ማለት 10000 (አሥር ሺህ ) ሜትር ካሬ ስፋት ያለው መሬት ነው::

**15. <u>የግጦሽ መሬት</u>**

የግል ይዞታ አካል ሆኖ ጥናቱ በሚካሄድበት ወቅት ግለሰቡ ለግጦሽ የሚገለገልበት መሬት ማለት ነው::

**16 <u>አዳሪ መሬት</u>**

አዳሪ መሬት ሰብል ሲመረትበት ቆይቶ መሬትን ለማዳበር ሆንተ ብሎ ቢያንስ ለአንድ የሰብል ወቅት ሳይታረስ የሚቆይ መሬት ነው::

**17. <u>በኮንትራት ወይም በኪራይ የተያዘ መሬት</u>**

የሌላ ሰው የሆነና ባለይዞታው ኪራይ (በገንዘብ ወይም በዓይነት) እየከፈለ የሚጠቀምበት መሬት ማለት ነው::

**18. በግል የተያዘ መሬት**

ባለይዞታው ለመንግስት ግብር እየከፈለ የግብርና ሥራ የሚያከናውንበት የግሉ (የራሱ) የሆነ መሬት ማለት ነው። ግብር መክፈል ግዴታ ቢሆንም በተለያየ ምክንያት ግብር ባይከፍሉም እንኳ ይዞታ እስካላቸው ድረስ በጥናቱ ይሸፈናሉ።

**19. ዓምድ**

ዓምድ ማለት በቅጹ ወይም በመጠይቁ ለሚሰበሰቡት መረጃዎች አርዕስት የአርዕስቱ ማብራሪያና በአርዕስቱ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች መልሶች መጻፊያ የተሰጠ ክፍት ቦታ ነው። በዓምዶቹ መረጃዎች በፊደል ወይም በአኃዝ ብቻ ወይም በሁለቱም እንደ አስፈላጊነቱ ሊሰፍሩ ይችላሉ። በቁጥር የሚገለጹ መረጃዎች በዓምዱ ውስጥ ከቀኝ በመጀመር ወደ ግራ ይሞላሉ። ይህ አሠራር በሙሉ ቁጥርና በዴሲማል ለሚገለጹ መረጃዎች በሙሉ ያገለግላል። የሚከተለውን ምሣሌ ይመልከቱ። 198 ኪሎ ከ760 ግራም 6 ኪሎ ከ75 ግራምና 20 ኪሎ ከ5 ግራም በሚከተለው ሁኔታ በተገለጸው የቁጥሮች አጻጻፍ ይሰፍራሉ።

←

| ኪ.ግ | ግራም |
|---|---|
| 198 | 760 |
| 6 | 075 |
| 20 | 005 |

**20. ኬሚካል ማዳበሪያ**

በኢንዱስትሪ ወይም በፋብሪካ የተመረተና የሰብል ምርትን ለማሻሻል የሚረዳ የማዳበሪያ ዓይነት ነው።

# በጥናቱ ስለሚሸፈኑ ቤተሰቦች አጭር መመሪያ

ቀደም ሲል በዚህ ጥናት በናሙና በተመረጡ የቆጠራ ቦታዎች ውስጥ የቤተሰቦች ምዝገባ የተካሄደ ሲሆን ከዚያም በኋላ 25 ቤተሰቦች (አስራ ሰባት ቤተሰቦች በሴፍቲ ኔት ከታቀፉት እና ስምንት ደግሞ ከታቀፉት ውጭ ከሆኑት ቤተሰቦች ውስጥ) በናሙና ተመርጠዋል:: እነዚህ ቤተሰቦች ቀደም ሲል የጥናቱ የመጀመሪያ ዙር ሲካሄድ መረጃ የተሰበሰበላቸው ሲሆን አሁን ደግሞ ለውጡን ለማየት የቀድሞውን ቅጽ ምዋጥ/1 በመጠቀም በናሙና የተመረጡትን ቤተሰቦች በመለየት ለሁለተኛ ጊዜ መረጃ ይሰበሰብላቸዋል:: የናሙና ቤተሰቦችን (በምዝገባ አንድ በ አንድ) ከመለየቱ በፊት ግን ስለ ቆጠራ ቦታው ድንበር የቆጠራ ቦታ ካርታን በመጠቀም አካባቢውን ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል ምክንቱም የናሙናዎቹ ቤተሰቦች በስመ ሞክሼ ከቆጠራ ቦታው ውጭ ሌሎች ቀደም ሲል በጥናቱ ያልተሸፈኑ ቤተሰቦች በዚህ ጥናት እንዳይካተቱ መጠንቀቅ ያስፈልጋል:: ስለዚህ መረጃ ሰብሳቢዎችም ወደ መስክ ከመሰማራታቸው በፊት በጥናቱ የሚሸፈኑትን ቤተሰቦች ዝርዝር እና ጥናቱ የሚካሄድባቸውን የቆጠራ ቦታ ካርታዎች መያዝ ይገባቸዋል::

ማስታወሻ

እነዚህ ቀደም ሲል ጥናቱ የተካሄደባቸውን ቤተሰቦች በትክክል ለመለየት እንዲያስችል የናሙና ቤተሰቦቹ የሚገኙበት የቀድሞው የቆጠራ ቦታ ካርታ እና የናሙና ቤተሰቦች ዝርዝር በጥንቃቄ መጠቀም ያስፈልጋል::ስለዚህ በዚህ ጥናት ምንም ዓይነት የቤተሰብ ምዝገባ ስለማይካሄድ የቆጠራ ቦታ ካርታውን ግን አካባቢውንና ነዋሪዎቹን ጠንቅቆ ከሚያውቅ ሰው ጋር በመሆን በትክክል መለየት ያስፈልጋል::

## የቆጠራ ቦታ ካርታ አጠቃቀም

ለጥናቱ በተመረጠዉ ቆጠራ ቦታ የሚመደብ መረጃ ሰብሳቢ ጥናቱ ከመጀመሩ በፊት በተቆጣጣሪው አማካኝነት የተመደበበት የቆጠራ ቦታ ካርታ እና ስለ ቆጠራ ቦታው የሚገልጽ የቆጠራ ቦታ መግለጫ ጽሁፍ ይደርሰዋል:: በተጨማሪም ከዚህ በታች በተዘረዘሩት መግለጫዎች መሠረት ስለቆጠራ ቦታዉ ካርታ ዝርዝር ማወቅ ይገባዋል::

1. መረጃ ሰብሳቢው የተመደበበትን የቆጠራ ቦታ በሚገባ ለማወቅ ይችል ዘንድ በመጀመሪያ የተሰጠውን የቆጠራ ቦታ ካርታ ማጥናት ይኖርበታል:: ለዚህም የተመደበበት የቆጠራ ቦታ ካርታ ይዘት ምን እንደሆነ በሚቀጥሉት ገጾች ውስጥ የተዘረዘሩትን ማጥናት አለበት::

2. መረጃ ሰብሳቢው ከካርታው ጋር የተያያዘውን የካርታ መግለጫ ጽሁፍ በሰሜን፣በምሥራቅ፣በደቡብ እና በምዕራብ አቅጣጫዎች የቆጠራ ቦታውን የወሰን መግለጫ ደጋግሞ በማንበብ በካርታው የሚታዩትን ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ነገሮች መሬት ላይ ካሉት ጋር ማገናዘብ ይኖርበታል።
3. በቆጠራ ቦታ ካርታ ላይ ከሚገኙ ዓብይ ነጥቦች ውስጥ አንዱ የቆጠራ ቦታው ድንበር ነው። የድንበሩ ዓላማ መረጃ ሰብሳቢው ከተወሰነለት ክልል እንዳይወጣ እና በክልሉ ውስጥ ያሉትን ቤተሰቦችና ቤቶች ለመመዝገብ እንዲችል ነው።። መረጃ ሰብሳቢው ይህን በመረዳት በቆጠራ ቦታዉ ካርታ ላይ የተገለጸውን ድንበር ጠንቅቆ ማወቅና በመሬት ላይም ለመለየት መቻል አለበት። በአንዳንድ የቆጠራ ቦታ ካርታ ላይ የተገለጸው ድንበር ምናልባት በአካባቢው ያሉትን ቋሚ ነገሮች ሳይጠቅስ ሊቀር ይችላል። ይህን እና ይህን የመሳሰሉ ችግሮች ለማስወገድ መረጃ ሰብሳቢው የቆጠራ ቦታውን እየተዘዋወረ በሚያጠናበት ወቅት የቀበሌ ሊቀመንበር ወይም ተወካይ አብሮ መዞርና ዳር ድንበሩን ማሳየትና ማረጋገጥ አለበት።
4. *መረጃ ሰብሳቢው የቆጠራ ቦታውን ድንበር በአመቺ መንገድ ለማወቅ ይችል ዘንድ ከቆጠራ ቦታ ካርታው ጋር አብሮ ከሚሰጠው የካርታ መግለጫ ላይ በተገለጸው መሠረት ከሰሜን በመነሳት ጉዞውን ይጀምራል። ይህን ለማድረግ ለመረጃ ሰብሳቢው በካርታው ላይ የሰፈሩትን የሕንጻ፣ የት/ቤት፣ የቤተክርስቲያን፣ የመስጊድ፣ የመንገድና ወዘተ ስሞች፣ የወንዝ ስም ካለ፣ ለምልክትነት የተጻፉ የግለሰቦች ቤት የቆጠራ ቦታውን የሚያዋስኑ ቀበሌ፣ወረዳ፣ ቆጠራ ቦታ . . . ወዘተ. እየጠየቀና እያገናዘበ ቦታዎቹን ለይቶ ማወቅ አለበት።*

*አንድ መረጃ ሰብሳቢ በተመደበበት የቆጠራ ክልል በሚዘዋወርበት ወቅት ልዩ ልዩ ችግሮች ሊያጋጥሙት ይችላሉ። ይኸውም የካርታው ሥራ በሚሠራበት ወቅት ምንም ያልተሸፈነ ቦታ ሳይተው ወይም ቦታዎች ሳይደራረቡ እንዲሠሩ ከፍተኛ ሙከራ ቢደረግም አንዳንድ ጊዜ በቆጠራ ቦታዉ እና በአዋሳኝ የቆጠራ ቦታ መሀከል ያልተሸፈኑ ቦታዎች ሊኖሩ ይችላሉ። እንዲሁም በሁለት የቆጠራ ቦታዎች መሀከል ያለ ቦታ በሁለት የቆጠራ ቦታዎች ውስጥ ሊደራረብ ይችላል። የዚህ ዓይነት ችግር በሁለት የቆጠራ ቦታዎች ድንበር ላይ በሚያጋጥም ወቅት መረጃ ሰብሳቢው ይህን ችግር ለተቆጣጣሪው በማስታወቅ እቦታው ድረስ በመሄድ ድንበሩን ማስተከከል ይኖርባቸዋል። ካርታው የጎላ ስህተት ከታየበት እርማት ማድረግ የሚቻለው ከተቆጣጣሪው ጋር በመወያየት ብቻ ነው። ስለ ቆጠራ ካርታ ይዘት በሚገባ ለመረዳት በዚህ መመሪያ ውስጥ ተያይዘው የቀረቡትን ካርታና መግለጫ መመልከት ያስፈልጋል።*

## የቆጠራ ቦታ ካርታ ይዘት:-

### አንድ የቆጠራ ቦታ ካርታ የሚከተሉትን ያካትታል:-

1. የቆጠራ ቦታው የሚገኝበት የክልል፣ የዞን ፣ የወረዳ እና ገ/ማህበር ስም
2. የቆጠራ ቦታው የሚገኝበት ገ/ማህበር ሊቀመንበር ስም
3. የቆጠራ ቦታ መለያ/ኮድ/:- ለምሣሌ የቆጠራ ቦታ መለያ 031-03 በገበሬ ማህበር 031 ውስጥ የሚገኝ የቆጠራ ቦታ 03 ነው ::
4. በቆጠራ ቦታው ውስጥ የሚገኙ ቤተሰቦች ብዛት
5. የ ቆጠራ ቦታዉ ግምታዊ ስፋት
6. የቆጠራ ቦታው ትክክለኛ ድንበር:- የድንበሩ ዓላማ ቆጣሪው ከተወሰነለት ክልል እንዳይወጣ እና በክልሉ ውስጥ ያሉትን ቤተሰቦች ብቻ ለመመዝገብ እንዲችል ነው::
7. የካርታው ሰሜናዊ አቅጣጫ:- መረጃ ሰብሳቢው የቆጠራ ቦታ ድንበሩን በአመቺ መንገድ ለማወቅ ይችል ዘንድ ከቆጠራ ቦታ ካርታው ጋር አብሮ ከሚሰጠው የካርታ መግለጫ ላይ በተገለጸው መሠረት ከሰሜን በመነሳት ከዚያ ወደ ምሥራቅ ከዚያ ወደ ደቡብ ከዚያ ወደ ሰሜን እየተጓዘ የቆጠራ ቦታውን ዙሪያ ይጨርሳል::
8. በካርታው ውስጥ በስዕላዊ መልክ የተሰጡ ምልክቶች (Legend):- በካርታው ውስጥ የሚታዩትን ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ነገሮች ብሎ ክ/ሕንጻ፣ ወንዝ፣ መንገድ፣ለምልክትነት የተፃፉ የግለሰቦች ቤት . . . ወዘተ መረጃ ሰብሳቢው መሬት ላይ ካሉት ጋር ማገናዘብ ይኖርበታል::
9. የካርታው መስፈርት
10. የቆጠራ ቦታውን የሚያዋስኑ የክልል፣የዞን፣የወረዳ፣ የገ/ማህበር. . . ወዘተ ስም ወይንም ቁጥር::

*በተጨማሪም እያንዳንዱ የቆጠራ ቦታ የድንበር መግለጫ ፅሁፍ ያለዉ በመሆኑ ይህ ፅሁፍ ካርታውን በበለጠ ስለሚያብራራ መረጃ ሰብሳቢው ከካርታው ጋር በአንድነት መረዳት አለበት:: ለአብነት ያህል አንድ የገጠር ካርታ ከነመግለጫው ከዚህ ቀጥሎ ተሰጥቷል::*

## የናሙና ቤተሰቦች ማስተላለፊያ ቅጽ አሞላል ቅጽ-98/1

ቀደም ሲል በናሙና የተመረጡት 25 ቤተሰቦች ለአሰራር ያመች ዘንድ ወደ የናሙና ቤተሰቦች ማስተላለፊያ ቅጽ-ቅጽ 98/1 ተላለፊዋል:: የነዚህም ቤተሰቦች ዝርዝር በቅጹ ላይ እደሚከተለው ከዚህ በታች የተሰጠውን ማብራሪያ በመመልከት መረዳት ያስፈልጋል::

### ክፍል አንድ የአካባቢ መለያ

ዓምድ 1 ክልል

ጥናቱ የሚካሄድበት የቆጠራ ቦታ የሚገኝበት ክልል ስም በዚህ ዓምድ ተሞልቷል::

ዓምድ 2 ዞን

ጥናቱ የሚካሄድበት የቆጠራ ቦታ የሚገኝበት ዞን ስም/ቁጥር/ በዚህ ዓምድ ተሞልቷል::

**ዓምድ 3 ወረዳ**

ጥናቱ የሚካሄድበት የቆጠራ ቦታ የሚገኝበት ወረዳ ስም በዚህ ዓምድ ተሞልቷል።

**ዓምድ 4 ገበሬ ማኅበር**

ጥናቱ የሚካሄድበት የቆጠራ ቦታ የሚገኝበት ገበሬ ማኅበር ስም በዚህ ዓምድ ተሞልቷል።

**ዓምድ 5 የቆጠራ ቦታ ቁጥር**

ጥናቱ የሚካሄድበት የቆጠራ ቦታ መለያ ቁጥር በዚህ ዓምድ ተሞልቷል።

**ክፍል ሁለት የናሙና ቤተሰቦች ዝርዝር (ከአምድ 6 -አምድ 8)**

*በዚህ ክፍል በናሙና የተመረጡት 25ቱም ቤተሰቦች ወደዚህ ቅጽ የተላለፉ ሲሆን በመጀመሪያም ከሴፍቲነት ከታቀፉት ቤተሰቦች የተመረጡት ናሙናዎች ሲሆኑ ከዚያም ካልታቀፉት ቤተሰቦች እንዳመራረጥ ቅደም ተከተላቸው ናቸው።*

**አምድ 6 የተመራጭ ቤተሰቦች ተከታታይ ቁጥር**

በዚህ አምድ በምዝገባ ወቅት በመመዝገቢያው ቅጽ ከቅጽ ምዋ 98/0 ላይ 25 ቱ ናሙና ቤተሰቦች የያዙትን የቤተሰብ ተራ ቁጥር በመውሰድ ወደዚህ አምድ ተሞልቷል።

**አምድ 7 የተመራጭ ቤተሰብ ኃላፊ ስም ከነአያት**

በዚህ አምድ ለ25 ቱ ናሙና ቤተሰቦች የያዙትን የቤተሰብ ተራ ቁጥር በመከተል የተመራጩን ቤተሰብ ኃላፊ ስም ከነአያት ከመመዝገቢያው ቅጽ (ቅጽ 98/0) በመውሰድ በጥንቃቄ በመለየት ተሞልቷል።

**አምድ 8 የአመራረጥ ቅደም ተከተል**

በዚህ አምድ ለ25 ቱ ናሙና ቤተሰቦች የያዙትን የናሙና ምርጫ ተራ ቁጥር ከመዝገቢያው ቅጽ የታቀፈ ቤተሰብ እና ያልታቀፈ ቤተሰብ የአመራረጥ ቅደም ተከተል ከቅጽ 98/0 በመውሰድ ወደዚህ ቅጽ ቅጽ ምዋ 98/1 ተሞልቷ።

**አምድ 9 አስተያየት**

በአጠቃላይ ይህ ቅጽ ሲሞላ ወ ይም ወጠይቁ ሲሞላ ያጋጠሙ ሁኔታዎች በሙሉ በዚህ አምድ ተሞልቶ ሊያጋጥም ይችላል።

## ቅፅ ምዋ2000/2 የቤተሰብ አባላትንና ዲሞግራፊያዊ ባህሪያት መመዝገቢያ አሞላል

ይህ ቅጽ የተዘጋጀው ለጥናቱ በተመረጠ ቤተሰብ ውስጥ የሚገኙ የቤተሰብ አባላትንና የእያንዳንዱ አባል ዲሞግራፊያዊ ባህሪያትን መመዝገቢያ ነው:: በመሆኑም ቅጽን ለመሙላት የቤተሰብ አባላት ተብለው የሚወሰዱት እነማን እንደሆኑ ማወቅ ስለሚያስፈልግ የቤተሰብ አባላት ትርጉም እንደሚከተለው ተሰጥቷል::

በመመዝገቢያ ቅጽ አሞላል ወቅት እንደተገለጸው ቤተሰብ በአንድ ቤት ውስጥ ወይም በተቀራረቡ ቤቶች ውስጥ እየኖሩ ምግባቸውን በጋራ እያዘጋጁ የሚመገቡ ዘመዳሞች ወይም ዘመዳሞች ያልሆኑ ሰዎች ማለት ነው::

የቤተሰብ አባል የሚባለው ቢያንስ ስድስት ወር ሙሉ ያለማቋረጥ ከቤተሰቡ ጋር ያደረ እንደሆነ ነው:: ከቤተሰቡ ጋር ለዘለቄታው ለመኖር የመጡ ሁሉ ከቤተሰቡ ጋር መኖር ከጀመሩ ስድስት ወር ባይሞላቸውም እንደቤተሰቡ አባል ይቆጠራሉ:: ከስድስት ወር በታች ከቤተቡ ለጊዜው ተለይተው የቆዩ አባላት የዚሁ ቤተሰብ አባል ሆነው ይቆጠራሉ:: ነገር ግን ከቤተሰቡ ተለይተው ከሄዱ ስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ ወይም ከስድስት ወር በላይ ለመቆየት አቅደው የሄዱ ከቤተሰቡ ከወጡ ስድስት ወር ባይሞላቸውም እንደቤተሰቡ አባል አይቆጠሩም::

<u>ክፍል 1 የአካባቢ መለያ</u>

<u>ዓምድ</u> 1-4 <u>ክልል፣ዞን፣ወረዳ፣ገበሬ ማህበር</u>

በእነዚህ ዓምዶች ጥናቱ የሚካሄድበት ቆጠራ ቦታ የሚገኝበት ክልል፣ዞን፣ወረዳና ገበሬ ማህበር በቅደም ተከተል በተሰጡት ቦታዎች ላይ ይመዘገባሉ::

<u>ዓምድ</u> -5 <u>ቆጠራ ቦታ</u>

ጥናቱ የሚካሄድበት ቆጠራ ቦታ ቁጥር በተሰጠው ቦታ ይሞላል::

<u>ዓምድ</u> -6 <u>የቤተሰብ መለያ ቁጥር</u>

በዚህ ዓምድ በጥናቱ የተመረጠው ቤተሰብ መለያ ቁጥር ከቅፅ ምዋ98/1 ክፍል 2 ዓምድ 6 በመውሰድ ይሞላል::

<u>ዓምድ</u> -7 <u>የቤተሰቡ ኃላፊ ስም</u>

በዚህ ዓምድ ለጥናቱ የተመረጠው ቤተሰብ ኃላፊ ስም ከቅጽ ምዋ98/1 ክፍል 2 ዓምድ 2 በመውሰድ ይሞላል::

<u>ክፍል 2ሀ-</u> የቤተሰብ አባላት ዝርዝርና የስነ-ሕዝብ ባህርያት

<u>ዓምድ</u> -8 <u>የቤተሰብ አባል መለያ ቁጥር</u>

በዚህ ዓምድ ከኃላፊው በመጀመር በቅደም ተከተል በሁለት ዲጅት ቁጥር ይሰጣል::

## ዓምድ -9 የቤተሰብ አባል ስም

በዘህ ዓምድ የእያንዳንዱ አባል ስም (ከኃላፊ በመጀመር) ይመዘገባል::

## ዓምድ -10 ከቤተሰብ ኃላፊ ጋር ያለው ዝምድና

በዚህ ዓምድ እያንዳንዱ አባል ከቤተሰብ ኃላፊ ጋር ያለው ዝምድና እየተጠየቀ በቃላት ከተጻፈ በኋላ ለዝምድና ዓይነት የተሰጠው ኮድ ይሞላል:: የዝምድና ኮዶቹ የሚከተሉት ናቸው::

ኃላፊ = 1
የኃላፊው ሚስት/ባል = 2
የኃላፊው ልጅ = 3
የልጅ ልጅ = 4
እናት/አባት = 5
ወንድም/እህት = 6
የወንድም/እህት ልጅ = 7
አጎት/አክስት = 8
አማች = 9
አማት = 10
ምራት = 11
አያት = 12
ሌላ የኃላፊው ወይም
የኃላፊው(ሚስት/ባል) ዘመድ = 13
ሠራተኛ = 14
ዘመድ ያልሆነ = 15

## ዓምድ 11 ዕድሜ በሙሉ ዓመት

በዚህ ዓምድ የእያንዳንዱ ቤተሰብ አባል ዕድሜ ያጠናቀቀው ዓመት (በሙሉ ዓመት) እየተጠየቀ ይሞላል:: ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች ለሆኑ ህጻናት ዕድሜ በወር ይሞላል:: ከዓመት በታች የሆናቸው ህጻናት ካሉ «00» ይሞላል::

**ማስታወሻ:- ዕድሜን ለማስላት እንዲረዳ በመመሪያው መጨረሻ የተሰጠውን የዋና ዋና ታሪካዊ ድርጊቶች ዝርዝር ተጠቀም::**

## ዓምድ 12 ፆታ

በዚህ ዓምድ ለእያንዳንዱ አባል ፆታው ወንድ ከሆነ «1» ሴት ከሆነች ደግሞ «2» ይሞላል::

## ዓምድ 13 የፈጸሙት ከፍተኛ ክፍል

በዚህ ዓምድ ዕድሜያቸው 5 ዓመትና በላይ ለሆናቸው የቤተሰብ አባላት የፈጸሙት ከፍተኛ ክፍል ተጠይቆ ይሞላል:: ያልተማረ ከሆነ ግን "0" ይሞላል:: ለፈጸሙት ክፍል የሚሰጡት ኮዶች የሚከተሉት ናቸው::

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሾፌር/መካኒክ | = 9 | እረኝነት | = 20 |
| የፋብሪካ ሠራተኛ | = 10 | ሌላ | = 21 |

<u>ዓምድ 15ለ</u> <u>በሌላ ማንኛውም ሥራ ክህሎት አለወት?</u>

በዚህ ዓምድ ዕድሜያቸው 7 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆናቸው የቤተሰቡ አባላት በሌላ ማንናውም ስራ ክህሎት መኖር አለመኖሩን በመጠየቅ ክህሎት የለኝም ካሉ ኮድ 1 ሲሞላ ክህሎት ያላቸው ከሆነ ግን ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ኮዶች መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

| | |
|---|---|
| ክህሎት የለኝም ............................................. | = 1 |
| ያለኝ ክህሎት ዋነኛ ስራዬ ላይ ነው ........................... | = 2 |
| ያለኝ ክህሎት ሁለተኛ ስራዬ ግብርና ላይ ነው ....... | = 3 |
| ያለኝ ክህሎት ሁለተኛ ስራዬ መንገድ ስራ ላይ ነው ...... | = 4 |
| ያለኝ ክህሎት ሁለተኛ ስራዬ ግምበኝነት ላይ ነው ....... | = 5 |
| ያለኝ ክህሎት ሁለተኛ ስራዬ አናጺነት ላይ ነው ...... | = 6 |
| ያለኝ ክህሎት ሁለተኛ ስራዬ ቤት መክደን ላይ ነው............. | = 7 |
| ያለኝ ክህሎት ሁለተኛ ስራዬ አንጥረኛ ላይ ነው | = 8 |
| ያለኝ ክህሎት ሁለተኛ ስራዬ ማሽን ኦፐሬተር ላይ ነው | = 9 |
| ሌላ ካለ ይጠቀስ | = 10 |

<u>ዓምድ 16</u> <u>የተጠቀሱት አባል 1998 ዓ/ም በቤተሰቡ ውስጥ ይኖሩ ነበር?</u>

በዚህ ዓምድ ለእያንዳንዱ አባል በ1998 ዓ/ም ውስጥ ከቤተሰቡ ጋር ይኖር እንደነበረ እየተጠየቀ ይኖር ከነበረ ኮድ «1» ካልነበረ ደግሞ ኮድ «2» በተሰጠው ቦታ ይሞላል፡፡ (ኮድ 1 ከተሞላ ወደ ክፍል 2ለ ይታለፍ ኮድ 2 ከተሞላ ወደ ዓምድ 17 ይታለፍ)

<u>ዓምድ 17</u> <u>በስንት ዓመተ ምህረት ወደ ቤተሰቡ መጡ?</u> (በዓምድ 16 ኮድ 2 ከተሞላ)

እያንዳንዱ አባል ወደ ቤተሰቡ መቼ እንደተቀላቀለ/እንደመጣ እየተጠየቀ በዚህ ዓምድ በተሰጠው ቦታ ዓመተ ምህረቱ ይሞላል፡፡

<u>ዓምድ 18</u> <u>እንዴት ወይም በምን ሁኔታ ወደ ቤተሰቡ መጡ?</u>

እያንዳንዱ አባል ወደ ቤተሰቡ በምን ምክንያት ወይም እንዴት እንደተቀላቀለ እየተጠየቀ ምክንያቱ በተሰጠው ቦታ ይመዘገባል፡፡ ከዚያም የምክንያቱ ኮድ ይሞላል፡፡ የምክንያቶቹ ኮዶች እንደሚከተለው ተሰጥቷል፡፡

<u>ለልጆች/ህፃናት</u>

| | | | |
|---|---|---|---|
| እዚሁ የተወለደ | = 1 | ስለታመሙ አስታማሚ ፍለጋ | = 11 |
| ከቤተሰብ ጋር የመጣ | = 2 | ስለአረጁ ሊጠሩ | = 12 |
| ት/ቤት እንዲቀርበው/ለትምህርት | = 3 | ከውትድርና ተመላሽ | = 13 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ቤተሰቡ ሞቶበት በማደኅየመጣ | = 4 | ሌላ ምክንያት | = 14 |
| ቤተሰቦቹ ሊንከባከቡት ባለመቻላቸው | = 5 | በመፋታት/በመለያየት | = 15 |

**ለአዋቂ**

| | | | |
|---|---|---|---|
| በጋብቻ | = 6 | ከዘመዶቹ ጋር ለመኖር | = 16 |
| ሥራፍለጋ | = 7 | ከሠፈራ ተመላሽ | = 17 |
| ለሥራው እንዲቀርባቸው | = 8 | ከቤተሰቦቹ ጋር ለመኖር | = 18 |
| የግብርና ሥራ ወይም ሌላ ተመሳሳይ ሥራ ለማገዝ | = 9 | የሥራው ኮንትራት በማለቁ | = 19 |
| ሌሎች ዘመዶቹን ለመንከባከብ | =10 | ቤተሰቡን በቤት ውስጥ ሥራ ለማገዝ | = 20 |

**ክፍል 2ለ የቤተሰቡና የኃላፊው ሌሎች ባህሪያት**

ባለፉት ሰባት ቀናት ከቤተሰቡ ተለይተው ወይም በሌላ ምክንያት ሳይመገቡ የቀሩ አባላት ካሉ በዓመድ 19 መለያ ቁጥራቸውን ከቅጽ ምቀ 2000/2 ዓምድ «8» በመውሰድ መሙላትና በዓምድ 20 ደግሞ እያንዳንዱ አባል በሳምንት ለምን ያህል ቀናት ሳይመገብ እንደቀረ በመጠየቅ የቀኑ ብዛት ይሞላል::

**ክፍል 2ሐ. የቀድሞው ቤተሰብ አባላት ሁኔታ**

**ጥያቄ 21.** ከሰኔ 1/98 ጀምሮ ምን ያህል የቤተሰብ አባላት ቤተሰቡን እንደለቀቁ ወይም በሞት እንደተለዩ በመጠየቅ ብዛታቸው በተሰጠው ቦታ ይመዘገባል::

**ዓምድ 22.** መለያ ቁጥር አግኝቷል::

**ዓምድ 23.** የአባሉ ስም መመዝገቢያ::

**ዓምድ 24 ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና**

የቤተሰቡ አባል ከመለየታቸው በፊት ከኃላፊው ጋር ያላቸው ዝምድና ምን እንደነበረ በመጠየቅ ከመዘገቡ በኋላ ተስማሚውን ኮድ በክፍል 2ሀ ለዓምድ 10 ከተሰጠው በመምረጥ መሙላት ያስፈልጋል::

**ዓምድ 25 ፆታ**

የተለዩት/የለቀቁ አባል ፆታ ተጠይቆ ወንድ ከሆነ ኮድ «1» ሴት ከሆነች ደግሞ ኮድ «2» ይሞላል::

**ዓምድ 26 ዕድሜ**

የተለዩት/የለቀቁ አባል ሲለዩ ዕድሜያቸው ስንት እንደነበረ በመጠየቅ በሙሉ ዓመት በተሰጠው ይመዘገባል፡፡

**ዓምድ 27 ያጠናቀቁት ከፍተኛ ክፍል**

የተለዩት/የለቀቁት አባል ከቤተሰቡ ሲለዩ ያጠናቀቁት ክፍል ተጠይቆ በተሰጠው ቦታ ይሞላል፡፡ ያልተማሩ ከነበሩ ኮድ «0» ይሞላላቸዋል፡፡ ኮዶቹን በተመለከተ በክፍል 2ሀ ለዓምድ 13 የተሰጡትን አማራጮች መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

**ዓምድ 28 በየትኛው ዓመት ተለዩ/ለቀቁ?**

የተለያዩ/የለቀቁ አባል በየትኛው ዓመት እንደተለዩ/ለቀቁ ተጠይቆ በተሰጠው ቦታ ዓመቱ ይመዘገባል፡፡

**ዓምድ 29 እንዴት ወይም በምን ምክንያት ከቤተሰቡ ተለዩ?**

የተለዩት አባል እንዴት ወይም በምን ምክንያት ከቤተሰቡ እንደተለዩ በመጠየቅ ምክንያቱ ይመዘገባል፡፡ ለዚህ ጥያቄ የሚከተሉትን ኮዶች ተጠቀሙ፡፡

**ህፃናት**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ከቤተሰቡ ጋር ለመሆን | = 1 | በጉዲፈቻ ወይም በማደጎ | = 4 |
| ለት/ቤት እንዲቀርበው/ለትምህርት | = 2 | ለለታመመ ለሕክምና | = 5 |
| ቤተሰቦቹ ሊንከባከቡት ባለመቻላቸው/ በመታመማቸው | = 3 | ሞት | = 6 |

**ለአዋቂ**

| | | | |
|---|---|---|---|
| በጋብቻ | = 7 | በመሬት እጥረት | = 15 |
| በፍቺ | = 8 | ሌሎች ዘመዶቹን ለመንከባከብ | = 16 |
| ወደቤቱ በመሄድ | = 9 | ወደ ሠራዊቱ በመቀላቀሉ | = 17 |
| ሥራ ፍለጋ | = 10 | ለለታመመ ለህክምና በመሄዱ | = 18 |
| ሥራ ስላገኘ | = 11 | የሄደበት ምክንያት አይታወቅም | = 19 |
| ለሥራ እንዲቀርበው ብሎ በመሄዱ | = 12 | ሞት | = 20 |
| በሄደበት ቦታ ያለውን ሥራ ለመሥራት | = 13 | ሌላ | = 21 |
| ኮንትራቱ በማለቁ | = 14 | | |

**ክፍል 3. ከ18 ዓመት በታች የሆናቸው ልጆች የሥራና የትምህርት ሁኔታ**

ዕድሜያቸው 18 ዓመት በታች የሆናቸው በሙሉ ወደዚህ ክፍል ይተላለፋሉ፡፡

ዓምድ 30. መለያ ቁጥር

በዚህ ዓምድ የቤተሰብ አባል ቁጥሩ ከቅጽ ምዋ 2000/2 ዓምድ 8 በመውሰድ ይሞላል::

ዓምድ 31. የልጁ የተፈጥሮ ወላጆች መለያ ቁጥር

በዚህ ዓምድ የልጁ የተፈጥሮ ወላጆች (አባትና እናት) መለያ ቁጥር ከቅጽ ምዋ2000/2 ዓምድ 8 በመውሰድ ይሞላል:: በቤተሰቡ ውስጥ የተፈጥሮ ወላጆቹ ከሌሉ በቤተሰቡ ውስጥ የሚገኙ አሳዳጊው ወይም ተንከባካቢው መለያ ቁጥር ከቅጽ ምዋ 2000/2 ዓምድ 8 ተወስዶ ይሞላል::

ዓምድ 32. በዓምድ 30 የተመዘገበው ልጅ የሚከተሉትን ስራዎች በሳምንት ለስንት ቀናት ይሰራል?

በዓምድ 30 የተመዘገበው ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ልጅ በዓምድ 32 ሥር ከተጠቀሱት ሥራዎች ( የቤት ውስጥ ሥራ ፣ እርሻ ወይም ከብት ጥበቃ፣ከቤተሰቡ ውጭ በክፍያ) ባለፉት ሰባት ቀናት ለምን ያህል እንዳደሠራ በመጠየቅ ብዛቱ በተሰጠው ቦታ ይሞላል::

ዓምድ 33. በዓምድ 30 የተመዘገበው ልጅ በስንት ዓመቱ ትምህርት ጀመረ?

በዓምድ 30 የተመዘገበው ልጅ በስንት ዓመቱ ትምህርት እንደጀመረ በመጠየቅ ዓመቱ ይመዘገባል:: ትምህርት ካልተማረ/ካልገባ ግን « 98 » ይሞላና ወደ ዓምድ 38 ይታለፍ::

ዓምድ 34. በዓምድ 30 የተመዘገበው ልጅ ከሁለት ዓመት በፊት (ከሰኔ/97 -ግንቦት /98) /ት/ቤት ተመዝግቦ ቢያንስ ግማሹን ተከታትሎ ነበር?

በዓምድ 30 የተመዘገበው ልጅ ከሁለት ዓመት በፊት (ከሰኔ/97 -ግንቦት /98) ት/ቤት ተመዝግቦ ቢያንስ ግማሹን መከታተል አለመከታተሉ ተጠይቆ ከተከታተለ ኮድ «1» ካልተከታተለ ደግሞ ኮድ «2» በዚህ ዓምድ ይሞላ::

ዓምድ 35. በዓምድ 30 የተመዘገበው ልጅ ባለፉት 12 ወራት (ሰኔ/99 - ግንቦት/2000) ትምህርት ይማር ነበር?

በዓምድ 30 የተመዘገበው ልጅ ባለፉት 12 ወራት (ሰኔ/99 - ግንቦት/2000) ትምህርት ይማር እንደነበረ ተጠይቆ ከተማረ ኮድ «1» ጨርሶ ያልተማረ ከሆነ ኮድ «2» ተሞልቶ ወደ ዓምድ 38 ይታለፍ፣ ያቋረጠ ከሆነ ደግሞ ኮድ «3» ተመልቶ ወደ ዓምድ 37 ይታለፍ::

**ዓምድ 36. በዓምድ 30 የተጠቀሰው ልጅ ባለፉት 12 ወራት ትምህርቱን እያቋረጠ ወላጆቹን በሥራ ያግዝ ነበር? ካገዘ ለምን ያህል ሣምንት?**

በዓምድ 30 የተጠቀሰው ልጅ ባለፉት 12 ወራት ትምህርቱን እያቋረጠ ወላጆቹን በሥራ ማገዝ አለማገዙን በመጠየቅ ካገዘ ለምን ያህል ሣምንት እንዳገዘ ተጠይቆ በዚህ ዓምድ በተሰጠው ቦታ ይሞላል:: ካላገዘ ግን በተሰጠው ክፍት ቦታ «0» ይሞላል:: የትምህርት እረፍትን በተመለከተ እንዳቋረጠ አይቆጠርም::

**ዓምድ 37. በዓምድ 30 የተጠቀሰው ልጅ ትምህርቱን በስንት ዓመተ ምህረት አቋረጠ?**

በዓምድ 30 የተጠቀሰው ልጅ ትምህርቱን አቋርጦ ከሆነ መቼ እንዳቋረጠ ተጠይቆ ዓመተ ምህረቱ በተሰጠው ቦታ ይመዘገባል::

**ዓምድ 38. በዓምድ 30 የተጠቀሰው ልጅ ለምን አይማርም/ ለምን አቋረጠ?**

በዓምድ 30 የተጠቀሰው ልጅ የማይማር ከሆነ ወይም ትምህርቱን ካቋረጠ ምክንያቱ ምን እንደሆነ ተጠይቆ ይሞላል::

**ለምክንያቶቹ የሚከተሉትን ኮዶች ተጠቀሙ**

| | | | |
|---|---|---|---|
| በጣም ልጅ ስለሆነ | =1 | የሚጠቅመውን እዚሁ ቤቱ ስለሚማር | =10 |
| ለእርሻ ሥራ ስለሚያስፈልግ | =2 | በመታመሙ | =11 |
| ለሌላ(ቤተሰቡ) ሥራ ስለሚያስፈልግ | =3 | በአካባቢው በሚገኝ ት/ቤት ቦታ ባለመኖሩ | =12 |
| የታመሙ ወይም ያረጁ ለመከባከብ | =4 | ለሃይማኖቱ ተስማሚ ትምህርት የሚሰጥ ትምህርት ቤት ስለሌላ | =13 |
| ተቀጥሮ መስራት ስለነበረበት (ደመወዝ ማግኘት ስለነበረበት) | =5 | ጥሩ/አስተማማኝ ባለመሆኑ | =14 |
| ለትምህርት የሚከፈለው ውድ በመሆኑ | =6 | በማግባቱ | =15 |
| ት/ቤቱ በመራቁ | =7 | ሌላ ምክንያት | =16 |
| ት/ቤቱ ለሴት ልጆች ተስማሚ ባለመሆኑ | =8 | | |
| መማር ስለማይጠቅም ወይም ገቢ ስለማያስገኝ | =9 | | |

## የቅፅ ምዋ 2000/3-የእርሻ መሬት ይዞታ ፣የሰብል (ጊዜያዊ /ቋሚ/) ምርት እና አቅርቦትን የተመለከተ አሞላል መመሪያ::

ይህ ቅፅ ለጥናቱ በተመረጡ ቤተሰቦች የሚሞላ ሲሆን ቅፁ የእርሻ መሬት ይዞታ፣ የግብርና ግብአት አጠቃቀም የሰብል ምርት ክምችት እና ሽያጭ እንዲሁም የሰው ሀይል አጠቃቀም ሁኔታ የሚሞሉበት ነው::

### ክፍል1:- የአካባቢ መለያ

**ዓምድ 1:- ክልል**

ጥናቱየሚካሔድበት ክልል ስምና ኮድ በዚህ አምድ ይሞላል::

**ዓምድ 2:- ዞን**

ጥናቱ የሚካሔድበት ዞን ስም ወይም ቁጥር በዚህ አምድ ይሞላል::

**ዓምድ 3:- ወረዳ**

ጥናቱ የሚካሔድበት ወረዳ ስምና ኮድ በዚህ አምድ ይሞላል::

**ዓምድ 4:- ገበሬ ማህበር**

ጥናቱ የሚካሔድበት ገበሬ ማህበር ስምና ኮድ በዚህ አምድ ይሞላል::

**ዓምድ 5:- የቆጠራ ቦታ**

ጥናቱ የሚካሔድበት የቆጠራ ቦታ ቁጥርና ኮድ በዚህ አምድ ይሞላል::

**ዓምድ 6:- የቤተሰብ መለያ ቁጥር**

ለጥናቱ የተመረጠው የቤተሰብ መለያ ቁጥር ከቅፅ ምዋ 98/1 ክፍል 2 ከአምድ 6 በመውሰድ ይሞላል::

**ዓምድ 7:- የቤተሰብ ሀላፊ ስም**

ለጥናቱ የተመረጠው ቤተሰብ ሀላፊ ስም ከቅፅ ምዋ 98/1 ክፍል 2 ከአምድ 7 በመውሰድ ይሞላል::

**ማስታወሻ:-** ከክልል እስከ ቆጠራ ቦታ ያሉት መለያ ኮዶች ከቅርንጫፍ ፅ/ቤት በሚሰጠው ዝርዝር መሠረት ይሞላሉ::

## <u>ክፍል 2፡- የእርሻ መሬት ይዞታ (1999/2000 ዓ.ም)</u>

ይህ ክፍል ቤተሰቡ የግብርና ስራ እንቅስቃሴ የሚያደርግበት፣ ለሰው ያከራየው በአዳሪነት የተያዘ በደን የተያዘ መሬት ወዘተ... መሬት በመጠየቅ በፓርስል ደረጃ መረጃ የሚመዘገብበት ነው።

### <u>ዓምድ 8፡-</u> <u>የፓርስል ቁጥር</u>

በቤተሰብ ውስጥ የግብርና ስራ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ የቤተሰቡ አባላት ያላቸውን መሬት በ2000 መኸርና በ1999 በልግ ወቅት ሳይደጋገሙ በዚህ አምድ ተከታታይነታቸው በጠበቀ መልኩ የፓርስል ቁጥር ይሰጣቸዋል። በአሁኑ ወቅት ያሉት ሌሎች የመሬት አጠቃቀሞችም የፓርስል ቁጥር ይሰጣቸዋል።

### <u>ዓምድ 9፡-</u> <u>የፓርስል ስም</u>

በዓምድ 8 የፓርስል ቁጥር የተሰጣቸው ፓርስሎች የፓርስል ስም በዚህ አምድ ይሞላል። ለምሣሌ ከወንዙ ተሻግሮ ያለው ፓርስል ፣ከመንገዱ አለፍ ብሎ፣ ቤቱ አካባቢ ወዘተ በማለት ይሰጣል። ይህ መላሹ በሚሰጠው ስያሜ የሚወሰን ይሆናል ማለት ነው።

### <u>ዓምድ 10 እና 11 የስፋት መጠንና መለኪያ</u>

### <u>ዓምድ 10፡-</u> <u>የስፋት መጠን</u>

በዚህ ዓምድ ቤተሰቡ በዓምድ ያስመዘገበው ፓርስል የስፋት መጠኑ ተጠይቆ በዚህ አምድ ይሞላል። ይህም ማለት በፓርስሉ ውስጥ ያሉትን የመሬት አጠቃቀሞች ስፋት በማጠቃለል ይሞላል ማለት ነው።

### <u>ዓምድ 11፡-</u> <u>የስፋት መለኪያ</u>

በዚህ አምድ እያንዳንዱን ፓርስል ውስጥ የለካበት የአካባቢ መለኪያ ዓይነት በተሰጠው ቦታ ተሞልቶ ኮዱ ከዚህ ክፍል መጨረሻ ከተሰጠው በመውሰድ ይሞላል።

### <u>ዓምድ 12፡-</u> <u>ከቤት እስከ ይዞታው ለመሄድ የሚወስደው ጊዜ</u>

ቤተሰቡ ከቤቱ ወደ እያንዳንዱ ፓርስል ለመድረስ የሚወስድበት ጊዜ ተጠይቆ የሚሰጠው መልስ ቤቱ አጠገብ ከሆነ ኮድ «1»፣ ከ5 ደቂቃ ያነሰ ከሆነ ኮድ «2»፣ ከ5 ደቂቃ እስከ ከ15 ደቂቃ ያነሰ ከሆነ ኮድ «3» ከ15 ደቂቃ እስከ 1 ሰአት ያነሰ

ከሆነ ኮድ«4»፣ አንድ ሰዓት እና ከዚያ በላይ ከሆነ ኮድ «5» በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል::

**ዓምድ 13:- የአየር ጠባይ ሁኔታ (ደጋ= 1 ወይና ደጋ=2 ቆላ=3 በረሀ=4)**

ቤተሰቡ ያስመዘገበው እያንዳንዱ ፓርስል የአየር ጠባይ ሁኔታ ተጠይቆ ደጋ ከሆነ ኮድ «1» ወይና ደጋ ከሆነ ኮድ «2» ቆላ ከሆነ ኮድ «3» በረሀ ከሆነ ኮድ«4» ይሞላል::

**ዓምድ 14:- የመሬት አቀማመጥ (Slope) (ሜዳ =1 ተዳፋት =2 ገደላማ =3 ቅልቅል =4)**

ቤተሰቡ ያስመዘገበውን እያንዳንዱን ፓርስል አስመልክቶ የመሬት አቀማመጡ (Slope) ሜዳ ከሆነ በተሰጠው ቦታ ተሞልቶ ኮድ «1» ተዳፋት ከሆነ ኮድ «2» ገደላማ ከሆነ ኮድ «3» የሁለቱ ወይም የሶስቱ ቅልቅል ከሆነ ኮድ «4» በተሰጠው ቦታ ይሞላል::

**ዓምድ 15:- የመሬት ለምነት ሁኔታ( ለም=1 ለም-ጠፍ=2 ጠፍ=3)**

ቤተሰቡ ያስመዘገበውን እያንዳንዱን ፓርስል አስመልክቶ የመሬት ለምነቱ ሁኔታን በመጠየቅ ለም ከሆነ ኮድ «1» ለም-ጠፍ ከሆነ ኮድ «2» ጠፍ ከሆነ ደግሞ ኮድ «3» በተሰጠው ቦታ ይሞላል::

**ዓምድ 16:- ይዞታው የተያዘው በስንት ዓመት ምህረት ነው?**

ቤተሰቡ ያስመዘገበውን እያንዳንዱን ፓርስል በይዞታነት የያዘው በስንት ዓመት ምህረት እንደሆነ በመጠየቅ በዚህ አምድ ይሞላል::

**ዓምድ 17:- ይዞታው በምን ሁኔታ ተያዘ/ተገኘ**

ቤተሰቡ ያስመዘገበው እያንዳንዱ ፓርስል በምን ሁኔታ እንዳተያዘ/ እንደተገኘ ተጠይቆ በአምዱ ከተሞላ በኋላ ተስማሚውን ኮድ ከዚህ ክፍል መጨረሻ በመውሰድ ይሞላል::

**ዓምድ 18:- በይዞታው ላይ ግንባታ ከተካሄደ ዋና የሆኑትን ሁለቱን ጥቀስ**

ቤተሰቡ በስመዘገበው እያንዳዱ ፓርስል ግንባታ ከተካሄደ ዋናዎቹን ሁለቱን ብቻ በዚህ አምድ በመጥቀስ ተስማሚውን ኮድ ከዚህ ክፍል መጨረሻ በመውሰድ ይሞላል:: (ገጽ 37-40 ያለውን ይመልከቱ)

__ዓምድ 19፡-__ የአካባቢ  የስፋት መለኪያ

ቤተሰቡ በአምድ 9 ያለውን ፓርስል የለካበትና በአምድ 11 ላይ የተጠቀሰው የአካባቢ የስፋት መለኪያ በዚህ አምድ ተላልፎ ይሞላል፡፡ ተስማሚውን ኮድም ከዚህ ክፍል መጨረሻ በመውሰድ ይሞላል፡፡

__ዓምድ 20፡-__ __አንድ ሄክተር በዓምድ 11/19 የተጠቀሰው የአካባቢ መለኪያ ምን ያህል ይሆናል?__

በዚህ አምድ አንድ ሄክታር በዓምድ 19 በተጠቀሰው የአካባቢ የስፋት መለኪያ ምን ያህል ሊሆን እንደሚችል ተጠይቆ ይሞላል፡፡

__ክፍል 3፡-__ __የሰብል ምርት ከሰኔ 1/1999 ዓ.ም. እስከ ግንቦት 30/2000 ዓ.ም.__

ሀ. __የመኸር ወቅት ሰብሎችና የመሬት አጠቃቀም (2000)__

__ዓምድ 21፡-__ __የፓርስል ቁጥር__

በዚህ ዓምድ ቤተሰቡ በክፍል 2 በይዞታነት ካስመዘገባቸው ጠቅላላ የመሬት ይዞታዎች በ2000 መኸር ወቅት የተጠቀመባቸው ወደዚህ ተላልፈው ይመዘገባሉ፡፡

__ዓምድ 22፡-__ __የማሣ ቁጥር__

የማሣ ፅንሰ ሀሣብን ተመርኩዞ በቤተሰቡ ያሉ የመሬት አጠቃቀሞች የማሳ ቁጥር ይሰጣቸዋል፡፡ ለድብልቅ ሰብሎች የማሣ ቁጥር የሚሰጠው ሰብሎቹ ወደታች ከተዘረዘሩ በኋላ የፓርስል እና የማሣ ቁጥሩ በመደጋገም ይሆናል፡፡

__ዓምድ 23፡-__ __የመሬት አጠቃቀም አይነት__

የፓርስልና የማሣ ቁጥሮች ተሰጣቸው የመሬት አጠቃቀሞች (በሰብል የተያዙ፣ ዕዳሪ መሬት በግጦሽ ወዘተ... እና ለሌሎች ሰዎች በኪራይ መልክ የሰጣቸውን ይዞታዎች በሙሉ) አይነታቸውን በአምዱ ላይ በማስፈር ኮዳቸውን ከዚህ ክፍል መጨረሻ በመውሰድ ይሞላል፡፡

__ዓምድ 24፡-__ __የሰብል/የመሬት አጠቃቀም ስም__

ቤተሰቡ በመኸር ወቅት ያመረታቸውን ሰብሎች ወይም ያሉትን የመሬት አጠቃቀምች እንዲሁም ለሰዎች ያከራያቸውን ማሳዎች በዚህ ዓምድ ከመዘገቡ በኋላ ተስማሚውን ኮድ ከዚህ ክፍል መጨረሻ በመውሰድ ይሞላል፡፡

**ዓምድ 25:- የይዞታው የኪራይ ሁኔታ**

ቤተሰቡ በአምድ 24 ላይ የጠቀሰውን የመሬት አጠቃቀም ወይም ሰብል ያለበትን እያንዳንዱ መሬት አስመልክቶ በመጠየቅ በኪራይ ያልተሰጠ ከሆነ ኮድ = 1 ፡ በኪራይ የተያዘ ከሆነ ኮድ = 2፣ ለሌላ በኪራይ የተሰጠ ከሆነ ኮድ = 3፣ በእኩል አራሽ የተያዘ ከሆነ ኮድ = 4 ፡ ለሌላ በእኩል አራሽ ከሆነ ኮድ = 5፣ ሌላ ከሆነ ኮድ 5 ይሞላል፡፡

## ሀ) የታረሰ መሬት ስፋትና የምርት መጠን (በመኸር ወቅት)

**ዓምድ 26 እና 27:- የመሬት ስፋት**

**ዓምድ 26:- የመሬት ስፋት መጠን**

ቤተሰቡ ያስመዘገበው እያንዳንዱ ሰብል/የመሬት አጠቃቀም የያዘው የስፋት መጠን ተጠይቆ በዚህ ዓምድ ይሞላል፡፡

**ዓምድ 27:- የስፋት መለኪያ ስም**

ቤተሰቡ በአምድ 26 ያስመዘገበውን መሬት የለካበት የስፋት መለኪያ በዚህ አምድ መዝግቦ ተስማሚውን ኮድ ከዚህ ክፍል መጨረሻ ከተሰጠው በመውሰድ ይሞላል፡፡

**ማስታወሻ:-**

በድብልቅ ሰብሎች በሚገጥሙበት ወቅት የፓስልን የማሣ ቁጥሮችን በመድገም በመፃፍ ከጠቅላላው የማሣ ስፋት ድርሻቸውን በማስላት ለእያንዳንዱ ሰብሎች የስፋት መጠኑን መረጃ ሰብሣቢው በማስገመት መሙላት ይኖርበታል፡፡ ቤተሰቡ ድርሻቸውን ማወቅ ካልቻለ የያዘው የመሬት ስፋት ለሰብሎቹ ተካፍሎ በአምድ 26 መጠኑ መስፈር አለበት፡፡

**ዓምድ 28 እና 29:- የተመረተው ምርት**

**ዓምድ 28:- የምርት መጠን**

ቤተሰቡ በመኸር ወቅት ያመረታቸውን ሰብሎች የምርት መጠን በመጠየቅ በዚህ ዓምድ ይሞላል፡፡ በሌላ በኩል ሌላ የመሬት አጠቃቀም፣ለሌላ ሰው ያከራየው እና በሰብል ያልተያዙ መሬቶች የምርት መጠን ስለሌላቸው በሰረዝ በዚህ ዓምድ መታለፍ አለበት፡፡

**ዓምድ 29:- የምርት መጠን መለኪያ**

ቤተሰቡ በአምድ 28 ላይ ያመረታቸውን ሰብሎች ምርት መጠን ለመለካት የተጠቀመባቸው የመጠን መለኪያዎች በዚህ ዓምድ ይሰፍራሉ:: ተስማሚውን ኮድ ከዚህ ክፍል መጨረሻ ከተሰጠው በመውሰድ ይሞላል::

**የተለያዩ የግብርና ግባአቶች (በመኸር ወቅት)**

**ዓምድ 30:- ፀረ- ተባይ መድሀኒት ከተጠቀሙ ዓይነቱ**

ቤተሰቡ በአምድ 24 ላይ ያስመዘገባቸው ሰብሎችን ለማምረት ሲል መድሀኒት ተጠቅሞ እንደሆነ ጠይቆ ከተጠቀመ በዚህ ዓምድ ዓይነቱ ተጠቅሶ ተስማሚው ኮድ ከዚህ ክፍል መጨረሻ ከተሰጠው በመውሰድ ይሞላል::

**ዓምድ 31:- የሰው ሀይል አጠቃቀም እንዴት ነበር?**

ቤተሰቡ በአምድ 24 ላይ ሰብሎችን ለማምረት የሰው ሀይል አጠቃቀሙ ቅጥር ከሆነ ኮድ«1» ደቦ/ወንፈል ከሆነ ኮድ «2» ሁለቱም ከሆነ ኮድ «3» ከተጠቀሱት ውጭ ከሆነ ደግሞ ኮድ «4» በመጥቀስ በዚህ ዓምድ ይሞላል::

**ዓምድ 32:- ምርጥ ዘር ተጠቅመዋል (አዎ =1 የለም = 2)**

ቤተሰቡ በአምድ 24 ላይ ለተጠቀሱት ሰብሎች ምርጥ ዘር መጠቀሙ አለመጠቀሙ ተጠይቆ አዎ ከሆነ በዚህ ዓምድ በመፃፍ ለኮድ በተሰጠው ቦታ ኮድ «1» ይሞላል:: ካልተጠቀመ የለም ተብሎ በአምዱ ኮድ «2» ይሞላል::

**ዓምድ 33፣34 እና 35 :- ዳኘ ማዳበሪያ ከተጠቀሙ**

**ዓምድ 33:- መጠን**

ቤተሰቡ እያንዳንዱ ማሣዎች ላይ በመኸር ወቅት ሰብል ለማምረት ዳኘ ማዳበሪያ ተጠቅሞ ከሆነ መጠኑ በዚህ ዓምድ ይሞላል::

**ዓምድ 34:- መለከያ**

ቤተሰቡ በአምድ 33 መጠኑን ለመግለፅ የተጠቀመበትን መለኪያ ስም በመጥቀስ ተስማሚውን ኮድ ከዚህ ክፍል መጨረሻ በመውሰድ በዚህ ዓምድ ይሞላል::

**ዓምድ 35:- ዋጋ**

ቤተሰቡ እያንዳንዱን ሰብል ለማምረት የተጠቀመበት የዳኘ ማዳበሪያ ጠቅላላ ዋጋ ተጠይቆ በዚህ ዓምድ ይሞላል:: በዚህ አምድ ቤተሰቡ የገዛውን ሣይሆን ለእያንዳንዱ ማሣ የተጠቀመውን ማዳበሪያ መጠን መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል::

ዓምድ 36፣37 እና 38:- ዩሪያ ማዳበሪያ ከተጠቀሙ

ዓምድ 36:-መጠን

ቤተሰቡ እያንዳንዱ ማሣዎች ላይ ሰብል ለማምረት የዩሪያ ማዳበሪያ ከተጠቀመ መጠኑ በዚህ አምድ ይሞላል::

ዓምድ 37:- መለኪያ

ቤተሰቡ በአምድ 36 መጠኑን ለመግለፅ የተጠቀመበትን መለኪያ ስም በመጥቀስ ተስማሚውን ኮድ ከዚህ ክፍል መጨረሻ በመውሰድ በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 38:- ዋጋ

ቤተሰቡ እያንዳንዱ ማሳ ላይ ያለውን ሰብል ለማምረት የተጠቀመበትን የዩሪያ ማዳበሪያ ዋጋ በመኸር ወቅት ተጠይቆ በዚህ ዓምድ ይሞላል:: በዚህ አምድ ቤተሰቡ የገዛውን ሣይሆን ለእያንዳንዱ ማሣ የተጠቀመውን ማዳበሪያ መጠን መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል::

ዓምድ 39 እና 40 የመስኖ ዘዴ ከተጠቀሙ

ዓምድ 39:- የመስኖ አይነት

ቤተሰቡ በአምድ 24 ላይ ያለውን ሰብል ለማምረት መስኖ ከተጠቀመ የመስኖ አይነቱ ተገልፆ ተስማሚውን ኮድ ከዚህ ክፍል መጨረሻ በመውሰድ በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 40:- መጠቀም ከጀመሩ ስንት አመት ሆነ

ቤተሰቡ በመኸር ወቅት ለተከታታይ አመት መስኖ የሚጠቀም ከሆነ እያንዳንዱን ማሣ አስመልክቶ ስንት አመት እንደተጠቀመ ተጠይቆ በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ለ- በልግ ወቅት ሰብሎች (1999)

ዓምድ 41:- የፓርስል ቁጥር

በዚህ ዓምድ ቤተሰቡ በ1999 በልግ ወቅት ለሚያመርታቸው ጊዜያዊ ሰብሎች ያሉባቸው ፓርስሎች በዚህ ዓምድ ይሞላል:: በቤተሰቡ አዲስ ፓርስል የፈጠረ ከሆነ ከአምድ 21 ጋር በተገናዘበ መልኩ ለተፈጠረው ፓርስል ከመጨረሻ ቀጣይ ቁጥር በመስጠት የፓርስልና የማሣ ቁጥር ይሞላል::

ዓምድ 42:- የማሣ ቁጥር

በዚህ ዓምድ ቤተሰቡ በበልግ ወቅት ለሚያመርታቸው ሰብሎች በአዲስ መልክ የማሣ ቁጥር በመስጠት ወደዚህ አምድ ያስተላልፋል:: በዚህ ዓምድ የግጦሽ

የእዳሪ መሬት ወዘተ ማሣዎች በመኸር ወቅት የሚካተቱ ሲሆን ወደዚህ አይመጡም:: በዚህ አምድ በበልግ ወቅት ያከራያቸውን እንዲሁም የተከራየውንና ሰብል ምርት የተመረተባቸውን ማሳዎች የማሣ ቁጥር በመስጠት በዚህ አምድ ይሞላሉ::

**ዓምድ 43:- የመሬት አጠቃቀም አይነት**

በዚህ አምድ በአምድ 42 ላይ የማሣ ቁጥር የተሰጣቸው ማሳዎች ላይ ያለው የመሬት አጠቃቀም ዓይነት (በአንድ ዓይነት ወይም በድብልቅ ሰብል የተያዘ በማለት ) ይሞላል::

**ዓምድ 44:- የሰብል/የመሬት አጠቃቀም ስም**

ቤተሰቡ በበልግ ወቅት በሰብል የተያዘ መሬት የሰብል ስም ወይም ለሰው ያከራየው መሬት አጠቃቀም ስም ተጠይቆ ስሙ በዚህ ዓምድ ሲሞላ ተስማሚውን ኮድ ከዚህ ክፍል መጨረሻ መውሰድ ይሞላል:: 35-38

**ዓምድ 45:- የይዞታው አይነት**

ቤተሰቡ በአምድ 44 ላይ የጠቀሰውን የመሬት አጠቃቀም ወይም ሰብል ያለበትን እያንዳንዱ መሬት አስመልክቶ በመጠየቅ በኪራይ ያልተሰጠ ከሆነ ኮድ = 1 ፡ በኪራይ የተያዘ ከሆነ ኮድ = 2፣ ለሌላ በኪራይ የተሰጠ ከሆነ ኮድ = 3፣ በእኩል አራሽ የተያዘ ከሆነ ኮድ = 4 ፡ ለሌላ በእኩል አራሽ ከሆነ ኮድ = 5፣ ሌላ ከሆነ ኮድ 5 ይሞላል::

## ለ) የታረሰ መሬት ስፋትና የምርት መጠን (በበልግ ወቅት)

**ዓምድ 46 እና 47:- የመሬት ስፋት**

**ዓምድ 46:- የስፋት መጠን**

በዓምድ 44 ላይ ያለውን የመሬት አጠቃቀም የስፋት መጠን በመጠየቅ በዚህ ዓምድ ይሞላል::

**ዓምድ 47:- የስፋት መለኪያ**

በአምድ 46 ላይ ያለውን የመሬት አጠቃቀም መጠን ለመግለፅ የተጠቀመበት የስፋት መለኪያ በዚህ አምድ ይሞላል:: ኮዱ ከዚህ ክፍል መጨረሻ ከተሰጠው በመውሰድ ይሞላል::

**ዓምድ 48 እና 49:- የተመረተው ምርት**

**ዓምድ 48:- የምርት መጠን**

ቤተሰቡ በዚህ ዓምድ በበልግ ወቅት ያመረታቸው የእያንዳንዱን ሰብል የምርት መጠን አስመልክቶ በመጠየቅ በዚህ አምድ ይሞላል::

**ዓምድ 49:- የምርት መጠን መለኪያ**

ቤተሰቡ በአምድ 48 ላይ የለካበትን የምርት መለኪያ ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል:: የመለኪያውን ኮድ ከዚህ ክፍል መጨረሻ ከተሰጠው በመውሰድ ይሞላል::

**የተለያዩ የግብርና ግባአቶች(በበልግ ወቅት)**

**ዓምድ 50:- መድሀኒት ከተጠቀሙ**

ቤተሰቡ በአምድ 44 ላይ የተጠቀሰውን የበልግ ሰብል ለማምረት መድሀኒት ተጠቅሞ ከሆነ በዚህ ዓምድ ተሞልቶ ተስማሚው ኮድ ከዚህ ክፍል መጨረሻ ከተሰጠው በመውሰድ ይሞላል::

**ዓምድ 51:- የሰው ኃይል አጠቃቀም እንዴት ነበር ?**

ቤተሰቡ በአምድ 44 ላይ ያሉትን ሰብሎች በበልግ ወቅት ለማምረት የተጠቀመው የሰው ሀይል ቅጥር ከሆነ ኮድ «1» ደቦ/ወንፈል ከሆነ ኮድ «2» ሁለቱም ከሆነ ደግሞ ኮድ «3» ከተጠቀሱት ውጭ ከሆነ ደግሞ ኮድ «4» በመጥቀስ በዚህ ዓምድ ይሞላል::

**ዓምድ 52:- ምርጥ ዘር ተጠቅመዋል? (አዎ =1 የለም =2)**

ቤተሰቡ በአምድ 44 ላይ የተጠቀሱትን ሰብሎች ለማምረት ምርጥ ዘር መጠቀሙ ተጠይቆ አዎ ከሆነ ኮድ «1» ካልተጠቀመ ደግሞ የለም ተብሎ ኮድ «2» በዚህ ዓምድ ይሞላል::

**ዓምድ 53፣ 54 55:- ዳኘ ማዳበሪያ ከተጠቀሙ**

**ዓምድ 53:- መጠን**

ቤተሰቡ በእያንዳንዱ ማሣዎች ላይ ዳኘ ማዳበሪያ ከተጠቀመ መጠኑ በዚህ አምድ ይሰፍራል::

**ዓምድ 54:- መለኪያ**

ቤተሰቡ በአምድ 53 ላይ መጠኑን ለመግለፅ የተጠቀመበትን መለኪያ ስም በመጥቀስ ተስማሚውን ኮድ ከዚህ ክፍል መጨረሻ ከተሰጠው በመውሰድ ይሞላል::

ዓምድ 55:- ዋጋ

ቤተሰቡ እያንዳንዱን ማሣ አስመልክቶ የተጠቀመው ማዳበሪያ ዋጋ በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 56፣ 57 እና 58:- ዩሪያ ማዳበሪያ ከተጠቀሙ

ዓምድ 56:- መጠን

ቤተሰቡ በእያንዳንዱ ማሣዎች ላይ ዩሪያ ማዳበሪያ ተጠቅሞ ከሆነ በዚህ ዓምድ መጠኑ ይሞላል::

ዓምድ 57:- የመጠን መለኪያ

ቤተሰቡ በአምድ 56 ላይ ያለውን መጠን ለመግለፅ የተጠቀመበት መለኪያ በዚህ ዓምድ ይፃፋል::

ዓምድ 58:- ዋጋ

ቤተሰቡ በእያንዳንዱ ማሣ አስመልክቶ የተጠቀመውን ዩሪያ የማዳበሪያ ዋጋ በዚህ አምድ ይሞላል::

ዓምድ 59 እና 60:- የመስኖ ዘዴ ከተጠቀሙ

ዓምድ 59:- የመስኖ ዓይነት

ቤተሰቡ በአምድ 44 ላይ ያለውን ሰብል ለማምረት መስኖ ከተጠቀሙ የመስኖ አይነቱ ተገልፆ ተስማሚው ኮድ ይሞላል::

ዓምድ 60:- መጠቀም ከጀመሩ ስንት ዓመት ሆነ?

ቤተሰቡ በበልግ ወቅት ለተከታታይ ዓመታት መስኖ የሚጠቀም ከሆነ እያንዳንዱ ማሣ ላይ መጠቀም ከጀመረ ስንት አመት እንደሆነው ጠይቆ በዚህ አምድ ይሞላል::

ሐ- በወቅት የማይገለጹ ሰብሎች (ቋሚ....) (2000)

ዓምድ 61:- የፓርስል ቁጥር

በወቅት የማይገለጹ ሰብሎችን (ለምሳሌ ቋሚ ሰብሎች) ለያዙ ፓርስሎች የፓርስል ቁጥር በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 62:- የማሣ ቁጥር

በወቅት የማይገለጹ ሰብሎችን ለያዙ ማሣዎች የማሣ ቁጥር በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 63:- የመሬት አጠቃቀም ዓይነት

በዓምድ 62 በተመዘገበው ማሳ ላይ ያለው ሰብል ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል:: ተስማሚው ኮድም ይሰጣል::

**ዓምድ 64:- የሰብል ስም**

በዚህ ዓምድ የሰብሉ ስም ይሞላል:: ተስማሚው ኮድም ይሰጣል::

**ዓምድ 65:- የይዞታ ዓይነት ስም**

ቤተሰቡ በአምድ 64 ላይ የጠቀሰውን የመሬት አጠቃቀም ወይም ሰብል ያለበትን እያንዳንዱ መሬት አስመልክቶ በመጠየቅ በኪራይ ያልተሰጠ ከሆነ ኮድ = 1 : በኪራይ የተያዘ ከሆነ ኮድ = 2፣ ለሌላ በኪራይ የተሰጠ ከሆነ ኮድ = 3፣ በእኩል አራሽ የተያዘ ከሆነ ኮድ = 4 : ለሌላ በእኩል አራሽ ከሆነ ኮድ = 5፣ ሌላ ከሆነ ኮድ 5 ይሞላል::

## የመሬት ስፋትና የምርት መጠን (በወቅት የማይገለጹ ሰብሎች)

**ዓምድ 66 እና 67:- የመሬት ስፋት**

**ዓምድ 66:- የስፋት መጠን**

በዚህ ዓምድ በዓምድ 64 ላይ የተጠቀሱ ሰብሎች የያዙት የስፋት መጠን በየአንጻራቸው ይሞላል::

**ዓምድ 67:- የስፋት መለኪያ**

ቤተሰቡ በዓምድ 66 ላይ የስፋት መጠኑን ለመግለፅ የተጠቀመበት የመለኪያ ስም በዚህ አምድ ይሞላል::ተስማሚው ኮድም ይሰጣል::

**ዓምድ 68 እና 69:- የተመረተ ምርት**

**ዓምድ 68:- የምርት መጠን**

በዚህ ዓምድ ቤተሰቡ በዓመቱ ውስጥ ያመረተውን ምርት መጠን በመጠየቅ ይሞላል::

**ዓምድ 69:- የምርት መለኪያ**

ቤተሰቡ በአምድ 68 መጠኑን ለመለካት የተጠቀመበት የአካባቢ መለኪያ ከነኮዱ በዚህ ዓምድ ይሞላል::

## የተለያዩ የግብርና ግባአቶች (በወቅት የማይገለፁ ሰብሎች)

**ዓምድ 70:- መድሀኒት (የፋብሪካ ውጤት) ተጠቅመዋል?**

ቤተሰቡ በማሳው ላይ ፀረ ተባይ መድሀኒት (የፋብሪካ) ውጤት ተጠቅሞ ከሆነ በዚህ አምድ አይነቱ ይፃፍና ኮዱ ይሞላል::

**ዓምድ 71:- የሰው ሀይል አጠቃቀም እንዴት ነበር?**

ቤተሰቡ ሰብሎቹን ለማምረት የተጠቀመው የሰው ሀይል ቅጥር ከሆነ ኮድ «1» ደቦ/ወንፈል ከሆነ ኮድ «2» ሁለቱም ከሆነ ደግሞ ኮድ «3» ከተጠቀሱት ውጭ ከሆነ ደግሞ «4» በዚህ አምድ ይሞላል::

**ዓምድ 72:- ምርጥ ዘር ተጠቅመዋል? (አዎ=1 የለም = 2)**

ቤተሰቡ በአምድ 64 ላይ የተጠቀሱትን ሰብሎች ለማምረት ምርጥ ዘር ተጠቅሞ ከሆነ ኮድ «1» ካልተጠቀመ ደግሞ ኮድ «2» በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል::

**ዓምድ 73፣74 እና 75:- ዳኘ ማዳበሪያ ከተጠቀሙ**

**ዓምድ 73:- መጠን**

ቤተሰቡ በእያንዳንዱ ማሣዎች ላይ ማዳበሪያ ከተጠቀሙ መጠኑ በዚህ አምድ ይሞላል::

**ዓምድ 74:- መለኪያ**

ቤተሰቡ በአምድ 73 ላይ የገለፀውን መጠን ለሚለካበት የተጠቀመበት መለኪያ ስም በዚህ አምድ ይሞላል:: ተስማሚው ኮድም ይሰጣል::

**ዓምድ 75:- ዋጋ**

ቤተሰቡ በእያንዳንዱ ማሣ ላይ የተጠቀመውን የማዳበሪያ ዋጋ በመጠየቅ በዚህ አምድ ይሞላል::

**ዓምድ 76፣77 እና 78:- ዩሪያ ማዳበሪያ ከተጠቀሙ**

**ዓምድ 76:- መጠን**

ቤተሰቡ በእያንዳንዱ ማሣዎች ላይ ዩሪያ ማዳበሪያ የተጠቀመ ከሆነ በዚህ ዓምድ መጠኑ ይሞላል::

**ዓምድ 77:- የመጠን መለኪያ**

ቤተሰቡ በአምድ 76 ላይ መጠን የተለካበትን መለኪያ ስም በዚህ አምድ በመግለፅ ተስማሚው ኮድ ይሰጣል::

**ዓምድ 78:- ዋጋ**

ቤተሰቡ እያንዳንዱን ማሣ አስመልክቶ ዩሪያ ማዳበሪያ ከተጠቀመ በዚህ ዓምድ ዋጋውን በመጠየቅ ይሞላል::

**ዓምድ 79 እና 80:- መስኖ ከተጠቀሙ**

**ዓምድ 79:- የመስኖ አይነት**

ቤተሰቡ በአምድ 64 ላይ ያለውን ሰብል ለማምረት መስኖ ከተጠቀመ የመስኖ አይነቱ ተገልፆ ተስማሚው ኮድ ይሞላል።

**ዓምድ 80:- መጠቀም ከጀመሩ ስንት አመት ነው?**

ቤተሰቡ በማሳው ላይ መስኖ መጠቀም ከጀመረ ስንት አመት እንደሆነው በመጠየቅ በዚህ አምድ ይሞላል።

## ክፍል 4ሀ- የሰብል ምርት ክምችትና ፍጆታ (ከሰኔ 1/99- ግንቦት 30/2000)

**ዓምድ 81- የሰብል ስም**

ቤተሰቡ በጥናቱ ዘመን ያከማቸው ሰብል ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል። ተስማሚው ኮድ በኮድ መፃፍያው ቦታ ይሰፍራል።

**ዓምድ 82 በሰኔ ወር/99 ዓ.ም. መጨረሻ ምን ያህል ክምችት ነበረዎት?**

ቤተሰቡ በአምድ 81 የተገለፀው ሰብል በሰኔ ወር /99 ዓ.ም. መጨረሻ ምን ያህል ክምችት እንደነበረው ተጠይቆ መጠኑ በተሰጠው ቦታ ይሞላል። የመጠን መለኪያ ስምና ኮድ በተገቢው ቦታ ይሰፍራል።

**ዓምድ 83- የ2000 ዓ.ም. መኸር ወቅት ከመሰብሰቡ በፊት የክምችትዎ መጠን ምን ያህል ነበር?**

ቤተሰቡ የ2000 ዓ.ም. መኸር ወቅት ከመሰብሰቡ በፊት ምን ያህል ክምችት እንደነበረው ተጠይቆ መጠኑ በተሰጠው ቦታ ይሞላል የመጠን መለኪያ ስምና ኮድ በዚህ ዓምድ በተገቢው ቦታ ይሞላል።

**ዓምድ 84- በአምድ 81 የተጠቀሰውን ሰብል ከሁለት ዓመት በፊት አምርተዋል? ( አዎ =1 አላመረትኩም = 2)**

ቤተሰቡ በዓምድ 81 የተጠቀሰውን ሰብል ከሁለት አመት በፊት አምርቶ ከሆነ አዎ ተብሎ ኮዱ «1» ይሞላል ካላመረተ ደግሞ አላመረትኩም ተብሎ ኮድ «2» ይሞላል።

## ክፍል 4ለ- የሰብል ምርት ሽያጭ (ከሰኔ 1/99 እስከ ግንቦት 30/2000)

**ዓምድ 85- የሰብል ስም**

ቤተሰቡ በተጠቀሰው ዓመት ለሽያጭ ያቀረባቸው ሰብሎች ካሉ ስማቸው በዚህ ዓምድ ይሞላል። ኮዳቸውም ከሰብል ኮድ ተመርጦ በኮድ መፃፊያው ቦታ ይሰፍራል።

**ዓምድ 86- የተሸጠበት ወር**

ቤተሰቡ በዓምድ 85 ላይ የተገለፀውን ሰብል የተሸጠበት ወር በአምዱ ይሰፍርና የወሩ ኮድ በኮድ መስጫው ቦታ ይሰፍራል።

**ዓምድ 87- የተሸጠ ምርት መጠንና መለኪያ**

በዚህ ዓምድ በዓምድ 85 የተሸጠው ሰብል የምርት መጠንና የመጠን መለኪያው ስም ከነኮዱ ይሰፍራል።

**ዓምድ 88- የአንዱ መለኪያ ዋጋ**

በዓምድ 87 የተጠቀሰው የአንዱ ምርት መጠን መለኪያ ዋጋ ምን ያህል እንደሆነ ተጠይቆ በብርና በሣንቲም በተገቢው ቦታ ይሰፍራል።

## ክፍል 4ሐ- የምርት መጠን መለወጫ

**ዓምድ 89ሀ ና 89ለ- የሰብል ሥም :የአካባቢ ምርት መጠን መለኪያ እና ኮድ**

በዚህ ዓምድ ለሰብል ምርት መለኪያነት የሚጠቀሙበትን የአካባቢ ምርት መለኪያ ስምና ኮድ በዚህ ዓምድ በተገቢው ቦታ ይሞላል።

**ዓምድ 89ሀ-የሰብል ሥምና ኮድ**

በተለያዩ ወቅቶች የተመረቱና በክምችት የተያዙ የሰብል ሥምና ኮድ በዚህ አምድ ይሞላል።

**ዓምድ 89ለ ና 90 የምርት መጠን መለወጫ**

**ዓምድ 89ለ** ለምርት መጠን መለወጫ የተጠቀምንበት የአከባቢ መለኪያ ስምና ኮድ በዚህ አምድ ይሞላል።

**ዓምድ 90- በዓምድ 89ለ የተጠቀሰው አንዱ መለኪያ ስንት ኪ.ግ. ይሆናል?**

በዓምድ 89ለ የተጠቀሰው አንዱ የአካባቢ መለኪያ ስንት ኪ.ግ. እንደሆነ በመለካት መጠኑ በዚህ ዓምድ ይሞላል።

## ክፍል 4መ- ሌሎች የሰብል ክምችት ተዛማች ጥያቄዎች

**ዓምድ 91- ካለፈው ዓመት መኸር (1999) የተሸጋገረ የሰብል ምርት አሁንም አለዎት ?**

ቤተሰቡ ካለፈው አመት መኸር (1999 ዓ.ም.) የተሸጋገረ የሰብል ምርት አሁንም ካለው ኮድ «1» ከሌለው ደግሞ ኮድ «2» በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል።

**ዓምድ 92**

ካለፈው ዓመት መኸር (1999) የተሸጋገረ የሰብል ምርት ካልነበረ የነበረውን ምርት በመቼ ወር እንደጨረሱት ወሩ ተጠቅሶ ተስማሚው ኮድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል::

**ዓምድ 93-**

የተሸጋገረው የሰብል ምርት ቤተሰቡ ካለው (በአምድ 91 ኮድ 1 ከተሞላ) ያለው ምርት በምን ያህል ወር እንደሚበቃ ቤተሰቡ ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል::

**ዓምድ 94-**

ቤተሰቡ ከሰኔ 1/1999 ዓ.ም. እስከ አሁን ባለው ጊዜ ውስጥ ለዘር የሚሆነውን ሰብል ለምግብነት መጠቀም አለመጠቀሙ ተጠይቆ ከተጠቀመ አዎ ተብሎ ኮድ «1» ካልተጠቀመ ኮድ «2» በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል::

**ዓምድ 95-**

ቤተሰቡ አብዛኛውን ጊዜ ያመረተውን ሰብል የት ወስዶ እንደሚሸጠው ተጠይቆ እዚሁ ቀበሌ ከሆነ ኮድ «1»፣ሌላ ቀበሌ ከሆነ ደግሞ ኮድ «2» በአካባቢ በሚገኝ የከተማ ገበያ ከሆነ ኮድ «3» በክልሉ ማዕከል ከሆነ ኮድ «4» አዲስ አበባ ከሆነ ኮድ «5» ከነዚህ ውጭ ሌላ ቦታ ከሆነ ኮድ «6» በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል::

## ክፍል 5- ቤተሰቡ በግብርና ምርት ወቅት የነበረው የስራ ስምሪት ሁኔታ (ከ15 አመትና በላይ)

**ዓምድ 96-**

15 ዓመትና በላይ የሆኑ የቤተሰብ አባላት መለያ ቁጥር ከቅፅ 2000/2 ዓምድ 8 ወደዚህ ይወራረሳል::

**ዓምድ 97-108**

እያንዳንዱ 15 አመትና በላይ የሆነው የቤተሰብ አባል ባለፉት 12 ወራት በቤተሰቡ ይዞታ ላይ ስራ እንደሰራ ተጠይቆ በሠራው ወር ትይዩ ኮድ «1» ካልሰራ ደግሞ በወሩ ትይዩ ኮድ «2» ይሞላል::

# ለቅጽ ም.ዋ.2000/3 የሚያገለግል የኮድ ዝርዝር

## ሀ የስፋት መለኪያ ኮድ (ለአምድ 11፣ 19፣ 27፣ 47፣ 67 )

1. ጋሻ
2. ሄክታር
3. ገመድ
4. ጥማድ
5. ቀርጥ
6. ማሣ
7. ቀዳማ
8. ቁፋሮ
9. ዝህር
10. ጥንቶ
11. እርምጃ
12. ዳሮ
13. ገዝም
14. ክንድ/ሉንት
15. ካሬ ዝህር
16. መዳብ
17. ካሬ ሜትር
18. ቦይ/ሰይጪ
19. ሰው የሚያውለው
20. እቃ በሬ
21. ቃምዲ
22. ትልም
23. ከተራ
24. እመም
25. እገታ
26. ሳህን/ሰዝር
27. ፊጋ
28. ሰአት
29. የሰው ቀን
30. ቃዳ
31. ቆቲ
32. አየ
33. ጫማ
34. ዱላ
35. ደቂቃ
36. ዶማ
37. ዲትኩል
38. ቀበኖ
39. መሽብን
40. መስመር
41. ሌላ ይገለጽ

## ለ. መሬቱ በምን ሁኔታ ተያዘ/ተገኘ ኮድ (በዓምድ 17)

1. በሽግሽግ
2. በአዋጅ የተከፋፈለ
3. መሬት ሳራሹ
4. ሰፈራ
5. በግዥ
6. በውርስ
7. በኪራይ
8. በእኩል አራሽ
9. መንደር ምስረታ
10. ሌላ (ይገለጽ)

## ሐ. በይዞታው ላይ ግንባታ ከተካሔደ (ለዓምድ 18/ኮድ

1. የመስኖ ጉድጓድ
2. የመስኖ ቦይ
3. የግል ኩሬ
4. መሬት ማስተካከል
5. ድንጋይ ጠረጋ
6. የድንጋይ እርከን
7. የአፈር ካብ
8. የግድብ መከላከያ
9. የውሀ መውረጃ ቦይ
10. ቀጭን የውሀ መውረጃ
11. ዛፍ ተክል
12. ሳር መትከል
13. መከላከያ አጥሮች
14. አጥር ማጠር
15. ውሀ ማቆር
16. ሌላ (ይገለጽ)

## መ. የመሬት አጠቃቀም አይነት ኮድ (ለአምድ 23፣43፣63)

1. በቤት የተያዘ
2. በአንድ አይነት ሰብል የተያዘ
3. በድብልቅ ሰብል የተያዘ
4. ግጦሽ
5. ጉቶ
6. ጥቅም ላይ ያልዋለ

## ሠ. የሰብል ስምና ኮድ (ለዓምድ 24፣44፣64፣81፣85)

1. ጤፍ
2. ገብስ
3. ስንዴ
4. በቆሎ
5. ማሽላ
6. ዘንጋዳ
7. አጃ
8. ባቄላ
9. ተልባ
10. ለውዝ
11. ሰሊጥ
12. ቁንዶ በርበሬ
13. ምስር
14. ቡና
15. ጫት
16. እንሰት
17. ሙዝ
18. ሣር
19. ጌሾ
20. ባህርዛፍ
21. ሽፈራው/ሃለኮ
22. ዳጉሣ
23. ሱፍ
24. ድንች
25. ሽንኩራ አገዳ
26. ትምባሆ
27. አናናስ
28. አቮካዶ
29. ቀይ ሽንኩርት
30. ቆስጣ
31. ነጭ ሽንኩርት
32. ካሣቫ
33. ፍሰሊያ
34. ማንጎ
35. ሽምብራ
36. አተር (ለከብቶች የሚሰጥ)
37. ብርቱኳን
38. ጐደሬ
39. አደንጓሬ
40. ስኳርድንች
41. ቲማቲም
42. ጓያ
43. ኑግ
44. ጐመን
45. ሩዝ
46. ሲናር/ገሪማ
47. በሎቄ
48. አተር
49. አብሽ
50. ቀይ ስር
51. ካሮት
52. ዝንጅብል
53. ሰላጣ
54. ጥቅል ጐመን
55. ዱባ
56. ቃሪያ
57. የከብቶች መኖ
58. ፓፓያ
59. የደን ውጤቶች (እጣን፣ቀጠላ ቅጠል ወዘተ.)
60. ሌሎች (ይገለጽ)

## ረ. የፀረ-ተባይ መድሀኒት አይነትና ኮድ (ለአምድ 30፣50፣70)

1. አልተጠቀመም
2. ፀረ-ተባይ
3. ፀረ-አዝእርት
4. ፀረ-በሽታ
5. 2 እና 3
6. 2 እና 4

7. 3 እና 4
8. ሁሉም።

ሰ. <u>የመስኖ አይነትና ኮድ (ለአምድ 39፣59፣79)</u>

1. አልተጠቀመም
2. አነስተኛ ግድብ
3. ውሀ በቦይ መጥለፍ
4. ከኩሬ
5. ውሀ ማቆር
6. ከጉድጓድ
7. ወራጅ ውሀ
8. ሌላ (ይገለጽ)

ሸ. <u>የመጠን መለኪያ እና ኮድ (ለአምድ 29፣49፣69)</u>

1. ኪሎ ግራም
2. ኩንታል
3. ጭነት
4. ዳውላ
5. ቁና
6. መደብ
7. ቁርበት
8. ስልቻ
9. አቁማዳ
10. እስር
11. ቦቦ
12. እሽግ
13. ኮሮጆ
14.
15. ቁርጥራጭ
16.
17. ሣጥን
18. ቅጠል
19. ሊትር
20. ቅል
21. ጋን
22. እንስራ
23. ጉርዝኝ
24. ጣሣ
25. ኩባያ
26. ብርጭቆ
27. ሲኒ
28. ገምቦ
29. ጠርሙስ
30. ብር
40. ትልቅ ማዳበሪያ
41. ትንሽ ማዳበሪያ
42. ሣህን/ሎተሪ
43. ማንቆርቆሪያ
44. ፌስታል
45. ዙርባ
46. አቃራ
47. ሚካ
48. ቅርጫት/ቁምባ
49.ዘለላ
50. መለኪያ
51. ጉችዬ
52. በኮሌ
53. እንቅብ
54.ሽክም
55. ቁጥር
56. ጉተራ
57. ለምባ
58. ሽሪምሪ
59. እግር
60. ወስላ
61. መስፈሪያ
62. ኩርፎ
63. ከለላ
64. ኬሻ
65. ጭሬት
66. ሞሻ
67. ታኒካ
68. አበት
69. ሳዳን
70.መስበሽ
71.ትርሽዋ
72.ቢኬሪ
73.ቁምጣ
74. ከፈር
75. ነፍቂ/ንፍቅ
76. ኮልኮሌ
77. ዳሮታ
78. ገበቴ
79. ሞሼ
80. ሌላ (ይገለጽ)

## ቀ. ለቅጽ ም.ዋ. 2000/3 የሚያገለግል የኮድ ዝርዝር

### የወራት ስምና ኮድ (ለአምድ 83፣86)

| | |
|---|---|
| 1. መስከረም | 7. መጋቢት |
| 2. ጥቅምት | 8. ሚያዝያ |
| 3. ህዳር | 9. ግንቦት |
| 4. ታህሣሥ | 10. ሰኔ |
| 5. ጥር | 11. ሐምሌ |
| 6. የካቲት | 12. ነሐሴ |
| | 13. ጳጉሜ |

# የቅጽ ምዋ 2000/4 የማምረቻ መሣሪያዎችና
# የቤት ቁሳቁስ መመዝገቢያ አሞላል

**ክፍል 1 :- የአካባቢ መለያ**

**ዓምድ 1 - ዓምድ 4.**

ጥናቱ የሚካሄድበት ቆጠራ ቦታ የሚገኝበት ክልል፣ዞን ፣ወረዳና ገ/ማህበር በቅደም ተከተል በተሰጠው ቦታ ይሞላል።

**ዓምድ 5.**

ጥናቱ የሚካሄድበት ቆጠራ ቦታ ቁጥር በተሰጠው ቦታ ይሞላል።

**ዓምድ 6. የቤተሰብ መለያ ቁጥር**

ለጥናቱ የተመረጠው ቤተሰብ መለያ ቁጥር ከቅጽ ምዋ 98/1 ክፍል 2 ዓምድ 6 በመውሰድ ይሞላል።

**ዓምድ 7.**

ለጥናቱ የተመረጠው ቤተሰብ ኃላፊ ስም በተሰጠው ቦታ ይመዘገባል።

**ክፍል 2:- የማምረቻ መሣሪያዎች ብዛትና ዋጋ በዓይነት**

**ዓምድ 8.**

በዚህ ዓምድ ተራ ቁጥር በቅደም ተከተል ተሰጥቷል።

**ዓምድ 9.**

የመሣሪያ ዓይነት በዝርዝር ተሰጥቷል።

**ዓምድ 10.**

ኮድ ተሰጥቷል።

**ዓምድ 11.**

በጥናቱ ቀን ማለትም ሰኔ 1/2000 የነበራቸው ብዛት በየዓይነቱ እየተጠየቀ በዚህ ዓምድ ይሞላል።

**ዓምድ 12.**

እያንዳንዱ መሣሪያ አሁን ባበለት ሁኔታ ዋጋው (ምን ያህል እንደሚያወጣ) እየተጠየቀ በዓምድ 11 የተመዘገቡት ጠቅላላ መሣሪያዎች ዋጋ በየዓይነታቸው ተሰልቶ በዚህ ዓምድ ይመዘገባል።

**ክፍል 3:- አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉ የቤት ቁሳቁሶች ብዛት በዓይነት**

**ዓምድ 13,**

ተራ ቁጥር በቅደም ተሰጥቷል::

**ዓምድ 14**

የቁሳቁስ ዓይነት በዝርዝር ተሰጥቷል::

**ዓምድ 15,**

ኮድ ለእያንዳንዱ ቁሳቁስ ተሰጥቷል::

**ዓምድ 16**

በጥናቱ ቀን ሰኔ 1/2000 ዓ.ም. ቤተሰቡ የነበረው ጠቅላላ የቤት የቁሳቁስ ብዛት ዓይነት በመጠየቅ በየአንፃሩ ይመዘገባል::

**ክፍል 4:- የመኖሪያ ቤት አሠራር ሁኔታ**

**ጥያቄ 17 . የዋናው መኖሪያ ቤት ጣራ የተሠራው ከምንድን ነው?**

የቤተሰቡ የዋናው መኖሪያ ቤት ጣራ የተሠራው ከምን እንደሆነ ተጠይቆ ከሣር ከሆነ ኮድ «1» ከቆርቆሮ ከሆነ ኮድ «2» ከጭቃ ከአሸዋ ከድንጋይና ከመሳሰሉት ከሆነ ኮድ «3» ከኘላስቲክ ከሆነ ደግሞ ኮድ «4» በተሰጠው ሣጥን ውስጥ ይሞላል::

**ጥያቄ 18 . የዋናው መኖርያ ቤት ወለል ምንድን ነው?**

የቤተሰቡ የዋናው መኖርያ ቤት ወለል የተሰራው ከምን እንደሆነ ተጠይቆ ከአፈር ከሆነ ኮድ «1» በእበት የተለቀለቀ ከሆነ ኮድ «2» ሊሾ/አርማታ/ድንጋይ ከሆነ ኮድ «3» ጡብ/ሸክላ ከሆነ ኮድ «4» በተሰጠው ሣጥን ይሞላ::

**ጥያቄ 19 . ባለፉት ሁለት ዓመታት አዲስ ቤት ለመስራት ወጪ አውጥተው ነበር?**

ቤተሰቡ ቤት/አጥር ለማሳደስ ወጪ ያወጣባቸው ዕቃዎች ማለትም የቤት ቀለም፣ አሸዋ፣ ሲሚንቶ፣ ጣውላ፣ ማዕዘንና ሚስማር፣ የቤት ክዳን ቆርቆሮ፣ ማጠፊያ፣ አጠና፣ ኮምፔሳቶ፣ ቺፕ ውድ፣ መስኮት፣ መዝጊያ፣ ድንጋይ፣ ቁልፍ፣ ኖራ፣ ለመሳሰሉት ዕቃዎች ያወጣባቸው ወጪ በዚህ አርእስት በኮድ 362 ስር ይጠቃለላል:: ሆኖም ለጥገናና ዕድሳት አገልግሎት የተደረገ ክፍያ በዚህ ክፍል ኮድ 452 ይመዘገባል::

እንዲሁም አዲስ ቤት ለመስራት ከላይ የተዘረዘሩት የህንፃ መሳሪያዎች ያወጣው ጠቅላላ ዋጋ በኮድ 363 ሲመዘገብ ለሠራተኛ ያወጣው (የጉልበት ሰራተኛ) ወጪ በኮድ 452 ይመዘገባል::

VII. ለዘመናዊ የህክምና አገልግሎትና መድሃኒቶች ኮድ 381

በዚህ አርእስት ስር ቤተሰቡ በመንግሥትና በግል የህክምና ተቋማት ለሐኪም መታያ፣ ለራጅ ክፍያ፣ የአልጋ ወጪ፣ ለኤድስ ምርመራ፣ የላቦራቶር ክፍያና ለመድሃኒቶችና ለመሳሰሉት ያወጣው ወጪ በዚህ ይካተታል::

VIII. ለባህል አካሚና መድሃኒቶች ኮድ 382

ከላይ ከተራ ቁጥር VII ውጪ ለተጠቀሱት ማለትም ለልምድ አዋላጅና ለባህላዊ ሃኪም (ወጌሻን ጨምሮ) የተከፈለና ለባህላዊ መድሃኒቶች ያወጣው ወጪ በዚህ አርዕስት ስር ይጠቃለላል::

IX. የትምህርት ቤት ክፍያ ኮድ 401

በዚህ አርእስት ስር ለመንግስት፣ ለህዝብ፣ ለግል፣ ለሚሲዮን፣ ለአዳሪና ለአገር ውስጥና ለውጭ ሀገር የተልዕኮ ትምህርት የወጡ ወጪዎች በዚህ ይካተታሉ:: ሆኖም ለፅህፈት መሳሪያዎች፣ የትምህርት መፃህፍትና ዩኒፎርም.... ወ.ዘ.ተ. የወጡ ወጪዎች በኮድ 402 ስለሚካተቱ በዚህ ኮድ አይካተትም::

X. ለግል ንፅህና ኮድ 453

በዚህ አርእስት ቤተሰቡ ለፀጉር ቅባት፣ ለፀጉር ቅቤ፣ ለሽቶ፣ ለፀጉር መስሪያና ለመሳሰሉት ያወጣው ወጪ ይመዘገባል::

## ሌሎች ቋሚና ከፊል ቋሚ ዕቃዎች/አገልግሎቶች

በዚህ አርእስት ስር ቤተሰቡ ባለፈው ዓመት ውስጥ ለቋሚና ከፊል ቋሚ ዕቃ/አገልግሎት የሚያደርጋቸው ወጪዎች መረጃ ለማግኘት በሚያስችል መልኩ የተዘጋጁ ስለሆነ በተሰጠው ኮድ መሠረት የወጪ መረጃዎች ይሰበሰባሉ::

**ለጥገናና ዕድሳት አገልግሎት/ከመኖሪያ ቤት ሌላ /ኮድ 454/**

ቤተሰቡ ባለፉት 12 ወራት ለልብስ ማስፊያ፣ ለጫማ ማስፊያ/ ማስጠገኛ ለቤት ዕቃዎች ማስጠገኛ ለመሳሰሉት ያወጣው ወጪ ካለ ጠቅላላ ወጪው በዚህ አርዕስት ስር ይመዘገባል።

**ለመገናኛ ኮድ 364**

ቤተሰቡ ባለፉት 12 ወራት ለመገናኛ ያወጣቸው ወጪዎች ማለትም ለስልክ መደወያ፣ ለፖስታ መላኪያ፣ የከፈላቸው ወጪዎች በዚህ አርዕስት ስር ይካተታሉ።

**ሌሎች ወጪዎች ኮድ 466**

በዚህ አርዕስት ስር የሚካተቱት ቤተሰቡ ሌሎች ያወጣቸው ወጪዎች የሚመዘገብበት ነው።

**ዓምድ 8:- ተራ ቁጥር በዚህ ዓምድ ለእያንዳንዱ ዕቃና አገልግሎት ተራ ቁጥር አስቀድሞ ተሞልቷል።**

**ዓምድ 9:- የዕቃው/አገልግሎት ዓይነት**

በዚህ ዓምድ ስር የዕቃ/አገልግሎት ዓይነቶች ተዘርዝሯል። ስለሆነም በዓምድ 11 የሚሰበሰበው መረጃ በዓምድ 9 ለተዘረዘሩት የዕቃዎቸ ወይም አገልግሎቶች ዓይነት ነው። ቤተሰቡ በዚህ ክፍል ከተመዘገቡት ዕቃዎች ውጪ የገዛ ከሆነ የዕቃውን አጠቃላይ ዋጋ ሌሎች በሚለው ኮድ 466 በተገቢው ቦታ በመለየት ይመዘገባል።

**ዓምድ 10 የዕቃው/የአገልግሎት ኮድ** በዚህ ዓምድ ስር የዕቃ/አገልግሎት ኮድ አስቀድሞ ተሞልቷል።

**ዓምድ 11:-** ባለፉት 12 ወራት (ከሰኔ 1/1999 - ግንቦት 30/2000 ዓ.ም.) ቤተሰቡ/የቤተሰቡ ኣባላት በዓምድ 9 ለተሞላው የዕቃ/አገልግሎት ያወጣው ወጪ ካለ ያወጣው ወጪ እያንዳንዱ አባል ተጠይቆ ጠቅላላ የቤተሰቡ ወጪ በዚህ ዓምድ ይሞላል።

**ዓምድ 12** :- ቤተሰቡ/የቤተሰቡ አባላት በስጦታ፣ በነፃ፣ በእርዳታ፣ ወ.ዘ.ተ. ያገኘው ዕቃ/አገልግሎት በመጠየቅ አጠቃላይ ዋጋው በወቅቱ የገበያ ዋጋ ቤተሰቡን በማስገመት ይሞላል። ቤተሰቡ ዋጋውን ካላወቀ በችርቻሮ ዋጋ ይሞላል።

**ክፍል 3:- ቤተሰቡ ባለፈው አንድ ወር ለአላቂ ዕቃዎችና ለሲጋራ ያወጣው ወጪ**

በዚህ ክፍል የሚሰበሰቡት መረጃዎች ቤተሰቡ በጥናቱ ወቅት ቢጠቀምባቸውም ባይጠቀምባቸውም ወጪ ያወጣባቸው ከማምረቻ፣ ከንግድ፣ . . . ወዘተ ለቤተሰቡ ያዋላቸው/የሚያውላቸው እንዲሁም ከተለያየ ምንጭ በነፃ ያገኛቸው/የተረከባቸው አላቂ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዋጋ ነው።

በዚህ ቅፅ መረጃ የሚሰበሰብላቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች በሚከተሉት ርዕሶች ስር የሚካተቱ ናቸው።

1. ነዳጅና ሃይል

በዚህ ርዕስ ስር በዋነኛነት መረጃ የሚፈለግላቸው ክብሪት፣ ባትሪ ድንጋይ፣ ሻማ፣ ጧፍ፣ እጣን፣ ከሰል፣ እንጨት፣ ቅጠላ ቅጠል. . .፣ ነጭ ጋዝ/ላምባ/ናፍታ፣ ኩበት ቤተሰቡ ባለፈው አንድ ወር ወጪ ያወጣባቸው ነዳጅና ሃይል በዚህ ክፍል የዋጋ መረጃቸው በተገቢው ቦታ ይሞላል።

2. ለፅዳት የሚያገለግሉ እቃዎች፣

በዚህ ርዕስ ስር በዋነኛነት ለየብቻ መረጃ የሚፈለግላቸው የፅዳት ዕቃዎች የልብስ ሳሙና፣ ኦሞ፣ እንዶድ፣ የብሳና ቅጠል ሲሆኑ ከዚህ ውጪ የሚያጋጥሙ የፅዳት ዕቃዎች አጠቃላይ ዋጋ ሌሎች በሚለው በኮድ 700 ላይ ይሞላል። ከዚህ ውጪ ሊያጋጥሙ የሚችሉ የፅዳት ዕቃዎች በረኪና፣ የሚጤሱ ቅጠላ ቅጠሎችና ስራስሮችና የጫማ ቀለም የመሳሰሉት ናቸው።

3. ለትራንስፖርት የወጣ

በዚህ አርእስት ስር ቤተሰቡ ባለፈው አንድ ወር ለአውቶብስ፣ ለጋሪ፣ በእንስሳ ለመጓዝ፣ የተሽካሚ ኪራይ ለትምህርት ቤት ጉዞ የተከፈለ ጠቅላላ ወጪ በኮድ 622 ይሞላል።

4. ሲጋራ፣ ትምባሆ፣ ሱረት፣ ጋያ

በዚህ ርዕስ ስር ቤተሰቡ በጥናቱ ቀናት ውስጥ የተጠቀመውን ዋጋ ብቻ ይመዘገባል በዚህ ርዕስ በጥናቱ ቀናት ውስጥ ተመርቶ ወይም በስጦታ መልክ ተገኝቶ በጥናቱ ቀናት ውስጥ ጥቅም ላይ ሳይውል የተቀመጠው ወይም የተጠራቀመው የሲጋራ፣ ትምባሆ፣ ሱረትና ጋያ ክምችት መረጃ አይሰበሰብም።

በክፍል 2 እና 3 የሚመዘገቡት ቤተሰቡ ጥናቱ በሚመለከተው ወቅት ውስጥ የተረከባቸው ወይም ያገኛቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች (ከተወሰኑት በስተቀር) በጥናቱ ወቅት ውስጥ ላይጠቀምባቸውም ይችላል።

ይኸውም:-

- እጅ በእጅ ገንዘብ ተከፍሎ የተረከባቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች በሙሉ፣
- ቤተሰቡ ከራሱ የማምረቻ፣ ንግድና ሌሎች ድርጅቶች ለቤተሰቡ አገልግሎት እንዲውል በማሰብ ወደ ቤተሰቡ የገባው ዕቃ/ያገኘው አገልግሎት፣
- ቤተሰቡ በዱቤ የተረከባቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች በሙሉ፣

- ቤተሰቡ በነፃ፣ በዕርዳታ፣ በስጦታ፣ . . . ወ.ዘ.ተ. ያገኛቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች በሙሉ የሚመዘገቡ ሲሆን የዋጋው መጠን የማይታወቅ ሲሆን በአካባቢው የችርቻሮ ዋጋ መሰረት መሰላት እንደሚኖርበት በጥልቀት መገንዘብ ያስፈልጋል::
- ቤተሰቡ ከጫካም ሆነ ከሜዳ የሰበሰባቸው ይመዘገባሉ::

ልዩ ትኩረት:- ከሰል፣የማገዶ እንጨትና ኩበት መረጃ የሚሰበሰበው በጥናቱ ወቅት ውስጥ ቤተሰቡ ከተጠቀመበት ብቻ ነው::

እነዚህ ምዝገባዎች ሲካሄዱ ስህተት እንዳይከሰት ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል:: ይኸውም፣

- ቤተሰቡ የተወሰነ ገንዘብ ከፍሎ የተረከባቸውና ዕዳቸው ገና ተከፍሎ ያላለቁ ዕቃዎች በጥናቱ ወቅት እስከተረከባቸው ድረስ የሚመዘገብላቸው ሙሉ ዋጋቸው እንጂ የተከፈለው ብቻ አለመሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::
- በነፃ በስጦታ፣ በዕርዳታ የተገኙት በጥናቱ ወቅት (መረጃው በተሰበሰበበት ወቅት) የችርቻሮ ዋጋ መሠረት የዋጋ ግምታቸው ይሰላላቸዋል::
- ቤተሰቡ ከጥናቱ ወቅት በፊት ለተረከባቸው ዕቃዎች በጥናቱ ወቅት ዕዳ ቢከፈል ዕቃውን የተረከበው በጥናቱ ወቅት ባለመሆኑ የተከፈለው የገንዘብ መጠን አይመዘገብለትም::
- ቤተሰቡ ምንም እንኳ በጥናቱ ወቅት ገንዘብ ቢከፍልበትም ካልተረከበው አይመዘገብም::

በክፍል 3 ቤተሰቡ ስማቸው በዓምድ 14 ለተጠቀሱት ዕቃዎች ባለፈው አንድ ወር ማለትም መረጃ ሰብሳቢው ቤተሰቡ ጋ ከደረሰበት ቀን ወደ ኋላ ባሉተ 30 ቀናት ውስጥ ቤተሰቡ ያወጣው ወጪ የሚመዘገብበት ክፍል ነው::

ለምሳሌ:- መረጃ ሰብሳቢው ቤተሰቡጋ ሰኔ 25/00 ቢደርስ ቤተሰቡ ከግንቦት 25 - ሰኔ 24/00 ያወጣው ወጪ ተጠይቆ ይሞላል ማለት ነው::

**ዓምድ 13:-** ተራ ቁጥር:- በዚህ ዓምድ ተራ ቁጥር አስቀድሞ ተሞልቷል::

**ዓምድ 14:- የዕቃው ዓይነት**

በዚህ ዓምድ ስር አላቂ ዕቃዎች/አገልግሎቶች ማለትም ክብሪት፣ ባትሪ ድንጋይ፣ ሻማ፣ ሚፍ፣ወ.ዘ.ተ. የመሳሰሉት ተዘርዝረዋል:: ስለሆነም በዓምድ 16 የሚሰበሰበው መረጃ በዓምድ 14 ለተዘረዘሩት ዕቃዎች ነው:: በዚህ ዓምድ ያልተዘረዘረ ዕቃ ካለ የዕቃውን ጠቅላላ ዋጋ ሌሎች በሚለው ኮድ 700 ላይ በተገቢው ቦታ ይሞላል::

**ዓምድ 15:- የዕቃው ኮድ**

በዚህ ዓምድ ስር የዕቃው ኮድ አስቀድሞ ተሞልቷል::

**ዓምድ 16:- ባለፈው ወር ቤተሰቡ ለዕቃው ያወጣው ጠቅላላ ወጪ ምን ያህል ነው?**

ባለፈው አንድ ወር ቤተሰቡ በዓምድ 14 ለተመዘገበው ዕቃ ያወጣው ወጪ ተጠይቆ የሚሞላበት አምድ ሲሆን የብሩ ብዛት «ብር» በሚለው ስር የሳንቲም ብዛት ደግሞ «ሣ» በሚለው ስር ይመዘገባል::

ማስታወሻ:- ቤተሰቡ ባለፈው አንድ ወር ለአውቶብስ፣ ለጋሪ፣ . . . ወ.ዘ.ተ. ያወጣው ወጪ በኮድ 622 የሚሞላ መሆኑን ማስታወስ ይገባል::

## ክፍል 4:- የአመጋገብ ሁኔታ፣ የወጪ/የገቢ ምንጭና ጠቋሚ የኑሮ ሁኔታ (ደረጃ) የሚስተናገዱበት ክፍል ነው::

በዚህ አርዕስት ስር በዓምድ 18 የተካተቱ የተፈጩ፣ ያልተፈጩና የተከኩ የምግብ እህሎች፣ ስጋና የእንስሳት ተዋጽኦ፣ አልኮልና አልኮል ያልሆኑ መጠጦች፣ አትክልትና ፍራፍሬ የመሳሰሉት ተዘርዝረዋል:: በተዘረዘሩት የምግብና መጠጥ መሠረት አስፈላጊው መረጃ ይሞላል:: በዓምድ 18 ከተዘረዘሩት ውጪ ቤተሰቡ ወጪ ያወጣባቸው ምግብ/መጠጥ ካለ የምግቡን/መጠጡን ስም ከታች ከተዘረዘረው ለፍጆታ የዋለ የምግብና የመጠጥ ዝርዝር ሠንጠረዥ ላይ በመፈለግ ተስማሚውን ስምና ኮድ መሙላት ይገባል:: ሆኖም ቤተሰቡ ወጪ ያወጣበት ምግብ/መጠጥ በዝርዝሩ ውስጥ ከሌለ ቤተሰቡ ወጪ ያወጣበት ምግብ/መጠጥ ጠቅላላ ዋጋ ለሌሎች በተሰጢው ኮድ 95 በመሙላት አስፈላጊው መረጃ ይሰበሰባል:: እንዲሁም ከተሰጡት የመጠን መለኪያዎች ውጪ ካጋጠመን የመጠን መለኪያውን ስም ከተሞላ በኋላ በኮድ ቦታ ላይ ለሌሎች የተሰጢው ኮድ 95 ይሞላል:: ጥናቱ በሚመለከተው ጊዜ ውስጥ ለፍጆታ የዋሉትን የምግብና የመጠጥ ዓይነት በምንመዘግብበት ጊዜ በቅፁና በዚህ መመሪያ የተዘጋጀውን የዕቃዎችና ሸቀጣ ሸቀጦች ዝርዝር በመጠቀም የዕቃውን ስምና ትክክለኛ ኮዱን መመዝገብ የሚያስፈልግ ሲሆን የሚከተሉትን መመሪያዎች መከተል ያስፈልጋል::

ሀ. ለፍጆታ የዋለው በርበሬና ድልህ ውስጥ የተጨመረው የቅመማ ቅመም መጠንና የገንዘቡ ልክ ተለይቶ የሚታወቅ ከሆነ የቁንዶ በርበሬ፣ የዝንጅብልና የበርበሬው መጠን ለየብቻ ተለልቶ በተሰጣቸው ኮድ መሠረት አስፈላጊው መረጃ የሚሞላላቸው ሲሆን ከዚህ ውጪ ያሉት ቅመማ ቅመሞች ግን በአንድነት ይመዘገባሉ:: ነገር ግን ለፍጆታ በዋለው በርበሬና ድልህ ውስጥ የተጨመረው የቅመማ ቅመምና የገንዘብ ልክ ተለይቶ የማይታወቅ ከሆነ ግን በበርበሬ ኮድ በአንድነት መመዝገብ አለበት::

ለ. ቤተሰቡ የዱር እንስሳትና አዕዋፍ ተመግቦ ከሆነ የዱር እንስሳው ወይም የወፉን ዓይነት በመፃፍ ኮድ 95 በመስጠት መጠኑ ከዚህ መመሪያ ላይ ካለው የመጠን መለኪያ በማገናዘብ ይሞላል::

ሐ. ከጫካ፣ ከልመናና ከስጦታ የተገኘው የምግብና የመጠጥ ዓይነት መለየት ከተቻለ በሚመለከተው ቦታ ይሞላል:: መለየት ካልተቻለ ስሙ በአጠቃላይ ተገልፆ መጠኑ መመዝገብ ይኖርበታል::

መ. በሆቴል ለፍጆታ የዋለ ምግብና መጠጥ መጠኑና ስሙ እንዲሁም ቤተሰቡ/የቤተሰቡ አባል ያወጣው ብቻ ይመዘገብለታል::

ሠ. ሠርግ ቤትና ሐዘን ቤት የተወሰደ ምግብና መጠጥ፣ ከእነዚህ ጋር የተያያዙ ሌሎች ልዩ ልዩ ወጪዎች ለምሳሌ:- ለጋብቻና ለልደት ወጪ የሆነ፣ በክፍል 4 እንዳይመዘገብ መጠንቀቅ ያስፈልጋል:: መመዝገብ ያለበት በክፍል 2 በመሆኑ ነው:: ይሁን እንጂ ከተዘጋጀው ውስጥ ቤተሰቡ ቢመገብ የተመገበው ያህል ብቻ ተወስዶ በክፍል 4 መመዝገብ ይኖርበታል::

ረ. አንድ ቤተሰብ (የቤተሰብ አባል) በሆቴል ለራሱ ያወጣው ወጪ በክፍል 4 የሚመዘገብ ሲሆን ለሌላ (ሰው) ጋብዞ ከሆነ ግን መመዝገብ ያለበት በክፍል 2 ነው::

<u>**ዓምድ 17:- ተራ ቁጥር:-**</u> በዚህ ዓምድ ተራ ቁጥር አስቀድሞ ተሞልቷል::

<u>**ዓምድ 18:- ለፍጆታ የዋለው የምግብና መጠጥ ዝርዝር**</u>

በዚህ ዓምድ ስር በቀጣይ ዓምዶች መረጃ የሚሰበሰብላቸው የምግብና የመጠጥ ዓይነቶች ተሞልተዋል:: ከተሞሉት ውጪ ካጋጠመ ከዚህ በታች የቀረቡትን ስምና ኮዶች በመጠቀም መረጃው ይሰበሰባል::

**ለፍጆታ የዋለ የምግብና የመጠጥ ዝርዝር ሠንጠረዥ**

| እህል | ኮድ |
|---|---|
| ነጭ ጤፍ | =01 |
| ቀይ /ሰርገኛ ጤፍ | =02 |
| ገብስ | =03 |
| ስንዴ | =04 |
| በቆሎ | =05 |
| ማሽላ | =06 |
| ዘንጋዳ | =07 |
| አጃ | =08 |
| ዳጉሣ | =24 |
| ሩዝ | =50 |
| ሲናር | =51 |
| ሽሮ/ቆሎ | =63 |

| ጥራጥሬ | ኮድ |
|---|---|
| ባቄላ | =09 |
| ምስር | =14 |
| ሽምብራ | =40 |
| አተር | =41 |
| አደንጓሬ | =44 |
| ጓያ | =47 |
| ቦለቄ | =52 |
| አብሽ | =54 |

| የቅባት እህል | ኮድ |
|---|---|
| ተልባ | =10 |
| ለውዝ/አቾሎኒ | =11 |
| ሰሊጥ | =12 |
| ኑግ | =48 |

| ቅመማ ቅመም | ኮድ |
|---|---|
| ቁንዶ በርበሬ | =13 |
| ዝንጅብል | =57 |
| ቅመም ቅመም | =83 |
| በርበሬ | =85 |
| እርድ | =89 |

| አትክልት | ኮድ |
|---|---|
| ቅጠላ ቅጠል | =15 |
| ሽፈራ/አለቆ | =23 |
| ሱፍ አበባ | =25 |
| ቀይ ሽንኩርት | =31 |
| ቆስጣ | =32 |
| ነጭ ሽንኩርት | =33 |
| ፎስሊያ | =35 |
| ቲማቲም | =46 |
| ጎመን | =49 |
| ቀይ ስር | =55 |
| ካሮት | =56 |
| ሰላጣ | =58 |
| ጥቅል ጎመን | =59 |
| ዱባ | =60 |
| ቃሪያ | =84 |

| ፍራፍሬ | ኮድ |
|---|---|
| ሙዝ | =19 |
| አናናስ | =29 |
| አቮካዶ | =30 |
| ፍራፍሬ | =36 |
| ማንጎ | =37 |
| ብርቱካን | =42 |
| ቁልቋል | =91 |

| ቡና፣ጫት፣ጌሾና ሌሎች | ኮድ |
|---|---|
| ቡና | =16 |
| የቡና ቅጠል/አሻራ/ ሻይ | =90 |
| ጫት | =17 |
| እንሰት/ቡላ | =18 |
| ጌሾ | =21 |

| ድንችና ሌሎች ስራስሮች | ኮድ |
|---|---|
| ድንች | =26 |
| ሚጣጢስ/ሸሮቂ/ | =34 |
| አሚቾ | =38 |
| ቆጮ | =39 |
| ጎደሬ | =43 |
| ስኳር ድንች | =45 |

| ስኳር ጨውና ማር | ኮድ |
|---|---|
| ሸንኮራ አገዳ | =27 |
| ስኳር | =75 |
| ማር | =76 |
| ጨው | =81 |

| ዳቦና ሌሎች | ኮድ |
|---|---|
| እንጀራ | =77 |
| ወጥ | =79 |
| ዳቦ | =86 |
| ፓስታ/መኮረኒ | =87 |

| ስጋ | ኮድ |
|---|---|
| የከብት ስጋ | =61 |
| የበግ/የፍየል ስጋ | =62 |
| የዶሮ | =67 |

| ዘይት፣ቅቤና እንቁላል | ኮድ |
|---|---|
| ቅቤ/አይብ | 64 |
| ወተት/እርጎ | 65 |
| እንቁላል | 68 |
| የምግብ ዘይት | 82 |

| አልኮልና ለስላሳ መጠጦች | ኮድ |
|---|---|
| ጠላ | =70 |
| ጠጅ | =71 |
| ቢራ | =72 |
| አረቄ/ካቲካላ | =73 |
| ለስላሳ መጠጥ | =74 |
| ቀረቦ/ቀረዶ | =88 |

| ሌሎች(ይገለፅ) | =95 |
|---|---|

ማስታወሻ፡- ቤተሰቡ ከላይ ከተዘረዘሩት ምግብ/መጠጥ ሌላ ወጪ ያወጣባቸው፣ በስጦታና በርዳታ ያገኛቸው . . . ወ.ዘ.ተ. ምግብ/መጠጥ ከተገኘ በዓምድ 17 ተ.ቁ. ከተሞላ በኋላ በዓምድ 18 ኮድ 95 በመሙላት አጠቃላይ ለዕቃው የወጣው ወጪ ይመዘገባል::

ዓምድ 19:- ኮድ:- ለእያንዳንዱ የፍጆታ ዕቃ ኮድ አስቀድሞ ተሞልቷል:: አስፈላጊ ሆኖም ሲገኝ ሊሞላ ይችላል::

**ዓምድ 20:- ቤተሰቡ ባለፈው ሳምንት ገዝቶ የተጠቀመው ምግብ/መጠጥ መጠንና ዋጋ**

በዚህ ዓምድ ቤተሰቡ ባለፈው ሣምንት የገዛው የምግብ/የመጠጥ መጠንና ዋጋ እንዲሁም ከገዛው ውስጥ የተጠቀመው የመጠን ድርሻ በመቶኛ የሚሞላበት ነው::

ለምሳሌ:- መረጃ ሰብሳቢው ቤተሰቡ ጋ ሰኔ 25 ቢደርስ ቤተሰቡ ከሰኔ 18 - 24 ድረስ የተጠቀመው መረጃ ተጠይቆ ይሞላለታል::

<u>የተገዛው መጠን፡-</u> በዚህ ንዑስ ዓምድ ቤተሰቡ ስሙ በዓምድ 18 የተገለፀውን ምግብ/መጠጥ ገዝቶ ከሆነ የገዛው መጠን ምን ያህል እንደሆነ የሚመዘገብበት ነው::የመጠን መረጃ ከክፍልፋይ በፊትና በኋላ ያሉትን ቁጥሮች ለመሙላት በሚያስችል መልኩ በሁለት ዓምድ ተዘጋጅቷል::

<u>የመጠን መለኪያ ስምና ኮድ:-</u> በዚህ ንዑስ ዓምድ ስር ቤተሰቡ በዓምድ 18 የተገለፀውን ምግብ/መጠጥ ገዝቶ ከሆነና በዚሁ ዓምድ የመጀመሪያው ንዑስ ዓምድ ላይ የተገዛው መጠን ከተሞላ በዚህ ንዑስ ዓምድ ከዚህ በታች የቀረቡትን የመጠን መለኪያ ስምና ኮድ በመውሰድ በአግባቡ በቦታው ይሞላል::

<u>የመጠን መለኪያዎች</u>

| ስም | ኮድ |
|---|---|
| ኪሎ ግራም | 01 |
| ኩንታል | 02 |
| ጭነት | 03 |
| ዳውላ | 04 |
| ቁና | 05 |
| መደብ | 06 |
| ቁርበት | 07 |
| ስልቻ | 08 |
| አቁማዳ | 09 |
| እስር | 10 |
| ሣቦ | 11 |
| ፓኬት | 12 |
| ቦርሳ/ከረጢት | 13 |

| | |
|---|---|
| ጥቅል | 14 |
| ፒስ/ነጠላ | 15 |
| ባርስ | 16 |
| ሣጥን | 17 |
| ቅጠል | 18 |
| ሊትር | 19 |
| ቅል | 20 |
| ጋን | 21 |
| እንስራ | 22 |
| ጉርዝኝ | 23 |
| ጣሳ | 24 |
| ኩባያ/ክለሣ | 25 |
| ብርጭቆ | 26 |
| ስኒ | 27 |
| ገምቦ | 28 |
| ጠርሙስ | 29 |
| ብር | 30 |
| ማዳበሪያ (ትልቁ) | 40 |
| ማዳበሪያ (ትንሹ) | 41 |
| ድርብ | 42 |
| ሳህን/ሎተሪ | 43 |
| ማንቆርቆሪያ | 44 |
| ፕላስቲክ ቦርሳ/ፌስታል | 45 |
| ዙርባ | 46 |
| እቃራ | 47 |
| የፕላስቲክ ቦርሳ/ፌስታል/ማይካ | 48 |
| ቅርጫት/ቀምባ | 49 |
| ሙዝ(ከነግንዱ) | 50 |
| መለኪያ/ልክ | 51 |
| ጉችዬ | 52 |
| በቆሎ | 53 |
| እንቅብ | 54 |
| ሸክም | 55 |
| ቁጥር | 56 |
| ጎተራ | 57 |
| ሳምባ | 58 |
| ሽሪሜር | 59 |
| እግር | 60 |
| ወሰላ | 61 |
| መስፈሪያ | 62 |
| ቁርፎ | 63 |
| ቆለላ | 64 |
| ጭልፋ | 65 |
| ሌሎች(ይገለፅ) | 95 |

__ጠቅላላ ወጪ (በብር)፡-__ ቤተሰቡ ባለፈው ሳምንት በዓምድ 20 በመጀመሪያው ንዑስ ዓምድ መጠኑን በነገረን የምግብ/የመጠጥ ዓይነት ለመግዛት ያወጣውን ወጪ በመጠየቅ በዚህ ንዑስ ዓምድ ይሞላል፡፡

የተመገበው መጠን በመቶኛ(%) ቤተሰቡ ባለፈው ሳምንት ከገዛው የምግብ/የመጠጥ ዓይነቶች ውስጥ የተመገበው ድርሻ በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ በመጠየቅ በዚህ ዓምድ

በሙሉ ቁጥር ይሞላል::

ለምሳሌ:- ቤተሰቡ ባለፈው ሳምንት 50 ኪሎ ግራም ጤፍ ገዝቶ ሩቡን ተመግቤያለሁ ካለ የተመገበው 12.5 በመቶ ስለሆነ በተገቢው ቦታ 12.5 ይሞላል ማለት ነው::

**ዓምድ 21:- ቤተሰቡ ካመረተው/ካስቀመጠው ባለፈው ሳምንት የተመገበው ምን ያህል ነው?**

በዚህ ዓምድ ቤተሰቡ ራሱ ካመረተው/ወይም ገዝቶ ካስቀመጠው ውስጥ ባለፈው ሳምንት የተመገበው መጠንና የመጠን መለኪያ በተገቢው ቦታ ይሞላሉ::

የተመገበው መጠን:- በዚህ ዓምድ ቤተሰቡ ካመረተው ወይም ከዚህ በፊት አምርቶ ወይም ገዝቶ ካስቀመጠው ውስጥ የተመገበው ካለ መጠኑን በመጠየቅ ይሞላል:: የመጠን መረጃ ከክፍልፋይ በፊትና በኋላ ያሉትን ቁጥሮች ለመሙላት በሚያስችል መልኩ በሁለት ዓምድ ተዘጋጅቷል::

የመጠን መለኪያ ስምና ኮድ:- ቤተሰቡ ተመግቤያለሁ ብሎ የነገረን መጠን በላይኛው ንዑስ ዓምድ ከሞላን በኋላ የመጠን መለኪያ ስምና ኮድ ከዚሁ ክፍል የመጠን መለኪያዎች ዝርዝር ላይ በመውሰድ ይሞላል::

ማስታወሻ:- ቤተሰቡ ከላይ ከተዘረዘሩት የመጠን መለኪያዎች የተለየ ሌላ የመጠን መለኪያ ከነገረን በመጠን መለኪያ ንዑስ ዓምድ ውስጥ ስሙን ከሞላን በኋላ በኮድ ቦታ ላይ ኮድ 95 ይሞላል::

**ዓምድ 22:-ቤተሰቡ በስጦታ/በብድር/በለውጥ፣ከደሞዝ በዓይነት (ከሴፍትኔት ያገኘውን ይጨምራል::) ባለፈው ሣምንት ውስጥ የተመገበው መጠንና የገቢ ምንጭ**

የተመገበው መጠን:- ቤተሰቡ በዓምድ 18 ከተዘረዘሩት ውስጥ በስጦታ ካገኘው ጠቅላላ የምግብ/የመጠጥ ዝርዝር ውስጥ ተመግቤያለሁ ያለው መጠን በዚህ ንዑስ ዓምድ ውስጥ ይሞላል:: የመጠን መረጃ ከክፍልፋይ በፊትና በኋላ ያሉትን ቁጥሮች ለመሙላት በሚያስችል መልኩ በሁለት ዓምድ ተዘጋጅቷል::

የመጠን መለኪያ ስምና ኮድ:- ቤተሰቡ ተመግቤያለሁ ብሎ የነገረንን የተመገበውን መጠን በዚህ ንዑስ ዓምድ ላይ ይሞላል:: የመጠን መለኪያ ስምና ኮድ ከዚሁ ክፍል የመጠን መለኪያዎች ዝርዝር በመውሰድ ይሞላል::

ምርቱ ከየት ተገኘ:- ቤተሰቡ በዓምድ 18 ከተዘረዘሩት ምግብ/መጠጥ ውስጥ በስጦታ አግኝቻለሁ ያለንን ምርት ከየት እንዳገኘ በመጠየቅ ስሙና ኮዱ ይሞላል:: ይኸውም:-

| አማራጭ መልሶች | ኮድ |
|---|---|
| ከዘመድ/ሀገር ውስጥ የተላከ | =01 |
| ከዘመድ/ሀገር ውጭ የተላከ | =02 |
| ከጎረቤት/ከአካባቢዬ | =03 |
| ከሰፈር/ከአካባቢ ውጭ ካለ ሰው | =04 |
| ስጦታ/ከመንግስት | =05 |
| መንግስታዊ ካልሆነ የዕርዳታ ድርጅት | =06 |
| ምግብ ለስራ | =07 |
| በዓይነት ክፍያ | =08 |
| ዕቃ በዕቃ በመለወጥ | =09 |
| ብድር | =10 |
| ሌላ/ይገለፅ | =11 |

**ዓምድ 23: የምግብ እህል በዋነኛነት የሚገዙት ከየት ነው?**

ቤተሰቡ የምግብ እህል በዋንኛነት የሚገዛው ከየት እንደሆነ በመጠየቅ በመጠይቁ ላይ የተዘረዘረው ስምና ኮድ በተገቢው ቦታ ይሞላል:: በመጠይቁ ላይ የተጠቀሱት የግዢ ቦታዎችና ኮድ ከታች ቀርበዋል::

| አማራጭ መልሶች | ኮድ |
|---|---|
| ከዚህ የገጠር ቀበሌ | =1 |
| ከሌላ የገጠር ቀበሌ | =2 |
| ቅርብ በሚገኝ የከተማ ገበያ | =3 |
| ከክልሉ ዋና ከተማ | =4 |
| ከአዲስ አበባ | =5 |
| ሌላ/ይጠቀስ | =6 |

ዓምድ 24:- የቤተሰቡ አባል/ቤተሰቡ ባለፈው ሳምንት ከቤት ውጪ የተዘጋጀ ምግብ ገዝቶ ተመግቧል?

በዚህ ዓምድ ባለፈው ሳምንት ውስጥ ቤተሰቡ ወይም የቤተሰቡ አባል ከቤት ውጭ የተዘጋጀ ምግብ ገዝቶ መመገቡ ከተጠየቀ በኋላ ገዝቼ ተመግቤያለሁ ካለ ኮድ 1 ገዝቶ ያልተመገበ ከሆነ ደግሞ ኮድ 2 ይሞላል ማለት ነው::

ዓምድ 25:- የቤተሰቡ አባል/ቤተሰቡ ባለፈው ሳምንት ከቤት ውጪ የተዘጋጀ ምግብ ገዝቶ የተመገበ ከሆነ ጠቅላላ ያወጣው ወጪ /በብርና ሣንቲም/ ምን ያህል ነው?

በዓምድ 24 ላይ ቤተሰቡ ከቤት ውጭ የተዘጋጀ ምግብ ገዝቶ መመገቡን ገልጾ ኮድ 1 የተሞላ ከሆነ በዚህ ዓምድ ቤተሰቡ ያወጣው ወጪ በብርና በሳንቲም ይሞላል::

ዓምድ 26:- ባለፈው ሳምንት ለጎረቤት ወይም ለሌሎች ሰዎች(የቤተሰብ አባል ላልሆኑ) ምግብ ሰጥተዋል?

በዚህ ዓምድ ቤተሰቡ ባለፈው ሳምንት ውስጥ የቤተሰቡ አባል ላልሆኑ ሰዎች ምግብ መግቦ ከሆነ አዎን የሚለውን በመምረጥ ኮድ 1 የሚሞላ ሲሆን ከዚህ ውጪ ከመለሰ ደግሞ ኮድ 2 ይሞላል ማለት ነው::

ዓምድ 27 :-ተራ ቁጥር:- ቤተሰቡ ለቀጣይ ጥያቄዎች መልስ በሚሰጥበት ወቅት ተራ ቁጥር በተገቢው ቦታ መሞላት ይኖርበታል::

ዓምድ 28:- በዓምድ 26 አዎ ከመለሱ :- በዓምድ 26 ላይ ቤተሰቡ የቤተሰብ አባል ላልሆነ ምግብ መግቤያለሁ ብሎ ከመለሰ ይህ ዓምድ በመጠየቅ ለተገቢው ጥያቄ ተገቢውን መልስ መሙላት ይገባል:: በዚህ ዓምድ የሚጠየቁትም:-

የምግብ ዓይነት ስምና ኮድ:- በዚህ ዓምድ ቤተሰቡ የቤተሰቡ አባል ላልሆነ ሰው የመገበውን የምግብ ዓይነት በመጠየቅ ይሞላል:: የምግቡን ስም ይሞላና ኮድ 95 በተሰጠው ቦታ ይሞላል::

የተሰጠው የምግብ መጠን:- በመጀመሪያው ንዑስ ዓምድ ላይ ቤተሰቡ ለሰጠው የምግብ ዓይነት መጠኑ በዚህ ንዑስ ዓምድ ይሞላል:: የመጠን መረጃ ከክፍልፋይ በፊትና በኋላ ያሉትን ቁጥሮች ለመሙላት በሚያስችል መልኩ በሁለት ዓምድ ተዘጋጅቷል::

**የመጠን መለኪያ ስምና ኮድ፡-** በዚህ ንዑስ ዓምድ ዓይነቱና መጠኑ የተሞላለት ምግብ የመጠን መለኪያው ቁጥር ተብሎ ይሞላና በኮድ ቦታ ኮድ 95 ይሞላል፡፡

**ምግቡን የሰጡት ለማነው፡-** በዚህ ንዑስ ዓምድ ምግቡ የተሰጠው ሰው ከቤተሰቡ ጋር ያለው ዝምድና ወይም ጉርብትና ከነኮዱ የሚሞላበት ነው፡፡ የዝምድና ወይም ጉርብትና ስምና ኮድ ከታች ቀርቧል፡፡

| አማራጭ መልሶች | ኮድ |
|---|---|
| ለሠራር ሰው | 1 |
| ከሩቅ ቦታ ለመጣ ሰው | 2 |
| ለጎረቤት | 3 |
| ለዘመድ | 4 |
| ሌላ /ይገለፅ/ | 5 |

<u>**ዓምድ 29፡- ባሰፈው ሳምንት የቤተሰብ አባል ያልሆኑ አዋቂ ሰዎች ከአንድ ጊዜ በላይ ከተመገቡ የሚሞላ**</u>

<u>**የተመጋቢዎች ብዛት (አዋቂ ሰዎች)**</u>

የቤተሰብ አባል ያልሆኑ ከአንድ ጊዜ በላይ የተመገቡ አዋቂ ሰዎች ብዛት በመጠየቅ በዚህ ንዑስ ዓምድ ይሞላል፡፡

<u>**የተመገቡበት ቀናት ብዛት**</u>፡- በዚህ ንዑስ ዓምድ የቤተሰቡ አባል ያልሆኑ አዋቂ ሰዎች ከቤተሰቡ ጋር የተመገቡበት ቀናት ብዛት በመጠየቅ በተገቢው ቦታ ይሞላል፡፡

**ዓምድ 30፡- ባሰፈው ሳምንት የቤተሰብ አባል ያልሆኑ ልጆች ከአንድ ጊዜ በላይ ከተመገቡ የሚሞላ**

በዚህ ዓምድ የቤተሰብ አባላት ያልሆኑ ልጆች ከቤተሰቡ ጋር ተመግበው ከሆነ የተመጋቢ ልጆች ብዛትና የተመገቡበት ቀን ብዛት በተገቢው ቦታ ይሞላል፡፡

<u>**የተመጋቢዎች ብዛት (ልጆች)**</u>**፡-** በዚህ ንዑስ ዓምድ ከቤተሰብ ጋር የተመገቡ የቤተሰብ አባል ያልሆኑ ልጆች ብዛት የሚሞላበት ነው፡፡

<u>**የተመገቡበት ቀናት ብዛት፡-**</u> በዚህ ንዑስ ዓምድ ብዛታቸው የተጠየቀላቸው ልጆች ከቤተሰቡ ጋር ለምን ያህል ቀናት እንደተመገቡ በመጠየቅ የቀኑ ብዛት ይሞላበታል፡፡

# ክፍል 5

ይህ ክፍል 5ሀ እና 5ለ በመባል በሁለት ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን ባጠቃላይ የምግብ አቅርቦት ምንጭ ፣ የምግብ እጥረትና እጥረቱን ለመቋቋም የተወሰዱ እርምጃዎች የሚሞላበት ሲሆን የአሞላሉ መመሪያ በዝርዝር ቀርቧል::

## ክፍል 5ሀ:- የምግብ አቅርቦት ምንጭ

ይህ ክፍል የምግብ አቅርቦት ምንጭ የሚሞላበት ነው:: ይኸውም ቤተሰቡ ባለፉት 12 ወራት የተመገቡትን ምግብ በዋነኛነትና በሁለተኛነት ደረጃ ከየት እንዳገኘ ተጠይቆ በተገቢው ቦታ ይሞላል::

ዓምድ 31 ደረጃ:- በዚህ ንዑስ ዓምድ ደረጃ በዋነኛነት እና በሁለተኛነት ቀድሞ ተሞልቷል::

ዓምድ 32-43:- ባለፉት 12 ወራት የተመገቡትን ምግብ በዋነኛነትና በሁለተኛነት ያገኙት ከየት ነው?

ይህ ጥያቄ ለእያንዳንዱ ወራት (ሰኔ፣ሐምሌ ፣ነሐሴ ፣ መስከረም፣ ጥቅምት ፣ህዳር ፣ታህሣሥ፣ ጥር፣ የካቲት፣ መጋቢት ፣ሚያዝያ፣ ግንቦት) ምግብ በዋነኛነትና በሁለተኛነት ያገኘው ከየት እንደሆነ በመጠየቅ ከተሰጡት አማራጭ ኮዶች ውስጥ ተገቢውን አማራጭ መሙላት ይገባል:: የተሰጡትም አማራጭ ኮዶች

| አማራጭ መልሶች | ኮድ |
|---|---|
| ቤተሰቡ ካመረተው | 1 |
| በመግዛት | 2 |
| ከቤተሰብ ወይም ከዘመድ የተሰጠ | 3 |
| ከጎረቤት የተሰጠ | 4 |
| ከሴፍቲኔት/ምግብ ለስራ | 5 |
| ከሴፍቲኔት /ቀጥተኛ ድጋፍ | 6 |
| ሌሎች | 7 |

## ክፍል 5ለ:- የምግብ ዕጥረትና እጥረቱን ለመቋቋም የተወሰዱ እርምጃዎች

ዓምድ 44:- በዚህ ዓምድ ቤተሰቡ ባለፉት 12 ወራት ውስጥ የምግብ እጥረት ደረሰበት እንደነበረ ወይም እንዳልደረሰበት የሚጠየቅበት ነው:: ቤተሰቡ ባለፉት 12 ወራት የምግብ ዕጥረት አጋጥሞት ከነበረ በዓምዱ ስር በተተወ ክፍት ቦታ የምግብ ዕጥረት ያጋጠመበት

የወራት ብዛት ይሞላል:: ቤተሰቡ የምግብ ዕጥረት አጋጥሞት ያልነበረ ከሆነ ዓምዱ በሰረዝ ይታለፋል::

አንድ ቤተሰብ የምግብ ዕጥረት አጋጠመው የሚባለው ከተለያየ ምንጭ በሚያገኘው ገቢ (በማምረት፣ ከእርሻ መገልገያ እንስሳት በስተቀር ያሉ እንስሳትና ውጤታቸውን በመሸጥ፣ በተለየ ምርታማ ስራዎች በማከናወን..ወዘተ የተገኘ ገቢ) ቤተሰቡን ከወር እስከ ወር ለመመገብ ያልቻለ እንደሆነ ነው::

ማስታወሻ:- አንድ ቤተሰብ በአንድ ወር ውስጥ የምግብ እጥረት አጋጥሞታል የሚባለው በወር ውስጥ ቢያንስ ለ5 ቀናት የምግብ እጥረት ካጋጠመው ነው::

ምሳሌ:- አንድ ቤተሰብ በ1997 ዓ.ም. የምርት ዘመን ያመረተው ምርት ቤተሰቡን ለ8 ወራት መግቧል እንበል:: የ1998 ዓ.ም. ምርት እስከሚደርስበት ጊዜ ድረስ የ4ወር የምግብ እጥረት ቢያጋጥመው በተሰጠው ሳጥን ውስጥ 04 ይሞላል ማለት ነው:: በተጨማሪም በሰኔ ወር ለ10 ቀን በሐምሌ ወር 15 ቀን በሌሎቹ ወራት ምንም እጥረት ባያጋጥመው ይህ ቤተሰብ ላለፉት 12 ወራት ውስጥ ለሁለት ወራት የምግብ ዕጥረት ያጋጠመው በመሆኑ በዓምዱ 02 ይሞላለታል::

**ዓምድ 45:- ባለፈው የዝናብ ወቅት ቤተሰቡ የምግብ ዕጥረት አጋጥሞት ነበር?**
ይህ ዓምድ የሚመለከታቸው ባለፉት የዝናብ ወቅት ውስጥ ቤተሰቡ የምግብ ዕጥረት አጋጥሞት ከነበረ በዓምዱ ስር በተተወ ክፍት ቦታ ኮድ 1 ይሞላል:: ቤተሰቡ ባለፈው የዝናብ ወቅት የምግብ ዕጥረት አጋጥሞት ያልነበረ ከሆነ የለም ተብሎ ኮድ 2 በተስማሚው ቦታ ይመዘገባል::

**ዓምድ 46:- ቤተሰቡ ባለፉት 12 ወራት ውስጥ በይበልጥ የምግብ ዕጥረት ያጋጠመው በየትኛው ወር ነው? (የወሩ ስምና ኮድ ይሞላ)**
ቤተሰቡ የምግብ እጥረት አጋጥሞኛል ብሎ በዓምድ 44 ያስመዘገበው የወር ስምና ኮድ በተገቢው ቦታ ይመዘገባል:: በይበልጥ የምግብ ዕጥረት ያጋጠመበት የወር ስም ቤተሰቡን በመጠየቅ ከተሞላ በኋላ ኮዶቻቸው ከታች በተሰጠው በመውሰድ ይሞላል:: ይኸውም:-

| የወራቶች ስም | ኮድ |
|---|---|
| መስከረም | 01 |
| ጥቅምት | 02 |
| ህዳር | 03 |
| ታህሣሥ | 04 |
| ጥር | 05 |

| | |
|---|---|
| የካቲት | 06 |
| መጋቢት | 07 |
| ሚያዝያ | 08 |
| ግንቦት | 09 |
| ሰኔ | 10 |
| ሐምሌ | 11 |
| ነሐሴ | 12 |

በዚህ ዓምድ ቤተሰቡ ባለፉት 12 ወራት የምግብ ዕጥረት ያላጋጠመው ከሆነ ከዓምድ 47-51 ያሉትን ሠረዝ በማድረግ ወደ ዓምድ 52 ይታለፋል:: እንዲሁም ለዓምድ 46 ቤተሰቡ 12ቱንም ወራት የምግብ ዕጥረት አጋጥሞኛል ብሎ ከመለሰ ከዓምድ 47-51 ከተጠየቀለት በኋላ ከዓምድ 52-53 በሠረዝ ከታለፈ በኋላ ከዓምድ 54-57 ያሉት ዓምዶች ይጠየቁለታል::

<u>ዓምድ 47-51 የምግብ ዕጥረት በነበረበት ወቅት ስለነበረው ሁኔታ የሚጠየቅ</u>

<u>ዓምድ 47:- የምግብ ዕጥረት በነበረበት ወቅት ከቤተሰቡ አባላት መካከል አዋቂዎች በቀን ስንት ጊዜ ይመገባሉ?</u>

ይህ ዓምድ የሚሞላው ቤተሰቡ በዓምድ 44 እና በዓምድ 46 ላይ የምግብ ዕጥረት ያጋጠመው ለመሆኑ መረጃዎችን ከሰጠን በነዚህ ወቅቶች ችግሩን ለመቋቋም ከተለመደው የአመጋገብ ሁኔታ በተለየ መልኩ የሚመገብ መሆኑን ለማየት የሚያስችል መረጃ ለማግኘት ያስችላል:: በመሆኑም በዚህ ዓምድ አዋቂዎች አብዛኛው ጊዜ በቀን ስንት ጊዜ እንደሚመገቡ በመጠየቅ መልሱን በተገቢው ቦታ መሙላት ያስፈልጋል::

<u>ዓምድ 48:- የምግብ ዕጥረት በነበረበት ወቅት ከቤተሰቡ አባላት መካከል ልጆች በቀን ስንት ጊዜ ይመገባሉ?</u>

በተመሳሳይ መልኩ በዚህ ዓምድ የምግብ ዕጥረት በነበረበት ጊዜ ልጆች በቀን ስንት ጊዜ እንደሚመገቡ በመጠየቅ ቤተሰቡ የሚነግረንን ምላሽ በተገቢው ቦታ ይሞላል::

<u>ዓምድ 49:- የምግብ ዕጥረት በነበረበት ወቅት ከቤተሰቡ አባላት መካከል/ ቤተሰቡ በችግሩ ምክንያት ወትሮ የማይመረጡ (Less Preferred) ምግቦችን ይመገብ ነበር?</u>

በዚህ ዓምድ የምግብ ዕጥረት ባጋጠመበት ወቅት ቤተሰቡ በችግሩ ምክንያት ወትሮ የማይመገባቸውን (Less Preferred) ምግቦች የተመገበ መሆኑ ተጠይቆ አዎን ካለን በሣጥኑ ውስጥ ኮድ 1 ይሞላል:: ተመራጭነታቸው እምብዛም የሆኑ ምግቦችን ያልተመገበ ከሆነ ደግሞ በሳጥኑ ውስጥ ኮድ 2 ይሞላል:: ለምሳሌ ሳማ ወትሮ የማይመገብ ሆኖ በችግሩ

ምክንያት ግን ተመግቦ ከሆነ ኮድ 1 ይሞላለታል:: እነዚህ ምግቦች አብዛኛውን ገበያ ላይ ላይገኙ ይችላሉ::

**ዓምድ 50:- የምግብ ዕጥረት በነበረበት ወቅት ቤተሰቡ የዱር እንስሳት /አዕዋፍ/ የዱር ፍሬ ይመገብ ነበር?**

የምግብ ዕጥረት በነበረበት ወቅት ቤተሰቡ የዱር እንስሳት/አዕዋፍ/ የዱር ፍሬ መመገብ አለመመገቡ ተጠይቆ ተመግቦ ከነበረ በሳጥኑ ውስጥ ኮድ 1 ያልተመገበ ከነበረ ደግሞ ኮድ 2 ይሞላል::

**ዓምድ 51:- የምግብ ዕጥረት በነበረበት ወቅት ቤተሰቡ ለዘር ያስቀመጠውን እህል ይመገብ ነበር?**

የምግብ ዕጥረት በነበረበት ወቅት ቤተሰቡ ወደፊት ለዘር ይሆነኛል ብሎ ያስቀመጠውን የዘር እህል መመገቡን ከገለፀልን በሳጥኑ ውስጥ ኮድ 1 የሚሞላ ሲሆን ካስቀመጠው የዘር እህል ያልተመገበ ከሆነ ደግሞ ኮድ 2 ይሞላል:: (ለዘር ያላስቀመጠ ከሆነ በሠረዝ ይታለፍ)

**ዓምድ 52:- ቤተሰቡ ካለፉት 12 ወራት ውስጥ የምግብ ዕጥረት ያላጋጠመው ወይም የምግብ አቅርቦት ከሁሉም የተሸለ የሆነለት ወር የትኛው ነው?**

ቤተሰቡ ካለፉት 12 ወራት ውስጥ የምግብ ዕጥረት ያላጋጠመባቸው ወራት ውስጥ የምግብ አቅርቦት የተሸለ የሆነለት ወር ከተጠየቀ በኋላ የሰጠውን ምላሽ የወሩን ስም በመሙላት የወሩን ኮድ ከዚሁ ክፍል ዓምድ 46 ዝርዝር ላይ በማምጣት ለኮድ በተተወው ክፍት ቦታ ላይ ይሞላል::

**ዓምድ 53-54 :- የምግብ ዕጥረት በሌለበት ወቅት**

የምግብ ዕጥረት በሌለበት ወቅት ከቤተሰቡ አባላት መካከል አዋቂዎች/ልጆች በቀን ስንት ጊዜ ይመገባሉ?

እነዚህ ዓምድ ቤተሰቦችን በመጠይቅ አዋቂዎች/ልጆች የምግብ ዕጥረት በሌለበት በቀን ምን ያህል ጊዜ እንደሚመገቡ በመጠየቅ ቤተሰቡ የነገረንን ምላሽ በእነዚሁ ዓምድ በሣጥኑ ውስጥ ቁጥሩ ይሞላል::

**ዓምድ 55:- ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ቤተሰቡ ያመረተውን ምርት በመጨረሱ ምክንያት በግዥ/ስጦታ በመጠየቅ ወይም ደግሞ ከሚመገበው በመቀነስ የተመገበበት ወር ይገለፅ**

ለጥናቱ የተመረጠው ቤተሰብ ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ያመረተውን ምርት በመጨረሱ ምክንያት በግዥ ወይም ስጦታ በመጠየቅ ወይም ደግሞ ከሚመገበው በመቀነስ የተመገበበት ወር ካለ ተጠይቆ የወራቶቹ ስምና ኮድ በዚህ ዓምድ ባለው ቦታ ላይ ይሞላል:: ወር ስምና ኮድ ከዚሁ ክፍል ዓምድ 46 ዝርዝር ላይ በማምጣት ለኮድ በተተወው ክፍት ቦታ ላይ ይሞላል::

ዓምድ 56:- ቤተሰቡ ከሰኔ 1998 - ግንቦት 1999 ዓ.ም. ለምን ያህል ወራት የምግብ ዕጥረት አጋጠመው?

ቤተሰቡ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ማለትም ከሰኔ 1998 - ግንቦት 1999 ዓ.ም. ድረስ የምግብ ዕጥረት አጋጥሞት ከሆነ የምግብ ዕጥረት ያጋጠመበት የወራት ብዛት በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 57:- ቤተሰቡ ከሰኔ 1997 - ግንቦት 1998 ዓ.ም. ለምን ያህል ወራት የምግብ ዕጥረት አጋጠመው?

ቤተሰቡ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ማለትም ከሰኔ 1997 - ግንቦት 1998ዓ.ም. ድረስ የምግብ ዕጥረት አጋጥሞት ከሆነ የምግብ ዕጥረት ያጋጠመበት የወራት ብዛት በዚህ ዓምድ ይሞላል::

# ቅፅ ምዋ 2000/8 ፡ የጤና ሁኔታ መጠይቅ አሞላል

**ክፍል 1፡-የተመረጠው ቤተሰብ አካባቢ መለያ**

ይህ ክፍል ከቅጽ ምዋ98/1 ክፍል 1 የሚወራረስ ነው።

**ክፍል 2፡-የጤና ሁኔታ (ዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በላይ ለሆኑ የቤተሰቡ አባላት የሚሞላ)**

**ዓምድ 8፡- መደበኛ የቤተሰብ አባላት ተራ ቁጥር**

ከቅፅ **ምዋ 2000/2 ዓምድ 8** የተመዘገቡት የቤተሰብ አባላት ተከታታይ ተራ ቁጥራቸው ሳይዛባ ወደዚህ ዓምድ በቀጥታ ይወራረሳል/ ይገለበጣል።

**ዓምድ 9-15፡- በጥናቱ ወቅት የቤተሰቡ የጤና ሁኔታ**

ይህ ጥያቄ ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የሚቀርብ ነው። የቤተሰቡ አባላት በጥናቱ ዕለት በጤና መታወክ ወይም በአደጋ ምክንያት የጤና ችግሮች ከነበራቸው ወይም ከአላቸው (ሕክምና ሊወስዱም ላይወስዱም ይችላሉ) ለተዘረዘሩት ችግሮች በጥያቄው ዓምድ ስር ከተሰጡት አማራጮች ስለ ሁኔታቸው የሚገልጸው አንዱ ተመርጦ በዓምዱ ስር ይመዘገብና በካርድ ኮለም ውስጥ ደግሞ የተሰጠው ኮድ ይሞላል።

**ለምሳሌ፡-መረጃ** ሰብሳቢው ቤተሰቡን የጎበኘው ሰኔ 1 ቀን ቢሆን ጥናቱ የሚመለከተው በጎበኘበት ዕለት ሰኔ 1 ቀን ያለውን ሁኔታ ይሆናል ማለት ነው።

**ማሳሰቢያ፡-** የቤተሰቡ አባል በጉብኝቱ ዕለት ከአንድ በላይ ችግሮች ሊያጋጥመው ስለሚችል በጥንቃቄ ጠይቆ ከህመሞቹ ወይም የአሉትን ችግሮች በተናጠል በመጠየቅ ይህንኑ ችግር በዓምዱ መዝግቦ ተገቢውን ኮድ በካርድ ኮለም ማስፈር ያስፈልጋል።

**ዓምድ 9፡ -ከተቀመጡበት ተነስተው መቆም ይችላሉ?**

ከተቀመጡበት ተነስተው መቆም መቻል አለመቻላቸው ተጠይቆ ስለ ሁኔታቸው ከዚህ በታች ከተገለጸውና ከተሰጡት አማራጮች የችግሩን ክብደት በማገናዘብ አንዱ ተመርጦ በዓምዱ በመመዝገብ ተገቢውን ኮድ በካርድ ኮለም ማስፈር ያስፈልጋል።

ኮድ

በቀላሉ፡-ምንም ዓይነት ችግር ሳይኖርባቸው በቀላሉ መንቀሳቀስ

የሚችሉና ጤናማ አቋም ያላቸው በዚህ ውስጥ ይመደባሉ፡፡ =1

ትንሽ ያስቸግረኛል፡- ሰውነታቸውን ለማንቀሳቀስ መጠነኛ ችግር

ሲኖርባቸው የሚገለጽበት ነው፡፡ =2

በብዙ ችግር፡-ሰውነታቸውን ለማንቀሳቀስ በጣም የሚቸገሩና

በግድ የሚንቀሳቀሱ በዚህ ውስጥ ይካተታሉ፡፡ =3

አልችልም፡-አካላቸው ፈጽሞ ለመንቀሳቀስ የሚያስቸግራቸውና

መንቀሳቀስ የማይችሉ ደግሞ አልችልም የሚለው ይሞላላቸዋል =4

ዓምድ 10 ፡-የቤት ወለል መጥረግ ይችላሉ?

የቤታቸውን ወለል መጥረግ መቻል አለመቻላቸው ተጠይቆ ስለ ሁኔታቸው የገለጹትን ከዚህ በታች ከተገለጸውና ከተሰጡት አማራጮች ጋር የችግሩን ክብደት በማገናዘብ አንዱ ተመርጦ በዓምዱ በመመዝገብ ተገቢውን ኮድ በካርድ ኮለም ይሞላል፡፡

| | ኮድ |
|---|---|
| በቀላሉ | = 1 |
| ትንሽ ያስቸግረኛል | = 2 |
| በብዙ ችግር | = 3 |
| አልችልም | = 4 |

ዓምድ 11 ፡- 5 ኪ.ሜ ያህል በእግርዎ መጓዝ ይችላሉ?

5 ኪ.ሜ ያህል በእግራቸው መጓዝ መቻል አለመቻላቸው ተጠይቆ ስለ ሁኔታቸው የገለጹትን ከዚህ በታች ከተገለጸውና ከተሰጡት አማራጮች ጋር የችግሩን ክብደት በማገናዘብ አንዱ ተመርጦ በዓምዱ በመመዝገብ ተገቢውን ኮድ በካርድ ኮለም ይሞላል፡፡

ኮድ

በቀላሉ = 1

ትንሽ ያስቸግረኛል = 2

በብዙ ችግር = 3

አልችልም = 4

**ዓምድ 12: - 20 ሊትር ውሃ ተሸክመው 20 ሜትር መውሰድ ይችላሉ?**

20 ሊትር ውሃ ተሸክመው 20 ሜትር መውሰድ መቻል አለመቻላቸው ተጠይቆ ስለ ሁኔታቸው የገለጹትን ከዚህ በታች ከተገለጸውና ከተሰጡት አማራጮች ጋር የችግሩን ክብደት በማገናዘብ አንዱ ተመርጦ በዓምዱ በመመዝገብ ተገቢውን ኮድ በካርድ ኮለም ይሞላል::

ኮድ

በቀላሉ = 1

ትንሽ ያስቸግረኛል = 2

በብዙ ችግር = 3

አልችልም = 4

**ዓምድ 13:- በጠዋት ተነስተው የእርሻ መሬትዎን ለግማሽ ቀን መቆፈር ይችላሉ?**

በጠዋት ተነስተው የእርሻ መሬታቸውን ቢያንስ ለግማሽ ቀን መቆፈር መቻል አለመቻላቸው ተጠይቆ ስለ ሁኔታቸው የገለጹትን ከዚህ በታች ከተገለጸውና ከተሰጡት አማራጮች ጋር የችግሩን ክብደት በማገናዘብ አንዱ ተመርጦ በዓምዱ በመመዝገብ ተገቢውን ኮድ በካርድ ኮለም ይሞላል::

ኮድ

በቀላሉ = 1

ትንሽ ያስቸግረኛል = 2

በብዙ ችግር = 3

አልችልም = 4

**ዓምድ 14-15 :- እነዚህ ችግሮች(የመስማት፣የማየት) አሉባቸው?**

የመስማትና የማየት ችግር እንዳለባቸውና እንደሌለባቸው ተጠይቆ ስለ ሁኔታቸው የገለጹትን ከዚህ በታች ከተገለጸውና ከተሰጡት አማራጮች ጋር የችግሩን ክብደት በማገናዘብ የሚሞላበት ነው:: በነዚህ ዓምዶች ውስጥ እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ስለነዚህ ችግሮች ሲጠየቅ ችግሩ ከሌለበት ምንም የለበትም ተብሎ ሲሞላለት፣ አልፎ አልፎ ሙሉ ለሙሉ መስማትና ማየት ካልቻሉ ደግሞ አንዳንድ ጊዜ፣ተብሎ ይሞላል :: በሁለቱም ጆሮዎች በደንብ መስማት ወይም ዓይኖቻቸው፣ በደንብ ማየት ካልቻሉና በማንኛውም መልኩ መጠነኛ ችግር ኖሮአቸው የቀነሰ ከሆነ ደግሞ የደከመ የመስማት ወይም የማየት ችግር እንዳለባቸው የሚገለጽበት ሲሆን ከአላቸው አካል በአንዱ ወይም በሁለቱም ላይ ችግሩ ከፍተኛ ሆኖ መስማት ወይም ማየት የተሳናቸው ከሆነ ተጠይቆ የሚሞላበት ዓምድ ነው::

**ዓምድ 14_:-.የመስማት ችግር አለባቸውን ?**

| | ኮድ |
|---|---|
| ምንም የለባቸውም፣ | = 1 |
| አንዳንድ ጊዜ | = 2 |
| ደካማ የመስማት አቅም | = 3 |
| አንድ ጆሮ መስማት የተሳነው | = 4 |
| ሁለት ጆሮ መስማት የተሳነው | = 5 |

**ዓምድ 15:-የማየት ችግር አለባቸውን ?**

| | ኮድ |
|---|---|
| ምንም የለባቸው፣ | = 1 |
| ከቅርብ የማየት ችግር | = 2 |
| ከርቀት የማየት ችግር | = 3 |
| በአጠቃላይ የደከመ ዕይታ አላቸው | = 4 |
| በምሽት ማየት አለመቻል | = 5 |
| አንድ ዓይናቸው የታወረ | = 6 |

ሁለት ዓይናቸው የታወረ = 7

ሌላ/ይገለጽ/ = 8

**ክፍል 3**

**ዓምድ 16-31:- የህመም ሁኔታ (ለአለፉት አራት ሣምንታት ጊዜ)**

**(ዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በላይ ለሆኑ የቤተሰብ አባላት የሚሞላ) ከአራት ሳምንታት በላይ የቆየ ህመም ከሆነ ኮድ 77 ይሞላ::**

አንድ ሰው የጤና ችግር ወይም አደጋ አጋጥሞታል የሚባለው ታሞ ወይም አደጋ ደርሶበት የጤና መታወክ ሲያጋጥመው ነው::

- ሕመም ማለት የአካል ወይም የአዕምሮ ደህንነት መጓደል ማለት ሲሆን ማንኛውም የቤተሰቡ አባል ባለፉት አራት ሳምንታት ውስጥ ለአጭር ጊዜ/ቢያንስ ለአንድ ሰዓት/ በአጋጠመው ሕመም ታሞ ከነበረ የጤና ችግር እንዳጋጠመው ይወሰዳል::
- በአደጋ ምክንያት የጤና ችግር አጋጥሞታል የሚባለው በጉዳቱ ምክንያት ቢያንስ ለአንድ ሙሉ ቀን የዘወትር ተግባሩን ለማከናወን ካልቻለና አደጋው ባደረሰው ጉዳት ምክንያት ሕክምና ያደረገና ወይም በአደጋው ምክንያት ሕክምና አስፈልጎት ያጣን ግለሰብ ያጠቃልላል::

**ዓምድ 16:- መደበኛ የቤተሰብ አባላት ተራ ቁጥር**

**ከቅፅ ምዋ 2000/2 ዓምድ 8 የተመዘገቡት የቤተሰብ አባላት ተከታታይ ተራ ቁጥራቸው ሳይዛባ ወደዚህ ዓምድ በቀጥታ ይወራረሳል/ ይገለበጣል::**

**ዓምድ 17:- ባለፉት አራት ሳምንታት ያጋጠመዎትህመም/ጉዳት ነበረ?**

**ኮድ**

አዎ = 1

የለም = 2 (የለም ብለው ከመለሱ ወደ ዓምድ 20 ይታለፋል::)

**ዓምድ 18:- ባለፉት አራት ሳምንታት ለምን ያህል ቀናት ታመሙ?**

ዓምድ 17 መታመማቸውን ከገለጹ ባለፉት አራት ሳምንታት በማንኛውም የህመም ዓይነት ታመው የቀሩባቸው ቀናት ብዛት የሚመዘገብበት ይሆናል፡፡

**ዓምድ 19:- በህመም/በጉዳት ምክንያት ለስንት ቀናት ከመደበኛ ሥራዎ ቀሩ?**

በዓምድ 17/18 ህመም/አደጋ አጋጥሞናል ብለዉ ለያንዳንዱ የቤተሰብ አባል በህመሙ/በደረሰበት አደጋ ምክንያት ባለፉት አራት ሳምንታት ለምን ያህል ቀናት ከመደበኛ ሥራ እንደተስተጓጎለ (ለሕፃናት) ትምህርት/ጨዋታ እንዳቋረጠ ተጠይቆ ትክክለኛውን መልስ በካርድ ኮለሞች ---- ይመዘገብለታል፡፡ በዚህም መሠረት ምንም እንኳን ቢታመምም ከመደበኛ ተግባሩ ከሥራ/ከትምህርት ካልተስተጓጎለ "00" በተሰጠው ቦታ ውስጥ ይሞላለታል፡፡ ሆኖም አደጋ አጋጥሞኝ ነበር ላሉ የቤተሰብ አባላት በዚህ ጥያቄ ቢያንስ 1 ቀን ከመደበኛ ሥራቸው/ትምህርታቸው ሊያቋርጡ እንደሚችሉ ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡

**ዓምድ 20:- የጐላ የክብደትመቀነስ ነበረዎት?**

ኮድ

አዎ = 1

የለም = 2 (የለም ብለው ከመለሱ ወደ ዓምድ 22 ይታለፋል፡፡)

ባለፉት አራት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ የቤተሰብ አባል በህመም/በጉዳት ምክንያት ለመልስ ሰጭው በውል የታወቀውንና የተገነዘበውን የጐላ ነው ብሎ የገመተውን ከ 2 ኪሎ ግራም ያላነሰ የክብደት መቀነስ ከአጋጠመውና ከነበረው "አዎ" ተብሎ በዓምዱ ይጻፍና ለኮድ በተመደበለት ቦታ ደግሞ ኮድ "1" ይሞላል፡፡ ምንም የክብደትመቀነስ ካላጋጠመወ ደግሞ በዓምዱ "የለም" ተብሎ ይጻፍና ለኮድ በተመደበለት ቦታ ኮድ "2" ይሞላል፡፡ (የለም ብለው ከመለሱ ወደ ዓምድ 22 ይታለፋል፡፡)

**ዓምድ 21:- ለምን ያህል ቀናት የጐላ የክብደት መቀነስ ነበርዎት?**

ባለፉት አራት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ የክብደትመቀነስ እንደነበራቸው በዓምድ 20 ከገለጹ ለምን ያህል ቀናት ይህ የክብደትመቀነስ እንደተገነዘቡት ተጠይቆ የቀናት ብዛት የሚሞላበትነው፡፡ ከ 4 ሳምንታት በላይ የቆየ ከሆነ የቆየ ህመም መሆኑ ተገልጾ ኮድ"77" ይሞላል፡፡

ዓምድ 22:- ረዥም ጊዜ የቆየ ትኩሳት ነበረዎት?

ኮድ

አዎ = 1

የለም = 2 (የለም ብለው ከመለሱ ወደ ዓምድ 24 ይታለፋል::)

ባለፉት አራት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ የቤተሰቡ አባል በህመም/በጉዳት ምክንያት ረዥም ጊዜ የቆየ ወይም ቀደም ብሎ የጀመረ ተከታታይነት ያለው ሊገልጸው የሚችለው የተሰማው የታወቀው የትኩሳት ህመም እንደነበረው ካለ / ከነበረ "አዎ" ተብሎ በዓምዱ ይጻፍና ለኮድ በተመደበለት ቦታ ደግሞ ኮድ "1" ይሞላል:: ምንም የትኩሳት ህመም ካላጋጠመ ደግሞ በዓምዱ "የለም" ተብሎ ይጻፍና ለኮድ በተመደበለት ቦታ ኮድ "2" ይሞላና በዓምድ 24 ያለውን ጥያቄ ይጠየቃሉ::

ዓምድ 23:- በጠቅላላው ለምን ያህል ቀናት ትኩሳት ነበረዎት?

ባለፉት አራት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ ተከታታይነት ያለው የቆየ ወይም ቀደም ብሎ የጀመረ ተከታታይነት ያለው ሊገልጸው የሚችለው የተሰማው የታወቀውና ሊገልጸው የሚችለው የትኩሳት ህመም እንደነበራቸው በዓምድ 22 ከገለጹ ለስንት ቀናት ታመው እንደነበረ ተጠይቆ የሚሞላበት ይሆናል:: ከ 4 ሳምንታት በላይ የቆየ ህመም ከሆነ የቆየ ህመም መሆኑ ተገልጾ ኮድ"77" ይሞላል::

ዓምድ 24:-.ለረዥም ጊዜ የቆየ የተቅማጥ ህመም ነበረዎት?

ኮድ

አዎ = 1

የለም = 2 (የለም ብለው ከመለሱ ወደ ዓምድ 26 ይታለፋል::)

ባለፉት አራት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ በቀን ቢያንስ አንድ ጊዜ/በላይ ተከታታይነት ያለው የተቅማጥ ህመም(በጣም ቀጭን የሆነ ዓይነምድር) ከነበረው ተጠይቆ የሚሞላበት ይሆናል:: የተቅማጥ ህመም እንደነበረው ከገለጸ "አዎ" ተብሎ በዓምዱ ይጻፍና ለኮድ በተመደበለት ቦታ ደግሞ ኮድ "1" ይሞላል:: ምንም የተቅማጥ ህመም ካላጋጠመወ ደግሞ በዓምዱ "የለም" ተብሎ ይጻፍና ለኮድ በተመደበለት ቦታ ኮድ "2" ይሞላና በዓምድ 26 ያለውን ጥያቄ ይጠየቃሉ::

**ዓምድ 25፡-በጠቅላላው ለምን ያህል ቀናት የተቅማጥ ህመም ነበረዎት?**

ባለፉት አራት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ በቀን ቢያንስ አንድ ጊዜ/በላይ የተቅማጥ ህመም እንደነበራቸው በዓምድ 24 ከገለጹ ለስንት ቀናት ታመው እንደነበረ ተጠይቆ የሚሞላበት ይሆናል፡፡ ከ 4 ሳምንታት በላይ የቆየ ህመም ከሆነ የቆየ ህመም መሆኑ ተገልጾ ኮድ"77" ይሞላል፡፡

**ዓምድ 26፡-ለረዥም ጊዜ የቆየ የማያቋርጥ ሣል ነበረዎት?**

ኮድ

አዎ = 1

የለም = 2 (የለም ብለው ከመለሱ ወደ ዓምድ 28 ይታለፋል፡፡)

ባለፉት አራት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ የቤተሰቡ አባል በህመም/በጉዳት ምክንያት ረዥም ጊዜ የቆየ ቀደም ብሎ ወይም በቅርብ የጀመረ ተከታታይነት ያለው የማያቋርጥ የሣል ህመም እንዳለው ወይም እንደነበረው ከገለጸ "አዎ" ተብሎ በዓምዱ ይጻፍና ለኮድ በተመደበለት ቦታ ደግሞ ኮድ "1" ይሞላል፡፡ ምንም የ ትኩሳት በህመም ካላጋጠመወ ደግሞ በዓምዱ "የለም" ተብሎ ይጻፍና ለኮድ በተመደበለት ቦታ ኮድ "2" ይሞላና በዓምድ 28 ያለውን ጥያቄ ይጠየቃል፡፡ ሣል ሲባል መረጃ ሰጭው የጉንፋን ህመም ነው ብሎ ተመርምሮ አውቆ የገለጸውን የጉንፋን ሳል አለመሆኑን ከመረጃ ሰጭው ጠይቆ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ መረጃ ሰጭው በምርመራ በውል ጉንፋን መሆኑን ካላወቀ የሣል ህመም እንደነበረው ተወስዶ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

**ዓምድ 27፡-በጠቅላላው ለምን ያህል ቀናት ይስሉ ነበር ?**

ባለፉት አራት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ ረዥም ጊዜ የቆየ ቀደም ብሎ ወይም በቅርብ የጀመረ ተከታታይነት ያለው ለረዥም ጊዜ የቆየ የማያቋርጥ የሣል ህመም እንደነበራቸው በዓምድ 26 ከገለጹ ለስንት ቀናት እንደነበራቸው ተጠይቆ የሚሞላበት ይሆናል፡፡ ከ 4 ሳምንታት በላይ የቆየ ህመም ከሆነ የቆየ ህመም መሆኑ ተገልጾ ኮድ"77" ይሞላል፡፡

**ዓምድ 28 :-.የጠቅላላ ሰውነት ሽፍታ ነበረዎት?**

<u>ኮድ</u>

አዎ = 1

የለም = 2 (የለም ብለው ከመለሱ ወደ ዓምድ 30 ይታለፋል::)

ባለፉት 4 ሳምንታት እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል በሙሉ የሰውነት ክፍላቸው ወይም በከፊል የሰውነታቸው ክፍል ሽፍታ አጋጥሞአቸው ከነበረ "አዎ" ተብሎ በዓምዱ ተጽፎ ለኮድ በተመደበለት ቦታ ኮድ "1" ይሞላል:: ምንም ህመም ካልነበረው ደግሞ በዓምዱ "የለም" ተብሎ ተጽፎ ለኮድ በተመደበለት ቦታ ኮድ"2" ይሞላና በዓምድ 30 ያለውን ጥያቄ ይጠየቃል::

**<u>ዓምድ 29:-..በጠቅላላው ለምን ያህል ቀናት የሰውነት ሽፍታ ነበረዎት?</u>**

ባለፉት አራት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ ረዥም ጊዜ የቆየ ቀደም ብሎ የጀመረ በሙሉ የሰውነት ክፍላቸው ወይም በከፊል የሰውነታቸው ክፍል ሽፍታ እንደነበራቸው በዓምድ28 ከገለጹ ለስንት ቀናት እንደታየ ወይም እንደነበራቸው ተጠይቆ የሚሞላበት ይሆናል::ከ 4 ሳምንታት በላይ የቆየ ህመም ከሆነ የቆየ ህመም መሆኑ ተገልጾ ኮድ"77" ይሞላል::

**<u>ዓምድ 30:-የአፍ መቁሰል ወይም የጉሮሮ ህመም ነበረዎት?</u>**

<u>ኮድ</u>

አዎ = 1

የለም = 2

ባለፉት 4 ሳምንታት እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል በውል የተረዳውና በግጭት በመጋጥ በመላጥ ምች ነው ብሎ ከሚገልጸው ቀላል ከሆኑት የመላጥ ችግሮች ሌላ የአፍ መቁሰል ወይም የጉሮሮ ህመም አጋጥሞት ከነበረና በጥናቱ ወቅትም ታሞ ከነበረ "አዎ" ተብሎ በዓምዱ ተጽፎ ለኮድ በተመደበለት ቦታ ኮድ "1" ይሞላል:: ምንም ህመም ካልነበረው ደግሞ በዓምዱ "የለም" ተብሎ ተጽፎ ለኮድ በተመደበለት ቦታ ኮድ "2" ይሞላል::

ዓምድ 31:- በጠቅላላው ለምን ያህል ቀናት የአፍ መቁሰል ወይም የጉሮሮ ህመም ነበረዎት?

ባለፉት አራት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ የአፍ መቁሰል ወይም የጉሮሮ ህመም ህመም እንደነበራቸው በዓምድ30 ከገለጹ ለስንት ቀናት ታመው እንደነበረ ተጠይቆ የሚሞላበት ይሆናል:: ከ 4 ሳምንታት በላይ የቆየ ህመም ከሆነ የቆየ ህመም መሆኑ ተገልጾ ኮድ"77" ይሞላል::

## ክፍል 4

## ክፍል 4ሀ:-የውሃ አቅርቦትና የአካባቢ ንጽህና

ዓምድ 32:-በክረምት ወቅት ቤተሰቡ ለመጠጥ የሚሆን ውኃ የሚያገኘው ከየት ነው?

ቤተሰቡ በጥናቱ ዓመት  በክረምት ወቅት የመጠጥ ውኃ የሚያገኘው ከየት እንደሆነ በመጠየቅ የተሰጠውን መልስ በዓምዱ ሥር ከተዘረዘሩት አማራጮች ጋር በማዛመድ በዓምዱ ውስጥ ዓይነቱን በመግለጽ ተገቢውን ኮድ ማስፈር ያስፈልጋል::

| የመጠጥ ውሃ ምንጮች | ኮድ |
|---|---|
| ከኩሬ /ግድብ | 1 |
| ከወንዝ/ሀይቅ | 2 |
| ከዝናብ ውኃ | 3 |
| ካልተጠበቀ ጉድጓድ | 4 |
| ከምንጭ | 5 |
| ከተጠበቀ የጉድጓድ | 6 |
| ከቤትውጭካለ የቧንቧውኃ | 7 |
| ሌላ /ይገለፅ/ | 8 |

የተጠበቀ ጉድጓድ ወይም ምንጭ

1ኛ- በጉድጓዱ ወይም በምንጩ ዙሪያ በሲሚንቶ የተገነባ ግንብ መኖር አለበት::ይኸውም:-

ሀ. ጉድጓድ ከሆነ ጉድጓዱ በሚገኝበት የአፈር ሁኔታ መሠረት ግንቡ ቢያንስ ከ2 እስከ 4 ሜትር ወደ መሬት ውስጥ የገባ እና 70 ሳንቲ ሜትር ያህል ደግሞ ከመሬት ወደ ላይ ከፍ ብሎ የወጣ መሆን ይኖርበታል፡፡

ለ. ምንጭ ከሆነ ግንቡ ጠንካራ መሬት ወይም አለት እስከሚገኝበት ድረስ መሬት ውስጥ የገባና እንደ አስፈላጊነቱ ከመሬት በላይ ከፍ ብሎ የወጣ መሆን ይኖርበታል፡፡ ግንቡ በአንድ በኩል ውኃ ማውጫ ክፍት ቧንቧ ያለው መሆን አለበት፡፡

2ኛ- በጉድጓድም ሆነ በምንጭ ዙሪያ የተገነባው ግንብ ከላይ ከሲሚንቶ የተሰራ ወይም ሌላ ዓይነት ጥብቅ ክዳን እንዲኖረው ያስፈልጋል፡፡

3ኛ-. ወደ ጉድጓዱ ወይም ምንጩ ጎርፍ እንዳይገባ የጎርፉን አቅጣጫ የሚቀይር ተስማሚ ቦይ ጎርፍ ሊመጣ ከሚችልበት አካባቢ ወይም አቅጣጫ መኖር አለበት፡፡

4ኛ- እንደ መጸዳጃ ቤት ከመሳሰሉት ውኃውን ሊበክሉ ከሚችሉ ነገሮች ጉድጓዱም ሆነ ምንጩ ቢያንስ ቢያንስ ከ25 እስከ 30 ሜትር የራቀ መሆን አለበት፡፡

5ኛ- በተራ ቁጥር 4 የተገለፀው በካይ ቆሻሻ ዓይነት የውኃው ጉድጓድ ወይም ምንጩ ከሚገኝበት ከፍ ባለ ቦታ ቢኖር ርቀቱ በተራ ቁጥር 4 ላይ ከተጠቀሰው ርቀት ብዙ መብለጥ ይኖርበታል፡፡

ስለዚህ ቤተሰቡ ውኃ የሚያገኘው ከላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች በሚያሟላ ሁኔታ ከተጠበቀ ጉድጓድ ወይም ምንጭ ከሆነ ከተጠበቀ ውኃ እንደተጠቀመ ይቆጠራል፤ በቧንቧ የሚመጣ ውኃ ካልሆነ በስተቀር ከወንዝ ወይም ከሐይቅ እየተቀዳ የሚገኘ ው ውኃ በአጠቃላይ ያልተጠበቀ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ስለዚህ ከወንዝ፤ ከሐይቅ ወይም ከኩሬ እየቀዳ የሚጠቀም ቤተሰብ በተጠበቀ ውኃ አይጠቀምም ማለት ነው፡፡ ከቧንቧ የሚገኝ ውኃ ግን በአጠቃላይ እንደተጠበቀ ይቆጠራል፡፡ ውኃው ግን ወደ ተጠቃሚዎቹ ቤት የሚያደርሰው በሰው ጉልበት ወይም በጋማ ከብቶች ሊሆን ይችላል፡፡

**ማሳሰቢያ፡-** **የቤተሰቡ መኖሪያ ቤት ነው ብለን ለዚህ ጥናት የምንወስደው በግልም ሆነ በኪራይ /በደባልነት፤ በማንኛውም መልኩ የያዘውንና እየተጠቀመበት፤እየኖረበት ያለውን ቤት ነው፡፡**

**ዓምድ 33:-በክረምት ወደ ውሃ ለመሄድ ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል? /በደቂቃ/**

በክረምት ወደ ውሃ ለመሄድ ብቻ ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ ተጠይቆ በደቂቃ ሚሞላበት ሲሆን በቤቱ ቅጥር ግቢ የሚገኝ ከሆነ ለ ደቂቃ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ "00 " ይሞላል:: ለመሄድ ብቻ ሲባል ከቤት ተነስቶ ውሃ እስካለበት ስፍራ ላለው ርቀት የሚወስደውን ጊዜ እንጂ ለደርሶ መልስ የሚወስደውን ጊዜ አለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል::

**ዓምድ 34:-በበጋ ወቅት ቤተሰቡ ለመጠጥ የሚሆን ውኃ የሚያገኘው ከየት ነው?**

ቤተሰቡ በጥናቱ፤ የበጋ ወቅት የመጠጥ ውኃ የሚያገኘው ከየት እንደሆነ ከዓምዱ ሥር ከተዘረዘሩት አማራጮች ጋር በማዛመድና በመጠየቅ የተሰጠውን መልስ በዓምዱ ውስጥ ዓይነቱን በመግለጽ ተገቢውን ኮድ ማስፈር ያስፈልጋል::

| የመጠጥ ውሃ ምንጮች | ኮድ |
|---|---|
| ከኩሬ /ግድብ | 1 |
| ከወንዝ/ሀይቅ | 2 |
| ከዝናብ ውኃ | 3 |
| ካልተጠበቀ ጉድጓድ | 4 |
| ከምንጭ | 5 |
| ከተጠበቀ ጉድጓድ | 6 |
| ከቤትውጭካለ የቧንቧውኃ | 7 |
| ሌላ/ይገለፅ/ | 8 |

**ዓምድ 35:-በበጋ ወቅትወደ ውሃ ለመሄድ ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?/በደቂቃ/**

በበጋ ወቅት ወደ ውሃ ለመሄድ ብቻ ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ ተጠይቆ በደቂቃ ሚሞላበት ሲሆን በቤቱ ቅጥር ግቢ የሚገኝ ከሆነ ለ ደቂቃ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ "00 " ይሞላል:: ለመሄድ ብቻ ሲባል ከቤት ተነስቶ ውሃ እስካለበት ስፍራ ላለው ርቀት የሚወስደውን ጊዜ እንጂ ለደርሶ መልስ የሚወስደውን ጊዜ አለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል::

**ዓምድ36:- ይህንኑ ውሃ ነው ለመታጠብ ልብስ ለማጠብና ለሌሎች ጉዳዮች የሚጠቀሙት?**

**ኮድ**

አዎ = 1

የለም = 2

ለመታጠብ ልብስ ለማጠብና ለሌሎች ጉዳዮች የሚጠቀሙት ይህንኑ ውሃ ከሆነ "አዎ" ተብሎ በዓምዱ ተጽፎ ለኮድ በተመደበለት ቦታ ኮድ "1" ይሞላል:: ሌላ ውሃ የሚጠቀሙ ከሆኑ ደግሞ በዓምዱ "የለም" ተብሎ ተጽፎ ለኮድ በተመደበለት ቦታ ኮድ "2" ይሞላል::

**ዓምድ 37:-ቤተሰቡ በዋነኛነት የሚጠቀምበት የመፀዳጃ ዓይነት ምንድን ነው?**

ቤተሰቡ በጥናቱ ወቅት፤ በዋነኛነት የሚጠቀምበት የመፀዳጃ ዓይነት በዓምዱ ሥር ከተሰጡት አማራጮች ተጠይቆ በዓምዱ ውስጥ ዓይነቱን በመግለጽ ተገቢው ኮድ ይሰፍራል::

| የመፀዳጃ ዓይነት | ኮድ |
|---|---|
| ሜዳ /ጫካ | 1 |
| የቤት ዕቃ፤ባልዲ/ፖፖ | 2 |
| የጉድጓድ መፀዳጃ/የግል | 3 |
| የጉድጓድ መፀዳጃ/የጋራ/ | 4 |
| በውሃየሚወርድመፀዳጃ /የግል | 5 |
| በውሃየሚወርድመፀዳጃ /የጋራ | 6 |
| ሌላ /ይገለጽ/-------- | 7 |

**ዓምድ 38:-አዋቂዎች በዋነኛነት የሚጠቀሙበት የመፀዳጃ ዓይነት ምንድን ነው?**

አዋቂዎች በጥናቱ ወቅት፤ በዋነኛነት የሚጠቀሙበት የመፀዳጃ ዓይነት በዓምዱ ሥር ከተሰጡት አማራጮች ተጠይቆ በዓምዱ ውስጥ ዓይነቱን በመግለጽ ተገቢው ኮድ ይሰፍራል::

| የመፀዳጃ ዓይነት | ኮድ |
|---|---|
| ሜዳ /ጫካ | 1 |
| የቤት ዕቃ፣ባልዲ/ፖፖ | 2 |
| የጉድጓድ መፀዳጃ/የግል | 3 |
| የጉድጓድ መፀዳጃ/የጋራ/ | 4 |
| በውሃየሚወርድመፀዳጃ /የግል | 5 |
| በውሃየሚወርድመፀዳጃ /የጋራ | 6 |
| ሌላ /ይገለጽ/-------- | 7 |

**ዓምድ 39 :-ህጻናት በዋነኛነት የሚጠቀሙበት የመፀዳጃ ዓይነት ምንድን ነው?**

ህጻናት በጥናቱ ወቅት፣ በዋነኛነት የሚጠቀሙበት የመፀዳጃ ዓይነት በዓምዱ ሥር ከተሰጡትአማራጮች ተጠይቆ በዓምዱ ውስጥ ዓይነቱን በመግለጽ ተገቢው ኮድ ይሰፍራል፡፡

| የመፀዳጃ ዓይነት | ኮድ |
|---|---|
| ሜዳ /ጫካ | 1 |
| የቤት ዕቃ፣ባልዲ/ፖፖ | 2 |
| የጉድጓድ መፀዳጃ/የግል | 3 |
| የጉድጓድ መፀዳጃ/የጋራ/ | 4 |
| በውሃየሚወርድመፀዳጃ /የግል | 5 |
| በውሃየሚወርድመፀዳጃ /የጋራ | 6 |
| ሌላ /ይገለጽ/--------- | 7 |

**ዓምድ 40:-ቤተሰቡ ለመጠጥም ሆነ ለሌሎች ጉዳች ተፈልቶ የቀዘቀዘ ውኃ የመጠቀም ልምድ አለው?**

ቤተሰቡ በጥናቱ ወቅት ተፈልቶ የቀዘቀዘ ውኃ የመጠጣትና የመጠቀም ልምድ መኖር አለመኖሩ በዓምዱ ሥር ከተሰጡት አማራጮች ተጠይቆ በዓምዱ ውስጥ ዓይነቱን በመግለጽ ተገቢው ኮድ ይሰፍራል፡፡

| | ኮድ |
|---|---|
| ለመጠጥና ሌሎች ጉዳዮች | =1 |
| ለመጠጥ ብቻ | = 2 |

ለሌሎች ጉዳዮችብቻ =3

አያፈላም =4

**ዓምድ 41፡- በቤተሰቡ ውስጥ ምግብ ከመዘጋጀቱ በፊት እጅን የመታጠብ ልምድ አለ?**

**ኮድ**

*አዎ* **= 1**

**የለም = 2**

በቤተሰቡ ውስጥ ምግብ ከመዘጋጀቱ በፊት እጅን የመታጠብ ልምድ ካለ "አዎ" ተብሎ በዓምዱ ተጽፎ ለኮድ በተመደበለት ቦታ ኮድ "1" ይሞላል። ልምድ የሌለው ከሆነ ደግሞ በዓምዱ "የለም" ተብሎ ተጽፎ ለኮድ በተመደበለት ቦታ ኮድ "2" ይሞላል።

**ዓምድ 42፡- በቤተሰቡ ውስጥ ምግብ ከመበላቱ በፊት እጅን የመታጠብ ልምድ አለ ?**

**ኮድ**

አዎ **= 1**

**የለም = 2**

በቤተሰቡ ውስጥ ምግብ ከመብላቱ በፊት እጅን የመታጠብ ልምድ ካለ "አዎ" ተብሎ በዓምዱ ተጽፎ ለኮድ በተመደበለት ቦታ ኮድ "1" ይሞላል። ልምድ የሌለው ከሆነ ደግሞ በዓምዱ "የለም" ተብሎ ተጽፎ ለኮድ በተመደበለት ቦታ ኮድ "2" ይሞላል።

**ክፍል5፡-ለረዥም ጊዜ ኑሮን የሚያናጋ ችግርና /አደጋ ሁኔታ**

**ክፍል5ሀ፡-ቤተሰቡ ባለፉት ሁለት ዓመታት የኑሮ ሁኔታውን የሚያናጋ ችግር ወይም አደጋ ገጥሞት ነበር?**

**ዓምድ 43- ተራቁጥር ከ 01 በመጀመር እስከ 17 ተሰጥቶአል።**

**ዓምድ 44-48፡ ቤተሰቡ ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ የኑሮ ሁኔታውን የሚያናጋ ችግር/አደጋ አጋጥሞት ነበር**

ዓምድ 44-45:- በዓምድ 44 የቤተሰቡ የኑሮ ሁኔታ ያናጋሉ ተብለው የተጠቀሱ ዋና ዋና የችግር ወይም አደጋ ዓይነት የተዘረዘሩ ሲሆን በዓምድ 45 ደግሞ ለችግሮቹ የተሰጡት ኮዶች ተገልጸዋል፡፡

ቤተሰቡ ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ኑሮውን የሚያናጋ አደጋ ወይም ችግር ደርሶበታል የሚባለው በመጠይቁ ዓምድ 44 በተዘረዘሩት ችግሮች ምክንያት ማለትም በድርቅ፣በጎርፍ፣ውርጭና በረዶ፣...ወዘተ በኑሮው ላይ የከፋ ችግር አጋጥሞት ራሱንም ሆነ ቤተሰቡን ማለትም መመገብ ማልበስ ማኖርና ማስተዳደር አቅቶት የተናጋውን ኑሮ ለማስተካከል የቤቱን ንብረት ፣ቤት እንስሳት እስከመሸጥ ወይም እስከመበደር በሚያደርስ ሁኔታ ላይ ሲገኝ ነው፡፡

ዓምድ 46:-ቤተሰቡ ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ የኑሮ ሁኔታውን የሚያናጋ አደጋ/ችግር ማለትም በመጠይቁ ዓምድ 44 ከታች የተዘረዘሩት የችግር/አደጋ አይነቶች ደርሶበት/አጋጥሞት እንደነበር ወይም እንዳልነበረ ለማወቅ እያንዳንዱ የተዘረዘሩት አደጋዎች/ችግሮች እየጠቀሱ በመጠየቅ ዓምድ 46 ፣አጋጥሞኝ ነበር፣ ለሚለው አደጋ/ችግር በአደጋው/በችግሩ ትይዩ ባለው ስፍራ ውስጥ ነበር ተብሎ ኮድ 1 ሲሞላ አላጋጠመኝም ብሎ ካለ ደግሞ በአደጋው/ችግሩ ትይዩ የለም ተብሎ ኮድ 2 ባለው ስፍራ ውስጥ ይሞላል፡፡

ምሳሌ:- አንድ ገበሬ የእርሻ ሰብሉን ውርጭና በረዶ ቢመታበት ነገር ግን ቤተሰቡ ይህ ሰብል በውርጭና በረዶ በመመታቱ ምክንያት ምንም አይነት የኑሮ መናጋት/ችግር ካላጋጠመው "ውርጭና በረዶ " በሚለው ትይዩ በዓምድ 46 "የለም" ተብሎ ኮድ "2" ይሞላል፡፡ ነገር ግን በ "ውርጭና በረዶ" የሰብል ውድመቱ ከፍተኛ ሆኖ ቤተሰቡን በጣም የጎዳው ከሆነ ነበር ተብሎ ኮድ"1" ይመዘገባል፡፡ ስለዚህ የጉዳቱን መጠን ከመልስ ሰጪው በጥልቀት ጠይቆ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ለሌሎችም ችግሮች ተመሳሳይ አጠያየቅ መከተል ያስፈልጋል፡፡

<u>የኑሮ ሁኔታውን የሚያናጋ ችግር/አደጋ ዓይነቶች ዝርዝር</u>

- ድርቅ
- ከመጠን ያለፈ ዝናብ ጐርፍ
- የአፈር መታጠብ
- ውርጭና በረዶ
- በተባይና በሰብል በሽታ/ከመታጨዱ በፊት/
- የተከማቸ እህል በበሽታ/በተባይ በመጠቃት

- እንስሳት በበሽታ/በተባይ በመጠቃታቸው
- የምርት ግብዐት ዕጥረት
- የዋጋ ንረትና ማሻቀብ (የምርት ግብዐት)
- ከፍተኛ በሆነ የምርት ውድቀት
- የባል ሞት
- የሚስት ሞት
- የሌላ አባል ሞት
- የባል ህመም
- የሚስት ህመም
- የሌላ አባል ህመም
- ፍቺ /መለያየት/ወጥቶ መቅረት

ዓምድ 47:-በእነዚህ ችግሮች/አደጋዎች በከፍተኛ ደረጃ/ ክፉኛ የተጠቁበትን 2 ዋና ዋና ዓመታት በደረጃ ቅደም ተከተል ቢገልጹልን ? (በዓምድ 47 ነበር ብሎ ለመለሱአቸውችግሮች ብቻ )

ይህ ዓምድ የሚመለከታቸው በዓምድ 47 ባለፉት 2 ዓመታት የቤተሰቡን የኑሮ ሁኔታ የሚያናጋ አደጋ/ችግር አጋጥሞት ተከስቶ ነበር ብለው ከመለሱአቸው ችግሮች መሃከል በየትኞቹ 2 ዓመታት በ1ኛ ደረጃ፣በ2ኛ ደረጃ፣ እንደተከሰቱ ዓመተ ምህረቱ የሚገለጽበት ነው:: በዚህ ዓምድ ቤተሰቡ በዓምድ 53 ቤተሰቡ ለጠቀሰው ችግር ካለፉት 2 ዓመታት እጅግ በጣም ከፍተኛ በሆነ ደረጃ ክፉኛ የተጠቃበት ዓመተ ምህረት በ1ኛ ደረጃ ፤ ከፍተኛ አደጋ/ችግር የአጋጠመበት ዓመተ ምህረት በ2ኛ ደረጃ፤ የሚመዘገብበት ነው:: በዓምድ 46 በተሞላለት አደጋ /ችግር ትይዩ ቤተሰቡ የአደጋውን/ችግሩን የጥቃት ደረጃ ቢያንስ ላለፉት 2 ዓመታት ማስታወስ ይችላል ተብሎ ስለሚገመት የሚሰጠውን መልስ በጥንቃቄ በማገናዘብ እንዲያነጻጸር ዕድል በመስጠት የሚሰጠውን መልስ በጥንቃቄ መሙላት ያስፈልጋል::

ዓምድ 48:-ባለፉት 2 ዓመታት ውስጥ በዓምድ 44 የተጠቀሱት አደጋ/ችግሮች የሚከተሉትን አስከትለው ነበር? (ዋና ዋና የሆኑትን ሶስት ብቻ በቅደምተከተል /በደረጃ ይጥቀሱ )

ቤተሰቡ በዓምድ 44 የተዘረዘሩት አደጋዎች/ችግሮች ባለፉት 2 ዓመታት ውስጥ እንዳጋጠመው የተከሰቱትን ክስተቶች ከታች ከተሰጡት አማራጮች እንዳጋጠመው/እንዳላጋጠመው በዝርዝር በመጠየቅ የሚሰጠውን መልስ በቅደምተከተል/በደረጃ በ1ኛ ደረጃ፤በ2ኛ ደረጃ፤ እንደተከሰቱ በዓምድ 47 በተዘረዘረው የአደጋ/ የችግር ቅደምተከተል/ደረጃ ዓመተ ምህረት መሰረት የክስተቱ ኮድ ይሞላል፡፡

ማሳሰቢያ፡- አንድ ችግር/አደጋ ተደጋገመ የሚባለው በአንድ ወቅት ተከስቶ በተለያዱ ዘዴዎች ከተፈታ በኋላ እንደገና በድጋሚ ከተከሰተ ነው፡፡

| ክስተት | ኮድ |
|---|---|
| የምርት መገልገያዎች ጥፋት | =1 |
| የቤተሰብ ገቢ መቀነስ | =2 |
| የቤተሰብ የምግብ ፍጆታ መቀነስ | =3 |
| የግል ንብረት ጥፋትና የገቢ መቀነስ | =4 |
| የንብረት ጥፋትና ፍጆታ በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ | =5 |
| የቤተሰብ ገቢና የምግብ ፍጆታ መቀነስ | =6 |
| የንብረትና ጥፋት፤የገቢና የምግብ ፍጆታመቀነስ | =7 |
| ሌሎች ያልተጠቀሱ ጉዳቶች | =8 |

ክፍል5ለ፡-ያለፉት አምስት ዓመታት ሲያስቡ በከፍተኛ ደረጃ ኑሮዎን ያናጉ ሶስት ችግሮች የትኞቹ ናቸው? በቅደምተከተል ከዓመተ ምህረቱ ጋር ቢገልጹልን?(በዓምድ 45 ያለውን ኮድተጠቀም)

ዓምድ 49-54፡-ከላይ በዓምድ 44 የቤተሰቡን የኑሮ ሁኔታ የሚያናጉ አደጋ/ችግሮች በዓምድ 45 በ 3 ዲጂት ኮድ ተዘርዝረዋል ፡፡ ቤተሰቡ ካለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ የኑሮ ሁኔታውን በከፍተኛ ደረጃ ያናጉና ያጋጠሙ 3ዋና ችግሮች/አደጋዎች በዓምድ 45 በተሰጠው ኮድ መሰረት ዓመተ ምህረቱ እየተጠቀሰ በደረጃ ቅደምተከተላቸው የሚጻፉበት ነው፡፡

በመጀመሪያ ካለፉት 2 ዓመታት ውስጥ በዓምድ 44 ከተዘረዘሩት የቤተሰቡን ኑሮ ሁኔታ ካናጉ አደጋ/ችግሮችመሀከል በየትኞቹ 3 ዋና የኑሮ ሁኔታውን በከፍተኛ ደረጃ ያናጉና ያጋጠሙ ችግሮች/አደጋዎች ቤተሰቡ መጠቃቱ ይጠየቃል፡፡ እነዚህን ችግሮቹ እንደከፍተኛነታቸው ቅደምተከተል/ ደረጃ

መሰረት በ1ኛ ደረጃ በዓምድ 49 ፣2ኛ ደረጃ በዓምድ 51፣ 3ኛ ደረጃ በዓምድ 53 ለይቶ በመጻፍ የተከሰቱበትን ዓመተ ምህረትደግሞ በዓምድ 50፣52ና ዓምድ 54 በተሰጠው ባዶ ስፍራ ይሞላል:: በዚህ ዓምድ ቤተሰቡ በዓምድ 48 ለተጠቀሰው ችግር ካለፉት 2 ዓመታት እጅግ በጣም ከፍተኛ በሆነ ደረጃ ክፉኛ የተጠቃበት ችግር በ1ኛ ደረጃ ፣ በከፍተኛ ደረጃ የተጠቃበት ችግር በ2ኛ ደረጃ፣ መጠነኛ አደጋ/ችግር የአስከተለውን ችግር ደግሞ በ3ኛ ደረጃ ለይቶ እንዲገልጽልን በተለያየ ጊዜ የተከሰቱ ሁኔታዎችን በማስታወስ እንዲያገናዝብ ዕድል መስጠት ያስፈልጋል:: ቤተሰቡ የአደጋውን/ችግሩን የጥቃት ደረጃ ቢያንስ ላለፉት 2 ዓመታት ማስታወስ ይችላል ተብሎ ስለሚገመት የሚሰጠውን መልስ በጥንቃቄ በማገናዘብ እንዲያነጻጽር ዕድል በመስጠት የሚሰጠውን መልስ በጥንቃቄ መሙላት አስፈላጊ ነው::

**ክፍል6 :- በእህልና በከብት ላይ ስለደረሰ ጥፋትና ጉዳት/ባለፉት 12 ወራት ብቻ/**

ሀገራችን የኣላት የግብርና ምርት በ ዝናብ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ በዚህ ምክንያት ባለፉት 12 ወራት በሰብልና በከብት ላይ ስለ ደረሰ ጥፋትና ጉዳት በዝርዝር በመጠየቅ የሚመዘገብበት ነው ::

ቤተሰቡ መሬት ይዞታ አለው ብለን ለዚህ ጥናት የምንወስደው በግልም ሆነ በኪራይ /በደባልነት በማንኛውም መልኩ የያዘውንና እየተጠቀመበት ያለውን መሬት ነው::በዚህ ክፍል የክረምት ዝናብን ተጠቅመው በአምናው የክረምት ወቅት በሰብላቸው ላይ በዕድገቱና በአጨዳ ወቅት የደረሰውን ጉዳት በተመለከተ በመኸር ወቅት ለአመረቱና ቋሚ ሰብል ለአሏቸው ቤተሰቦች የሚቀርብ ጥያቄ ነው::

ቋሚ ሰብል የሚያመርቱ ቤተሰቦች የሚጠየቁት ያለፈውን የመጨረሻ ምርት እስካገኙበት ጊዜ ያለውን ዋናውን የዝናብ ወቅት በተመለከተ ሲሆን ሰብሉ ሳያቋርጥ በተከታታይ ምርት ከሰጠ በክረምት ወቅት ያለውን የመጨረሻ አጠቃላይ የዕድገቱን ሁኔታ አስመልክቶየደረሰውን ጥፋት ለመገመገም የሚጠየቅበት ይሆናል::

ለተሰጡት መልሶች ስለ ደረሰው ጥፋት በበለጠ መግለጽ ወይም ማብራራት ከአስፈለገ የጥያቄ ቁጥሩን በመጥቀስ ከመጠይቁ ጀርባ አስተያየት መፃፍ ይቻላል::

**ዓምድ 55:- የክረምት ዝናብ ለዘሩት ሰብል ያስፈልጋልን?**

**ኮድ**

| | |
|---|---|
| አዎ | =1 |
| የለም | =2 - *(መልሱ የለም ከሆነ ወደ ዓምድ 61 ይለፍ)* |
| በጣም አስፈላጊአይደለም | =3 |

ከጥናቱ ቀን ወደ ኋላ ላለፉት 12 ወራት የቤተሰቡ ሃላፊ ለዘሩት ሰብል የክረምት ዝናብ ተፈላጊነትን ለማወቅ የሚጠየቅ ሲሆን አዎ በጣም ያስፈልጋል ብለው የሚሉ ከሆነ ለመልስ በተሰጠው ስፍራ "አዎ" ተብሎ ተጽፎ ለኮድ በተሰጠው ስፍራ ደግሞ ኮድ "1 " ይሞላል።ምንም አያስፈልግም ብለው ካሉ "የለም" ተብሎ ተጽፎ ለኮድ በተሰጠው ስፍራ ደግሞ ኮድ "2 " ተሞልቶ ወደ ዓምድ 61 የሚታለፍ ሲሆን በመጠኑ ያስፈልጋል ያን ያህል ግን በጣም አስፈላጊ አይደለም ብለው ከመለሱ በዓምዱ ስር በተሰጠው ስፍራ "በጣምአስፈላጊ አይደለም " የሚለው ተጽፎ ለኮድ በተሰጠው ስፍራ ደግሞ ኮድ "3 " ይሞላል።

**ዓምድ 56:- በታቀደው ጊዜ የክረምት ዝናብ ዘንቧልን?**

በዓምድ 55 ዝናብ ያስፈልጋል አዎ ወይም በጣም አስፈላጊ አይደለም በመጠኑ ብለው ከመለሱ በዚህ ዓምድ ባለፉት 12 ወራት የክረምት ዝናብ ይዘንባል ተብሎ በተጠበቀበትና በተፈለገው ጊዜ መዝነብ አለመዝነቡን የቤተሰቡ ሃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በትክክለኛው ጊዜ ዘንቧል ብለው ከአሉ ኮድ "1 " በጣም ዘግይቷል ከአሉ ኮድ "2 " በጣም ቀድሞ ነው የዘነበው ብለው ካሉ ደግሞ ኮድ "3 " ለመልስ በተሰጠው ስፍራ ይጻፋል።

**ኮድ**

| | |
|---|---|
| በትክክለኛው ጊዜ | =1 |
| በጣም ዘግይቶ | =2 |
| በጣም ቀድሞ | =3 |

**ዓምድ 57- በክረምቱ መጀመሪያ በእርሻ መሬቱ ላይ በቂ ዝናብ ዘንቦ ነበር?**

በክረምቱ መጀመሪያ ቤተሰቡ በነበረው የእርሻ መሬት ላይ በቂ ዝናብ መዝነቡን ወይም አለመዝነቡን የቤተሰቡ ሃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በቂ ዝናብ

መዝነቡን ከገለጹ ኮድ "1 " በጣም ብዙ ዝናብ ዘንቦ ነበር ብለው ከአሉ ኮድ "2 " በጣም ትንሽ ነው የዘነበው ብለው ካሉ ደግሞ ኮድ "3 " ለመልስ በተሰጠው ስፍራ ይጻፋል::

**ኮድ**

| | |
|---|---|
| በቂ | =1 |
| በጣም ብዙ | =2 |
| በጣም ትንሽ | =3 |

**ዓምድ 58:- በዕድገቱ ወቅት የእርሻ መሬቱ በቂ ዝናብ አግኝቶ ነበርን?**

በዕድገቱ ወቅት ቤተሰቡ በነበረው የእርሻ መሬት ላይ በቂ ዝናብ አግኝቶ ወይም አለአገኘ እንደሆነየቤተሰቡ ሃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በቂ ዝናብ ማግኘቱን ከገለጹ ኮድ "1 " በጣም ብዙ ዝናብ አግኝቶ ነበር ብለው ከአሉ ኮድ "2 " በጣም ትንሽ ዝናብ አግኝቷል ብለው ካሉ ደግሞ ኮድ "3 " ለመልስ በተሰጠው ስፍራ ይጻፋል::

**ኮድ**

| | |
|---|---|
| በቂ | =1 |
| በጣም ብዙ | =2 |
| በጣም ትንሽ | =3 |

**ዓምድ 59:- በትክክለኛ ወቅትና ጊዜ የክረምቱ ዝናብ ቆሞአልን?**

በዚህ ዓምድ ባለፉት 12 ወራት የክረምት ዝናብ በትክክለኛ ወቅትና ጊዜ መቆሙንና አለመቆሙን የቤተሰቡ ሃላፊ ተጠይቀው የሰጡት መልስ በትክክለኛው ጊዜ ቆሞአል ብለው ከአሉ ኮድ "1 " በጣም ዘግይቷል ከአሉ ኮድ "2 " ቀደም ብሎ ቆሞአል ብለው ካሉ ደግሞ ኮድ "3 " ለመልስ በተሰጠው ስፍራ ይጻፋል::

**ኮድ**

| | |
|---|---|
| በትክክለኛው ጊዜ | =1 |
| ዘግይቶ | =2 |

ቀደም ብሎ ቆሞአል =3

ዓምድ 60:-. በአዝመራ ወቅት ዘንቦ ነበር?

እህል በሚታጨድበት የአዝመራ ወቅት ዝናብ መዝነቡን ወይም አለመዝነቡ ተጠይቆ ዘንቦ ነበር ካሉ በተሰጠው ስፍራ "አዎ" ተብሎ ተጽፎ ለኮድ በተሰጠው ስፍራ ደግሞ ኮድ "1 " ይሞላል::የለም አልዘነበም ብለው ካሉ ደግሞ "የለም" ተብሎ ተጽፎ ለኮድ በተሰጠው ስፍራ ደግሞ ኮድ "2 " ይሞላል::

ኮድ

አዎ =1

የለም =2

ዓምድ 61:- ሰብልዎ ከዚህ በታች ባሉት ችግሮች ተጠቅቶ ነበር?

ኮድ

አዎ =1

የለም =2

በዚህ ዓምድ ባለፉት 12 ወራት ከታች የተዘረዘሩት የችግር/አደጋ አይነቶች በሰብሉ ላይ ደርሶበት/አጋጥሞት እንደነበር ወይም እንዳልነበረ ለማወቅ እያንዳንዱ የተዘረዘሩት አደጋዎች/ችግሮች እየጠቀሱ በመጠየቅ ፤አጋጥሞ/ተጠቅቶ ነበር፤ ለሚለው አደጋ/ችግር በአደጋው/በችግሩ ትይዩ ባለው ስፍራ ውስጥ "አዎ"ተብሎ ተጽፎ ለኮድ በተሰጠው ስፍራ ደግሞ ኮድ "1 " ተብሎ ኮድ 1 ሲሞላ አላጋጠመም ብሎ ካለ ደግሞ በአደጋው/ችግሩ ትይዩ የለም ተብሎ "የለም" ተብሎ ተጽፎ ለኮድ በተሰጠው ስፍራ ደግሞ ኮድ "2 " ይሞላል ::

የችግር/አደጋ አይነቶች

- ዝቅተኛ የአየር ፀባይ/ውርጭ
- አውሎ ነፋስ/ማዕበል
- ጎርፍ/ደራሽ ውሃ/የተቋጠረ ውሃ
- የሰብል በሽታ
- በተባይ
- በከብት መበላት/መረጋገጥ

- በወፍና ሌሎች አራዊት መበላት
- በአረም መበላሸት

**ዓምድ 62:-** **በክረምት ወቅት ከታች ባሉት ችግሮች ምክንያት የሰብል ጉዳት ደርሶ ነበር?**

**ኮድ**

አዎ =1

የለም =2

በዚህ ዓምድ በክረምት ወቅት ከታች የተዘረዘሩት የችግር አይነቶች በሰብሉ ላይ ደርሶበት/አጋጥሞት እንደነበር ወይም እንዳልነበረ ለማወቅ እያንዳንዱ የተዘረዘሩት ችግሮችን እየጠቀሱ በመጠየቅ ፤አጋጥሞ ደርሶ ከነበረ፤በችግሩ ትይዩ ባለው ስፍራ ውስጥ "አዎ"ተብሎ ተጽፎ ለኮድ በተሰጠው ስፍራ ደግሞ ኮድ "1 "ሲሞላ ሳጋጠመም/አልደረሰም ብሎ ካለ ደግሞ በችግሩ ትይዩ "የለም" ተብሎ ተጽፎ ለኮድ በተሰጠው ስፍራ ደግሞ ኮድ "2 " ይሞላል ::

**የችግር/አደጋ አይነቶች**

- የእርሻ በሬ በወቀቱ አለመኖር /አለማግኘት
- ገበሬው/ የቤተሰቡ አባላት በጠና ታመው ለመሥራት አለመቻል
- በወቅቱ ሌላ ሠራተኛከውጭ ማግኘት ባለመቻሉ

**ዓምድ 63:-** **ባለፉት 12 ወራት የቤትእንስሳት በነዚህ ችግሮች ተጠቅተውነበር?**

**ኮድ**

በመጠኑ =1

በከፍተኛ ደረጃ =2

የለም =3

በዚህ ዓምድ ባለፉት 12 ወራት ከታች የተዘረዘሩት የችግር አይነቶች በቤት እንስሳት ላይ ደርሶ/አጋጥሞ እንደነበር ወይም እንዳልነበረ ለማወቅ ለእያንዳንዱ ከታች የተዘረዘሩት ችግሮችን እየጠቀሱ በመጠየቅ ፤አጋጥሞ ደርሶ ከነበረ፤በችግሩ ትይዩ ባለው ስፍራ ውስጥ የችግሩን ክስተትና አስከፊነት ደረጃ

መረጃ ሰጭው አገናዝቦ በሚሰጠው መልስ መሰረት መጠነኛ መሆኑን ከገለጸ "በመጠኑ" ተብሎ ተጽፎ ለኮድ በተሰጠው ስፍራ ደግሞ ኮድ "1 " ይሞላል ። በከፍተኛ ደረጃ ተጠቅተው ወይም ደርሶ ከነበረ " በከፍተኛ ደረጃ " ተብሎ ተጽፎ ለኮድ በተሰጠው ስፍራ ደግሞ ኮድ "2 "ሲሞላ አላጋጠመም/አልደረሰም ብሎ ካለ ደግሞ በችግሩ ትይዩ "የለም" ተብሎ ተጽፎ ለኮድ በተሰጠው ስፍራ ኮድ "3 " ይሞላል ።

<u>የችግር/አደጋ አይነቶች</u>

- በመጠጥ ውሃ ዕጦት
- በገንዲ የከብት በሽታ
- የግጦሽ መሬት ዕጦት
- በሌሎች የእንስሳት በሽታዎች

<u>ክፍል 7:- ቤተሰቡ ስለ ድህነትና ደህንነቱ ያለው ግንዛቤ፤</u>

<u>ዓምድ 64:-.የቤተሰቡን አጠቃላይ ሁኔታ (በሀብት ደረጃ) ሲያስቡ እንዴት ይገልጹታል?</u>

በዚህ ዓምድ የቤተሰቡን ሃላፊ በጥናቱ ወቅት/ ያለውን የቤተሰቡን አጠቃላይ ሁኔታ ማለትም በሀብት ደረጃ ያለውን ሁኔታ በመጠየቅ ከታች የተገለጹትን የማነጻጸሪያ አማራጮች በመጠቀም ይሞላል። ይኸውም ቤተሰቡ በአጠቃላይ የኑሮ ሁኔታው ባለው ሀብት (ባለው አጠቃላይ ገቢና ቋሚንብረት፤የአመጋገብ፤አለባበስ፤----.ወ.ዘ.ተ) በጣም ሀብታም ከሆነ ኮድ "1 "በመጠኑ ሀብታም ከሆነ ኮድ "2 "የሚሞላ ሲሆን ከመሃከለኛ ደረጃ በላይ ሆኖ በቂ መተዳደሪያ ኖሮት ራሱን ማስተዳድር የሚችልና በምቹ ኔታ ላይ የአለ ከሆነ ኮድ "3 "በማንኛውም ደረጃ ሲታይ ራሱን ማስተዳድር የሚችል ነው ተብሎ ሲገመት ደግሞ ኮድ "4 "ይሞላለታል። በመጠኑ ደሀና በቂ መተዳደሪያ የሌለው ከሆነ ኮድ "5 " ለራሱ በቂ መተዳደሪያ የሌለው፤ ራሱን እየተቸገረ የሚያስተዳድር ፤ ድሀ ከሚባሉት ደረጃ የሚመደብ ከሆነ ኮድ "6 " በጣም ከተቸገሩት፤ ራሱን ማስተዳድር የማይችል፤ መተዳደሪያ የሌለውና የመጨረሻ ደሀ ከሆነ ደግሞ ኮድ" 7 " በዓምዱ ሥር ባለው ክፍት ቦታ ይሞላለታል። ቤተሰቡ ያልተመሰረተና የቤተሰብን ትርጉም በሚያሟላ መልኩ የልተደራጀ ከሆነ ደግሞ ስለ ማይመለከተው ኮድ "8" ይሞላል።

**<u>ኮድ</u>**

በጣም ሀብታም =1

ሀብታም =2

በምቹ ሁኔታ =3

ራሱን ማስተዳደር የሚችል =4

በቂ መተዳደሪያ የለውም =5

ደሀ =6

የመጨረሻ ደሀ =7

የማይመለከተው =8

ዓምድ 65:- ቤተሰብን ከሌሎች በመንደር ውስጥ ካሉ ቤተሰቦች ጋር ሲያነጻጽሩ እንዴት ይገልጹታል?

በዚህ ዓምድ የቤተሰቡን ሃላፊ አሁን/በጥናቱ ወቅት/ ያለውን የቤተሰቡን የኑሮ ሁኔታ ከሌሎች በመንደር ውስጥ ካሉ ቤተሰቦች ጋር እንዲያነፃፅር በመጠየቅ ከታች የተገለጹትን የማነጻጸሪያ አማራጮች በመጠቀም የታየው ለውጥ ይሞላል:: ይኸውም ቤተሰቡ በአጠቃላይ የኑሮ ሁኔታው (ባለው ገቢና ንብረት፤የአመጋገብ፤አለባበስ፤----.ወ.ዘ.ተ) እጅግ በጣም ሀብታም ከሆነ ኮድ 1 በመጠኑ ሀብታም ከሆነ ኮድ 2 የሚሞላ ሲሆን ከመሃከለኛ ደረጃ በላይ ሆኖ ከአብዛኞዎቹ የተሻለ ከሆነ ኮድ 3 በመሃከለኛ ደረጃ ናቸው ከሚባሉት የሚመደብ ከሆነ ደግሞ ኮድ 4 ይሞላለታል:: በመጠኑ ደሀ ከአብዛኛዎቹ ባነሰ ደረጃ የሚገመት ከሆነ ኮድ 5 ራሱን እየተቸገረ የሚያስተዳድር ከሆነና ድሀ ከሚባሉት ደረጃ የሚመደብ ከሆነ ኮድ 6 በጣም ከተቸገሩት፤ ራሱን ማስተዳድር የማይችልና የመጨረሻ ደሀ ከሆነ ደግሞ ኮድ 7 በዓምዱ ሥር ባለው ክፍት ቦታ ይሞላለታል::

ኮድ

በጣም ሀብታም =1

ከሀብታሞች አንዱ =2

ከብዙዎቹ የተሻለ ነው =3

ከመሃከለኛ ደረጃ =4

ከብዙዎቹ ባነሰ ደረጃ/በመጠኑደሀ =5

ድሀ ከሚባሉት መሃከል =6

የመጨረሻ ድሀ =7

**ዓምድ 66 :-ቤተሰቡ ለድንገተኛ አደጋ 100 ብር ማግኘት ቢፈልግ በሳምንት ውስጥ ማግኘት ይችላል ?**

**ኮድ**

አዎ =1

የለም =2 (*መልሱ የለም ከሆነ ወደ ዓምድ 68 ዕለፍ*)

ቤተሰቡ በጥናቱ ወቅት ያልተጠበቀ ችግር /ድንገተኛ አደጋ ቢያጋጥመው በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ 100 ብር ማግኘት ይችል ወይም አይችል እንደሆነ በመጠየቅ እችላለሁ ካለ "አዎ " የሚለው በዓምዱ ስር ተመዝግቦ ኮድ "1 " አልችልም ካለ ደግሞ "የለም" የሚለው በዓምዱ ተመዝግቦ ኮድ "2 " በ ዓምድ ሥር በተሰጠው ክፍት ቦታ ተሞልቶ ወደ ዓምድ 68 ይታለፋል፡፡

**ዓምድ 67 :-ይህንን 100 ብር እንዴት ማግኘት ይችላል?**

በዓምድ 66 ቤተሰቡ ያልተጠበቀ ችግር ቢገጠምኝ 100 ብር በአንድ ሣምንት ውስጥ ማግኘት እችላለሁ ብሎ ኮድ 1 ከተሞላለት በዚህ ዓምድ ቤተሰቡ በቅድሚያ/በዋንኛነት ከየት ማግኘት እንደሚችል በመጠየቅ ቤተሰቡ የሚሰጠውን መልስ ከተዘረዘሩት አማራጭ መልሶች ጋር በማገናዘብ ትክክለኛውን መልስና ተገቢውን ኮድ በዓምዱ ስር በተተወው ባዶ ቦታ መፃፍና መሙላት ይገባል፡፡

**ኮድ**

ከእንስሳት ሽያጭ =1

ከሌሎች የእርሻናየመሥሪያ ዕቃች ሽያጭ =2

ከቤት ዕቃች ሽያጭ =3

ከራሳቸው ገንዘብ =4

ከቁጠባ/እቁብ/እድር/ =5

በብድር =6

ከእህል ሽያጭ =7

ከሌላ =8

**ዓምድ 68:-የአለፈውን ወር የቤተሰቡን ምግብፍጆታ በተመለከተ ከነዚህ የትኛው ትክክል ነው?**

ለጥናቱ የተመረጠው ቤተሰብ የአለፈው ወር የቤተሰቡ የምግብ ፍጆታ ምን እንደሚመስል ተጠይቆ ቤተሰቡ የሚሰጠውን መልስ ከታች ከተሰጡት አማራጮች ጋር በማገናዘብና ትክክለኛውን በመምረጥ በዓምዱ ስር መዝግቦ ተገቢውን ኮድ መሙላት ያስፈልጋል:: ቤተሰቡ ያልተመሰረተና የቤተሰብን ትርጉም በሚያሟላ መልኩ ያልተደራጀ ከሆነ ደግሞ ስለ ማይመለከተው ኮድ "4" ይሞላል::

| | ኮድ |
|---|---|
| ለቤተሰቡ ፍላጎት ከበቂ በታች | =1 |
| ለቤተሰቡ ፍላጎት በቂ ነው | =2 |
| ለቤተሰቡ ፍላጎት ከበቂ በላይነው | =3 |
| አይመለከተውም | =4 |

**ዓምድ 69 :-ቤተሰቡን መኖሪያ ቤት በተመለከተ ከነዚህ የትኛው ትክክል ነው?**

ለጥናቱ የተመረጠው ቤተሰብ የራሱ ወይም በማንኛውም መልክ የያዘውንና እየኖረበት ያለውን - መኖሪያ ቤት ሁኔታ ምን እንደሚመስል ተጠይቆ ቤተሰቡ የሚሰጠውን መልስ ከታች ከተሰጡት አማራጮች ጋር በማገናዘብና ትክክለኛውን በመምረጥ በዓምዱ ስር መዝግቦ ተገቢውን ኮድ መሙላት ያስፈልጋል:: ቤተሰቡ ያልተመሰረተና የቤተሰብን ትርጉም በሚያሟላ መልኩ የልተደራጀ ከሆነ በማንኛ ውም መልክ መኖሪያ ቤት የሌለው ደግሞ ስለ ማይመለከተው ኮድ "4" ይሞላል::

| | ኮድ |
|---|---|
| ለቤተሰቡ ፍላጐት ከበቂ በታች | =1 |
| በቂ ነው | =2 |
| ከበቂ በላይ | =3 |

አይመለከተውም =4

ዓምድ 70፡-ቤተሰቡን የልብስ ሁኔታበተመለከተ ከነዚህ የትኛው ትክክል ነው?

ለጥናቱ የተመረጠው ቤተሰብ በጥናቱ ወቅት ያለውን የቤተሰቡን የልብስ ሁኔታ ምን እንደሚመስል ተጠይቆ ቤተሰቡ የሚሰጠውን መልስ ከታች ከተሰጡት አማራጮች ጋር በማገናዘብና ትክክለኛውን በመምረጥ በዓምዱ ስር መዝግቦ ተገቢዉን ኮድ መጻፍና መሙላት ያስፈልጋል፡፡ ቤተሰቡ ያልተመሰረተና የቤተሰብን ትርጉም በሚያሟላ መልኩ የልተደራጀ ከሆነ ደግሞ ስለ ማይመለከተው ኮድ "4'" ይሞላል፡፡

| | ኮድ |
|---|---|
| ለቤተሰቡ ፍላጐት ከበቂ በታች | =1 |
| በቂ ነው | =2 |
| ከበቂ በላይ | =3 |
| አይመለከተውም | =4 |

ዓምድ 71፡-ቤተሰቡን ያለፈውን ወር ጠቅላላ ገቢ በተመለከተ የትኛው ትክክል ነው?

ያለፈው ወር የቤተሰቡን ጠቅላላ ገቢ ሁኔታ ምን እንደሚመስል ተጠይቆ የሚሰጠውን መልስ ከተዘረዘሩት አማራጮች ጋር በማገናዘብና ተስማሚውን በመምረጥ በዓምዱ ስር ተመዝግቦ ተገቢው ኮድ ይሞላል፡፡

| | ኮድ |
|---|---|
| ለቤተሰቡ ፍላጐት ከበቂ በታች | =1 |
| በቂ ነው | =2 |
| ከበቂ በላይ | =3 |
| አይመለከተውም | =4 |

ዓምድ 72፡-ቤተሰቡ አሁን ያለበትን የኑሮ ሁኔታ ካለፈው ዓመትጋር እንዴት ያነጻጽሩታል?

ለጥናቱ የተመረጠው ቤተሰቡ በጥናቱ ወቅት ያለውን አጠቃላይ የኑሮ ሁኔታ ከአምናው ጋር በማነፃፀር ኑሮውና አቅሙ ምን እንደሚመስል ተጠይቆ ቤተሰቡ የሚሰጠውን መልስ ከተሠጡት አማራጮች ጋር በማገናዘብና ትክክለኛውን በመምረጥ በዓምዱ ስር መዝግቦ ተገቢው ኮድ ይጻፋል፡፡

**ኮድ**

| | |
|---|---|
| አሁን በጣም የተሻለ ነው | =1 |
| አሁን ትንሽ የተሻለ ነው | =2 |
| ለውጥ የለውም | =3 |
| አሁን ትንሽ ብሶአል | =4 |
| አሁን በጣም ብሶአል | =5 |
| አላውቅም | =6 |

**ዓምድ 73፡-ከሁለት ዓመት በፊት የቤተሰቡ ሁኔታ በምን ደረጃ ነበር?**

በዚህ ዓምድ የቤተሰቡን ሃላፊ አሁን/በጥናቱ ወቅት/ ያለውን የቤተሰቡን የኑሮ ሁኔታ ከሁለት ዓመት በፊት ከነበረው ጋር እንዲያነፃፅር ተጠይቆ ቤተሰቡ የሚሰጠውን መልስ ከታች ከተሠጡት አማራጮች ጋር በማገናዘብና ትክክለኛ ውን በመምረጥ የታየውን ለውጥ/ በምን ደረጃ ላይ እንዳለ ይሞላል፡፡ ይኸውም ቤተሰቡ አሁን ያለው አጠቃላይ የኑሮ ሁኔታ (ባለው ገቢና ንብረት፤የአመጋገብ፤አለባበስ፤----.ወ.ዘ.ተ) ከሁለት ዓመት በፊት ከነበረው ጋር ሲነፃፀር በጣም ሀብታም ከሆነ ኮድ "1 "በመጠኑ ሀብታም ከሆነ ኮድ "2 "የሚሞላ ሲሆን ከመሃከለኛ ደረጃ በላይ ሆኖ በቂ መተዳደሪያ ኖሮት ራሱን ማስተዳድር የሚችልና በምቹ ኔታ ላይ የአለ ከሆነ ኮድ "3 "በማንኛውም ደረጃ ሲታይ ራሱን ማስተዳድር የሚችል ነው ተብሎ ሲገመት ደግሞ ኮድ "4 "ይሞላለታል፡፡ በመጠኑ ደሀና በቂ መተዳደሪያ የሌለው ከሆነ ኮድ "5" ለራሱ በቂ መተዳደሪያ የሌለው፤ ራሱን እየተቸገረ የሚያስተዳድር ፤ ድሀ ከሚባሉት ደረጃ የሚመደብ ከሆነ ኮድ "6 " በጣም ከተቸገሩት፤ ራሱን ማስተዳድር የማይችል፤ መተዳደሪያ የሌለውና የመጨረሻ ደሀ ከሆነ ደግሞ ኮድ" 7 " በዓምዱ ሥር ባለው ክፍት ቦታ ይሞላለታል፡፡ ቤተሰቡ ያልተመሰረተና የቤተሰብን ትርጉም በሚያሟላ መልኩ የልተደራጀ ከሆነ ደግሞ ስለ ማይመለከተው ኮድ "8'" ይሞላል፡፡

**ኮድ**

በጣም ሀብታም =1

ሀብታም =2

በምቹ ሁኔታ =3

ራሱን ማስተዳደር የሚችል =4

በቂ መተዳደሪያ የለውም =5

ደሀ =6

የመጨረሻ ደሀ =7

የማይመለከተው =8

ዓምድ 74:-ከሁለት ዓመት በፊት ካለው ጋር ሲያነጻጽሩ ለምን የቤተሰቡ ኑሮ ሁኔታ ተቀየረ?

ለጥናቱ የተመረጠው ቤተሰቡ በጥናቱ ወቅት ያለው አጠቃላይ የኑሮ ሁኔታ /ጠቅላላ አቅም ከሁለት ዓመት በፊት ካለው ጋር በማነፃፀር የቤተሰቡ ኑሮና የአቅም ሁኔታ (በውድቀትም ሆነ በዕድገት ) ለምን እንደተቀየረ ያሳየውን ለውጥ እያገናዘበ በምክንያትነት የሚሰጠውን ዋና /መልስ ከተሠጡት አማራጮች ጋር በማገናዘብና ትክክለኛውን በመምረጥ በዓምዱ ስር መዝግቦ ተገቢው ኮድ ይጻፋል፡፡

የኑሮ ሁኔታ ድህነትና ደህንነት ለውጥ መግለጫ **ኮድ**

የተገኘው ምርት ጥሩ ስለነበረ =1

አዳዲስ የአስተራረስ ዘዴች በሥራ ላይ በማዋል =2

አዳዲስ ሰብሎችን በማብቀል/በመዝራት =3

አዳዲስ ሥራች በመፍጠር/በንግድ =4

የግል ሥራ ወይም ንግድ ትርፍ አስገኝቷል =5

ብዙ የቤት እንስሳት ስለአሉኝ =6

በጥሩ ቤት ስለምንኖር =7

የተሰበሰበ ሌላ ንብረት መኖር =8

ሰብልና የቤት እንስሳቶች በጥሩ ሁኔታ በመያዛቸው =9

የግልሥራዬን በጥሩ ሁኔታ በመሥራቴ =10

ጠንክረንስለሠራን =11

ጉዳቶችን በፀጋ በመቀበል = 12

ትንሽ በመጠጣት = 13

ባለቤቴ ትንሽ ስለምትጠጣ = 14

ብዙልጆች ስለአሉኝ = 15

ባለቤቴ ጠንክራ ስለምትሠራ = 16

ጊዜው በጣም በመሻሻሉ = 17

በተገኘው ጥሩ ዕድል = 18

በእግዚአብሔር ዕርዳታ = 19

የተሻለ የቤተሰባዊነት ትስስርና ግንኙነት መኖር = 20

በምርት ጥበቃ የጋራ መረዳጃ፣ ፕሮጀክት በመሥራት፣

ደመወዝ በማግኘታቸው = 21

በቀጥታ የሚላክላቸው ገንዘብ ዕቃ በማግኘታቸው በመቀበላቸው = 22

የተገኘው ምርትበጣም ዝቅተኛ አናሳ ነበር = 31

አዳዲስ ሰብሎችን በመዝራት/አዳዲስ የአስተራረስዘዴች

ሞክረን የተፈለገውን ውጤት አላስገኘም = 32

የግል ሥራዬም አልተሳካልኝም/አልተዋጣልኝም = 33

ያሉኝ የቤትእንስሳት አናሳ መሆን = 34

ቤታችን እንደበፊቱ ቆንጆ አይደለም = 35

ያሉኝ ሌላ ንብረት ጥቂት ስለሆነ = 36

ሰብሌን በደንብ መያዝአለመቻሌ = 37

ሥራዬን በደንብ መሥራት ባለመቻሌ = 38

ሰነፍ ስለነበርኩ = 39

የሚደርሰው ችግር በመፍራትና ሀላፊነት ለመውሰድ

አለመፈለግ = 40

ትንሽ/ብዙ በመጠጣት = 41

| | |
|---|---|
| ባለቤቴ በጣም ስለምትጠጣ | = 42 |
| ባለቤቴ ታማ ነበር | = 43 |
| ባለቤቴ ሞታ ነበር | = 44 |
| የልጆችህመም/ሞት | = 45 |
| ልጆች ጥለው በመሄዳቸው | = 46 |
| ባለቤቴ ሰነፍ ነች | = 47 |
| ጊዜው መጥፎ ነበር | = 48 |
| መጥፎ ዕድል ስለገጠመን | = 49 |
| እግዚአብሔር አልረዳንም | = 50 |
| የደከመ የቤተሰብ ትስስር | = 51 |
| ሌላ | = 52 |

**ዓምድ 75:-በጠቅላላው የቤተሰቡን ኑሮ ሁኔታ ሲገልጹ እንዴት ይገልጹታል?**

ቤተሰቡ በጥናቱ ወቅት አጠቃላይ የኑሮ ሁኔታን ለመናር አስፈላጊ ከሆነው ፍጆታና ገቢ አኳያ የቤተሰቡን ፍላጎት ጠብቆ ለመኖር በአለው ሁኔታ አጠቃላይ መልኩ ምን እንደሚመስል ተጠይቆ የሚሰጠውን መልስ ከተዘረዘሩት አማራጮች ጋር በማገናዘብና ተስማሚውን በመምረጥ በዓምዱ ስር ተመዝግቦ ተገቢው ኮድ ይሞላል።

| | ኮድ |
|---|---|
| በጥሩ ሁኔታ ላይ ነው | =1 |
| ደህና ነው | =2 |
| ኑሮን ለማሸነፍ (በመፍጨርጨር ላይ) ነው | =3 |
| የቤተሰቡን ፍላጎት አይሸፍንም/ችግሩን ሊወጣ አልቻለም | =4 |

ጥያቄ 76: ለጥናቱ የተመረጠ ቤተሰብ ስለአንድ ሰው ስኬታማነት በተመለከተ የሚቀርብ ጥያቄ ሲሆን ይኸውም ከሚከተሉት በየትኛው ሀሳብ (በአብዛኛው) ይስማማሉ ተብሎ በመጠየቅ የሚከተሉትን እንደአማራጭ በማቅረብ ቤተሰቡ የመረጠውን በኮድ መስጫ ኮዱን የሞላል።

ሀ) እያንዳንዱ ሰው በህይወት ስኬታማ ለመሆን/ለአለመሆን በራሱ የሚወሰን ነው = 1 ወይም እያንዳንዱ ሰው በህይወት ስኬታማ ለመሆን/ለአለመሆን እጣ-ፈንታ ነው = 2

ለ) ስኬታማ ለመሆን ሰው ጠንክሮ መስራት አለበት/ያስፈልገዋል = 1 ወይም
ስኬታማ ለመሆን ሰው እድለኛ መሆን አለበት = 2

**ጥያቄ 77:** ለጥናቱ የተመረጠው ቤተሰብ በወረዳው ውስጥ ስኬታማ ሆነዋል ለሚላቸው ሰዎች በሚመለከት የሚጠየቅ ሲሆን ይኸውም በወረዳው ውስጥ ስኬታማ ሆነዋል ስለሚሏቸው ሶስት ሰዎች ስማቸውን ሳይጠቅሱ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥያቄዎችን ማቅረብ ይገባል::

ሀ) የመጀመሪያ ስኬታማ ሰው፣ ሁለተኛው ስኬታማ ሰውና ሶስተኛው ስኬታማ ሰው እድሜው/ዋ ስንት እደሆነ በሙሉ ዓመት ተጠይቆ በቅደም ተከተል ይሞላል::

ለ) የመጀመሪያ ስኬታማ ሰው፣ ሁለተኛው ስኬታማ ሰውና ሶስተኛው ስኬታማ ሰው ፆታ በመጠየቅ ፆታው ወንድ ከሆነ ኮድ = 1፣ ሴት ከሆነች ኮድ = 2 ተጠይቆ በቅደም ተከተል ኮዱን ይሞላል::

ሐ) የሶስቱ ስኬታማ ሰዎች በቅደም ተከተል የአፍ መፍቻ ቋንቋ ምንድነው?
<u>ማሳሰቢያ:</u> ቋንቋን በተመለከተ በዕዝል 3 የተሰጡትን ተጠቀም::

መ) የመጀመሪያ ስኬታማ ሰው፣ ሁለተኛው ስኬታማ ሰውና ሶስተኛው ስኬታማ ሰው ሀይማኖት በመጠየቅ የሚከተሉትን ተስማሚ ኮዶችን መጠቀም ያስፈልጋል::

1 = ኦርቶዶክስ (ተዋህዶ፣ ቅባት፣ ፀጋ)
2 = ፕሮቴስታንት (ሰባት ቀን አድቬንቲስት፣ ጴንጤቆስጤ፣ ሉተራን መንነኢየሱስ፣ ባፕቲስት፣ በነናይት፣ አንግሊካን፣ ፕረስፒተርያን፣ መሠረተ ክርስቶስ፣ ሙሉ ወንጌል፣ ቃለ ህይወት፣ ... ወዘተ)
3 = ካቶሊክ
4 = ሙስሊም (እስላም)
5 = ባህላዊ እምነት
6 = ሌላ (ለምሳሌ:- ጀሆቫ፣ብሃይ፣ ይሁዳ፣ ሂንዱ፣ ... ወዘተ)

ሠ) እነዚህ ስኬታማ ሰዎች በእርስዎ ቀበሌ ይኖራሉ?
አዎን = 1 የለም = 2

ረ) እነዚህ ስኬታማ ሰዎች በእርስዎ ሰፈር/መንደር ይኖራሉ?
አዎን = 1 የለም = 2

ሰ) እነዚህ ስኬታማ ሰዎች በምን መልኩ ነው ስኬታማ የሆኑት?
1 = ሀብት በማፍራታቸው፣ 2 = በጣም የተከበሩ በመሆናቸው፣
3 = ልጆቻቸውን ትምህርት ቤት በመላካቸው፣ 4 = ጠንካራና ኀበዝ በመሆናቸው፣ 5 = በስራቸው ውጤታማ ስለሆኑ፣ 6 = ሌላ (ይገለጽ)
(ዋና ዋና የሆኑትን የሶስቱን ኮድ በቅደም ተከተል ሙላ)

ሸ) በአምስት አመት ውስጥ እርስዎ እንደነዚህ ሰዎች ስኬታማ እሆናለሁ ብለው ያስባሉ? አዎን = 1፣ የለም = 2 መልሱ አዎን ከሆነ ወደ ጥያቄ በ ይለፉ።

ቀ) ከላይ ለጥያቄ «ሸ» መልሹ የለም ከሆነ ምክንያቱ ምንድነው?

1 = የገንዘብ እጦት፣ 2 = የእውቀት ማነስ፣ 3 = የመረጃ እጦት፣
4 = አለመድፈር፣ 5 = ተነሳሽነት አለመኖር፣ 6 = ሌላ (ይገለጽ)

በ) በእርስዎ አመለካከት በዚህ መንደር በአምስት ዓመት ውስጥ ምን ህል ሰዎች ስኬታማ ይሄናሉ ብለው ያስባሉ?

1 = ማንም አይሆንም፣ 2 = ሩብ ያህሉ ይሆናሉ፣ 3 = ግማሹን፣
4 = ሶስት አራተኛው፣ 5 = ሁሉም

ተ) በህይወትዎ ስኬታማ እንዳይሆኑ እንቅፋት ሊሆኑብኝ ይችላሉ የሚሏቸውን ሶስት ዋና ምክንቶች ይግለጹ።

1 = የገንዘብ እጦት፣ 2 = የእውቀት ማነስ፣ 3 = የመረጃ እጦት፣
4 = አለመድፈር፣ 5 = ተነሳሽነት አለመኖር፣ 6 = ሌላ (ይገለጽ)

ቸ) በተመሳሳይ መልኩ በክልሉ ሶስት ስኬታማ ሰዎች ቢጠየቁ እነዚሁ ሰዎች ናቸው ብለው የመልሳሉ?

አዎን = 1፣ የለም = 2

# ቅጽ2000/9

## ዕድሜያቸው ከ 6 ወር እስከ 7 ዓመት የሆኑ ሕፃናት ክብደትና ቁመት ልኬቶሽ

### ቃለ መጠይቅና ልኬቶሽ የተካሄደበት ቀን፦

ልኬቶሽ የተካሄደበት_ቀን ሲሞላ ከ 1-30 ያሉትን ቁጥሮች በመጠቀም ሚሞላ ሲሆን ለወር ደግሞ በዓምድ 10 ውስጥ የተገለጹትን ለወራት የተሰጡትን ኮዶች በመጠቀም የሚሞላ ይሆናል፡፡

### ክፍል 1፡

የተመረጠው ቤተሰብ አካባቢ መለያ

ይህ ክፍል ከቅጽ ምዋ 2000/1 ክፍል 1 የሚወራረስ ነው፡፡

## ክፍል 2፡

## ዕድሜያቸው ከ 6 ወር እስከ 7 ዓመት የሆኑ ሕፃናት ክብደት ልኬቶሽ

ዕድሜያቸው ከ6 ወር እስከ 7 ዓመት የሆኑ ሕጻናት የሚባሉት ጥናቱ በተካሄደበት ቀን ዕድሜያቸው ከ 5 ወር ከ29 ቀን በላይና ከ6 ዓመት ከ 11 ወር ከ29 ቀን የሚደርሱ ሕጻናትን ያጠቃልላል፡፡

### ዓምድ 8 ፦ የቤተሰብ አባል ተ/ቁጥር

በዚህ ዓምድ የሚመዘገበው ከቅጽ ምዋ 2000/2 ክፍል 2 ዓምድ 8 ለእያንዳንዱ መደበኛ አባል ከተሰጠው ተራ ቁጥር መካከል ዕድሜአቸው ዕድሜያቸው ከ አምስት ወር ከ29 ቀን በላይና ከስድስት ዓመት ከ አስራ አንድ ወር ከ ሃያ ዘጠኝ ቀን በታች የሆኑ ሕጻናትን ከቅጽ ምዋ 2000/2 ክፍል 2 ዓምድ 11 ዕድሜያቸውን በማየት የሕፃኑን ተራቁጥር ከዓምድ 8 በቀጥታ በማስተላለፍ ነው፡፡ ሕፃናት በቅፅ ምዋ 2000/2 ላይ ሲመዘገቡ ተከታታይ በሆነ መንገድ ላይሆን ስለሚችል ወደዚህ ዓምድ ሲተላለፍም ቀድሞ የተመዘገበው ተራ ቁጥር ምንም ዓይነት ማስተካከያ ሳይደረግበት እንዳለ በመገልበጥ ይሆናል፡፡

**ለምሳሌ፦** በቅጽምዋ 2000/2 ክፍል 2 ዓምድ 8 ለሕፃኑ የተሰጠው ተራ ቁጥር "06" ቢሆን በቅጽ ምዋ 2000/9 ክፍል 2 ዓምድ 8 ለሕፃኑ የሚሰጠው ተራ ቁጥር "06" ይሆናል ማለት ነው፡፡

## ዓምድ 9፦ የ ሕፃናት ስም ዝርዝር፦

ይህ ዓምድ ከቅጽ ምዋ 2000/2 ክፍል 2 ዓምድ 8 ወደ ቅጽ ምዋ 2000/9 ክፍል 2 ዓምድ 8ተራ ቁጥሩ ለተላለፈለት ሕፃን ሙሉ ስም ከ ቅጽ ምዋ- 2000/2 ክፍል 2 ዓምድ 9 የሚገለበጥ ነው።በዚህወቅትየሕፃናቱ ስምና ተ/ቁ እንደይሳሳት ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡

## ዓምድ 10፦ ሕፃኑ የተወለደበት ቀን /ወር/ ዓ.ም

ይህ ዓምድ ሕፃኑ የተወለደበት ቀን፣ወርና ዓመተ ምህረት ተጠይቆ የሚመዘገብበት ነው።ይህ ዓምድ በቅጽ ምዋ 2002/2 ከተሰጠው ዕድሜ ጋር ተገናዝቦ የሚሞላ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ቀን የሚሞላው ከ 1-30 ባሉት የቀን ቁጥሮች በመጠቀም ሲሆን ወር ደግሞ የሚሞላው በዐምዱ ውስጥ በተገለጹትና በተሰጡት የወር ኮዶች መሰረት ይሆናል።ዓመተምህረቱ በኢትዮጵያ አቆጣጠር የሚሞላ ሲሆን የአሙቱን የመጨረሻ ሁለት ቁጥሮች በመውሰድ ይመዘገባል።ወር ሲሞላ ለወራት የተሰጡትን የሚከተሉትን ኮዶች በመጠቀም ይሞላል ።

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| መስከረም | = 1 | ጥቅምት | = 2 | ሕዳር | = 3 | ታህሳስ | = 4 |
| ጥር | = 5 | የካቲት | = 6 | መጋቢት | = 7 | ሚያዚያ | = 8 |
| ግንቦት | = 9 | ሰኔ | = 10 | ሐምሌ | = 11 | ነሃሴ | = 12 |
| ጳጉሜ | = 13 | | | | | | |

ምሣሌ፦ የተመዘገበው ሕጻን ጥቅምት 18 ቀን 1996 ዓ.ም የተወለደ ቢሆን ለቀን በተሰጠው ስፍራ 18 ለወር በተሰጠው ቦታ ደግሞ ለጥቅምት የተሰጠው ኮድ **2** ሲሞላ ዓመተ ምህረቱ ደግሞ **96** ሆኖይሞላል ማለት ነው። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በቅጽምዋ 2002/2ክፍል 2 የተመዘገበው ዕድሜ በሙሉ ዓመት ስለሆነና ለዚህ ጥናት የሚፈለገው የሕፃኑ የተወለደበት ቀን ወርና ዐመተ ምህረት ተለይቶ የሚሞላ ስለሆነ የቤተሰቡ ሃላፊ፣ እናት/አሳዳጊ በትክክል አስታውሰው እንዲነግሩን ያስፈልጋል። ስለሆነም ትክክለኛውን የልደት ጊዜ ለማስታወስ እንዲቻል መረጃ ሰብሳቢው መልስ ሰጭው በአከባቢው ከተደረጉ ታዋቂና ታሪካዊ ድርጊቶች ጋር በማገናዘብና በማስታወስ ትክክለኛውን የልደት ዘመን ለማግኘት ለመሙላት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል ። ሆኖም ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በቅጽምዋ2002/2 ክፍል2 ላይ በዓመት የተሰጠውን ዕድሜ 4 ዓመት ቢሆን

ይህ 4 ዓመት ማለት 4X12 =48 ወራት ማለት ብቻ ላይሆን ይችላል:: ለምሳሌ በቅጽ ምቀ 2002/2ዕድሜ በሙሉ ዓመት ስለሚሞላ እስከ 11 ወራት ያህል ልዩነት ሊኖረው ይችላል:: በመሆኑም የልደት ቀን፤ወርና ዓ.ም ሲሞላ በጥንቃቄ ተጠይቆ መሞላት የአለበትና ልዩነት ሊኖር እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል::

**ዓምድ 11:-የሕጻኑ የልደት( የተወለደበት ቀን/ወር/ ዓ.ም )መረጃ የተገኘው ከየት ነው ?**

በዚህ ዓምድ ከላይ የተገኘው የልደት መረጃ ከየት እንደተገኘ ለማረጋገጥ የቀረበ ጥያቄ ሲሆን የበተሰቡ ሃላፊ/እናት/አሳዳጊ ጥያቄውን ተጠይቀው ሲመልሱ እንዴትና ከየት አግኝተው እንደ መለሱ ለማወቅ የቀረበ ነው:: ስለሆነም ከታች ከተገለጹት አማራጮች የትኛው እንደሆነ በማረጋገጥ የተገኘ ውን መልስና ኮድ በሕጻኑ አቅጣጫ ያለውን መስመር ተከትሎ በተዘጋጀው ቦታ መሙላት ያስፈልጋል::

| | ኮድ |
|---|---|
| ከልደት ምስክር ወረቀት | = 1 |
| ከጥምቀት ማስረጃ | = 2 |
| ከክሊኒክ ካርድ ላይ | = 3 |
| ከቤት ከተቀመጠ ማስረጃ | = 4 |
| በአካባቢ ከተፈጸሙ ታዋቂ ደርጊቶች ጋር በማገናዘብ | = 5 |
| እናትየው/አሳዳጊው በማስታወስ | = 6 |
| ከሌሎች ሰዎች በማሰባሰብ | = 7 |
| ከሌላ | = 8 |

**ዓምድ 12:የሕፃኑ ቁመት በሳንቲሜትር (ዝርዝር የአለካክ መመሪያው በዕዝል 1 ተሰጥቷል)**

ለዚሁ ተግባር በተሰጠው የቁመት መለኪያ በመጠቀም የህፃኑ ቁመት በሳንቲ ሜትር በመለካት በዓምዱ ስር በተሰጠው ክፍት ቦታ የሕጻኑን ስም መስመር ተከትሎ ይሞላል :: በልክቶሽ ጊዜ ሊከሰት ሚችለውን ስህተት ለመቀነስ መረጃ ሰበሳቢው ልክቶሹ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ <u>ሁለት ጊዜ</u> ለክቶ ትክክለኛ የሆነውን ቁጥር አረጋግጦ መሙላት ይኖርበታል :: የህፃናት ቁመት ሲለካ በሚከተለው መንገድ መሆን ይገባዋል::

ለማንኛውም ዕድሜው ሁለት ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆነ ሕፃን የቁመት መለኪያውን ከግድግዳ አስጠግቶ ጠፍጣፋ መሬት ላይ ማቆምና ከዚያም ሕፃኑን ማቆሚያው ላይ እግሩን ገጥሞ ቀና አድርጎ በማቆም ኗድሮው የሕፃኑን አናት እስኪነካ ከላይ ቀስ ብሎ ጫን በማለት ቁመቱን በትክክል በሙሉ ሴንቲ ሜትር አንብቦ መመዝገብ ያስፈልጋል:: ሕፃኑ ቀጥ ብሎ ሲቆም ተረከዙ ራሱና መላ ቁመቱ ሳይነብጥ ሜትሩ የተለጠፈበትን እንጨት መንካት ያለባቸው ከመሆናቸው በላይ እግሮቹ ፍፁም ቀጥ ያሉ ወይም የተገተሩ መሆን ሲገባቸው የሕፃኑ እይታ ፊት ለፊት ቀጥ ያለ መሆን አለበት:: ይህም ማለት ሕፃኑ መሬት ሳያይ ወይም ወደ ላይ ሳያንጋጥጥ ማለት ነው::

ለማንኛውም ዕድሜው ከሁለት ዓመት በታች ለሆነ ሕፃን ደግሞ ቁመቱ የሚለካው የቁመት መለኪያውን ወጣ ገባ በሌለበት ጠፍጣፋና ጠንካራ ከሆነ ወለልና ጠረጴዛ ...ወዘተ ላይ በማስተኛት ነው:: ከዚያም ሕፃኑን በመደገፍ በመለኪያ መሳሪያው ላይ የሕፃኑን ጭንቅላት /አናት ወደ መለኪያ መሳሪያው መቆሚያ በማድረግ ቀጥ አድርጎ በጀርባው በማስተኛት ነው:: ልኬቱም ከመነበቡ በፊት የሕፃኑ አናት የመለኪያ መሳሪያውን መቆሚያ በሚገባ ማስነካትና የሕፃኑን ጆሮ ግንድ በእጅ ደግፎ ሕፃኑ በሚገባ ወደ ላይ መመልከቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በመጨረሻ የሕፃኑን እግሮች አንድ ላይ ገጥሞ ቀጥ ብለው የተዘረጉ መሆናቸውን ጉልበቱን በእጅ በመጫንና እግሮቹን በእጅ በመግጠም ጭምር ካረጋገጡ በኋላ ኗድሮው መሀል ለመሀል ማስረገጥና ትክክለኛውን መመዝገብ ነው:: ርዝመቱ በሚመዘገብበት ጊዜ የሕፃኑ ቁመት ከ100 ሳንቲ ሜትር ያነሰ ከሆነ በቁጥሩ በስተግራ "0" በመጨመር ባለ ሶስት ዲጂት ቁጥር አድርጎ መፃፍ አለበት::

**ለምሳሌ**፦ የህፃኑ ቁመት 89 ሳንቲ ሜትር ቢሆን ከግራ ወደ ቀኝ ከሚገኘው የመጀመሪያ ኮለም "0" በቀጣዩና በመሃከለኛው ኮለም ደግሞ "8" በመጨረሻው ኮለም ደግሞ "9" በመሙላት "089" በመፃፍ ይሞላል ማለት ነው::

## ዓምድ 13: የቁመት ልክቶሽ የተለካው እንዴት ነው?

ከላይ በተሰጠው መመሪያ መሰረት ለማንኛውም ዕድሜው ሁለት ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆነ ሕፃን የቁመት መለኪያውን ከግድግዳ አስጠግቶ ጠፍጣፋ መሬት ላይ በማቆም ሕፃኑ ቀጥ ብሎ ሲቆም ተረከዙ ራሱና መላ ቁመቱ ሳይነብጥ **ቆሞ** መለካት ያለበት ሲሆን ዕድሜው ከሁለት ዓመት በታች ለሆነ ሕፃን ደግሞ ቁመቱ የሚለካው የቁመት መለኪያውን ወጣ ገባ በሌለበት ጠፍጣፋና ጠንካራ ከሆነ ወለልና ጠረጴዛ ...ወዘተ ላይ በጀርባው በማስተኛት **ተጋድመው** መሆን ይኖርበታል:: ስለሆነም በመመሪያው መሰረት መፈጸሙን ለማጋገጥ ይህ ጥያቄ ቀርቧል::በዚህም መሰረት በተዘጋጀው የመልስ ስፍራ ቆመው ተለክተው ከሆነ "ቆመው" የሚል መልስ ተጽፎ ለኮድ በተሰጠው ስፍራ ደግሞ "1" ይሞላል "ተጋድመው" ከሆነ ደግሞ ይኸው ተጽፎ ኮድ"2" ይሞላል ማለት ነው::

ኮድ

ቆመው = 1

ተጋድመው = 2

## ዓምድ 14: የሕፃኑ ክብደት (በኪሎ ግራም)

ዕድሜያቸው ከ 5 ወር ከ29 ቀን በላይና ከ6 ዓመት ከ 11 ወር ከ29 ቀን በታች የሆኑ ሕጻናትን በሙሉ ለዚህ ጥናት በተዘጋጀው ሚዛን በመመዘን የሚገኘው ክብደት በኪሎ ግራም በተሰጡት የመልስ ስፍራዎች ይሞላሉ::በምዘና ወቅት ሊኖር የሚችለውን ስህተት ለመቀነስና ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ምዘናውን ሁለት ጊዜ በማድረግ ትክለኛውን ክብደት መሙላት ያስፈልጋል:: በኪሎ የተገኘው ውጤት ለኪሎ በተሰጠው ቦታ በሁለት ዲጂት ስለሚሞላ ከ10 ኪሎ ያነሱ ክብደቶች ሁሉ በቁጥሩ በስተግራ ማለትም ከግራ በመጀመሪያው ክፍት ቦታ "0" በመጨመር ባለ ሁለት ዲጂት ቁጥር ሆኖ መፃፍ አለበት:: በግራም የተገኘው ቁጥር በሁለት ወይም በሶስት ዲጂት ቢሆን የሂሳብ የማጠጋጋትን ደንብ ተከትሎ ወደ አንድ ዲጂት በማጠጋጋት ለግራም በተሰጠው ባዶ ቦታ የተጠጋጋው አንድ ቁጥር ይሞላል::.

ለምሣሌ:- የህጻኑ ክብደት 6ኪሎ ከ0560 ግራም ቢሆን ከኪሎ በኋላ የሚገኙትን ቁጥሮች ወደ ኪሎ ግራም ለመቀየር 1 ኪሎ ግራም =1000 ግራም ስለሆነ የተገኘውን ቁጥር ለ 1000 በማካፈል ወደ ኪሎግራም ቀይሮ የተገኘውን ቁጥር በማጠጋጋት በመልስ መስጫው ቦታ የሚሞላው **06 .6** ኪሎ ግራም ይሆናል ማለት ነው::

## ዓምድ 15: በልኬቶሽ ወቅት ሕጻኑ ሲመዘን የለበሰው ልብስ ምን ዓይነት ነበር?

በክብደት አለካክ ወቅት ትክክለኛውን ክብደት ለማግኘትና የአለውን ትክክለኛነት ለማመዛዘንና የነበረውን ሁኔታ ለማገናዘብ እንዲያስችል ይህ ጥያቄ ቀርቧል:: ስለሆነም በምዘናው ወቅት የሕጻኑ አለባበስ በምን ሁኔታ እንደነበር በማየትና በማገናዘብ ከታች ከተሰጡት አማራጮች መሀከል አንደኛው ተመርጦ ይሞላል:: በተሰጠው የመልስ ቦታ ከተሰጠው አማራጮች መሃከል የተገኘው መልስ በጽሁፍ ተገልጾ ተገቢው ኮድ መሞላት ይኖርበታል::

ኮድ

አለበሰም = 1

ቀላል ልብስ ለብሷል = 2

መጠነኛ ክብደት ያለው ልብስ ለብሷል = 3

ብዙ ልብስ ለብሷል = 4

# ዕዝል- 1

## ለ: የቁመትና የክብደት ልክቶሽ

ዕድሜያቸውከ6ወርእስከ7ዓመትየሆናቸው ሁሉም ሕፃናት መመዘንና መለካት ይኖርባቸዋል።የቁመትና የክብደት ልክቶሽ ራሱን የቻለ የሥራ ሂደት ሲሆን የሚከናወነውም መረጃ ሰብሳቢና አንድ ሌላ የቡድኑ አባል (ተቆጣጣሪው፣ አዲተሩ ወይም ሌላ መረጃ ሰብሳቢ) ይሆናል።የአለካኩ ሂደት በዚህ ክፍ

ል

መጨረሻ ላይ ቀርቧል።

**የመልስ ሰጭዎችንና የሕፃናትን የቁመትና የክብደት ልክቶሽ ለማካሄድ የቀረበ መመሪያ**

I. **ልክቶሹ ከመጀመሩ በፊት መወሰድ ያለባቸው ቅደም ተከተሎችና ጥንቃቄዎች፣**

ሀ. የቅደም ተከተሎች ጽንሰ ሃሳብ፣
እያንዳንዱ የልክቶሽ ተግባር በተወሰኑና በልክቶሹ ላይ በሚሳተፉ ሠራተኞች የሚካሄድ ይሆና ል። እነዚህም "ለኪ"፣ "ረዳት"፣ ... ወዘተ እየተባለ ስም ተሰጥቷቸዋል።

ለ. ሁለት የሰለጠኑ ሰዎች ያስፈልጋሉ፣

የሕፃናትን ቁመትና ክብደት ልክቶሽ ለማካሄድ ሁለት የሰለጠኑ ሰዎች ያስፈልጋሉ። ለ ኪው ሕፃኑን በመያዝ ልክቶሹን ያካሂዳል። ረዳቱ ሕፃኑን ለመያዝ የሚረዳ ሲሆን በተጨማሪ የልክቶሹን ውጤት ይመዘግባል። ያልሰለጠነ ረዳት (እንደ እናት፣ ወንድም ...ወዘተ) ከአለ የሰለጠነው ለኪ የልክቶሹን ውጤት በመጠይቁ ላይ መመዝገብ ይችላል። ረዳት ከሌለ አንድ ሰው ብቻ የልጁን ክብደት በመለካት መመዝገብ ይችላል።

ሐ. የመለኪያው ጣውላና የመለኪያው አቀማመጥ፣

የመለኪያው ጣውላና መለኪያው የሚቀመጡበትን ቦታ መምረጥ ያስፈልጋል። በቀን ጊዜ ከቤት ውጭ ሜዳ ላይ ልክቶሹን ማከናወን ጠቀሜታ ይኖረዋል። ቅዝቃዜ ከአለ፣ ዝና ብ ከሆነ ወይም ብዙ ሴቶች ተሰብስበው ግር ግር ከፈጠሩ ልክቶሹን በቤት ውስጥ ማከናወን ተገቢ ይሆናል። ያም ሆነ ልክቶሹ በሚካሄድበት ቦታ ይህ በቂ ብርሃን መኖሩን ማረጋገጥ ያ ስፈልጋል።

መ. የዕድሜን ሁኔታ ማጤን፣

ልክቶሹ ከማከናወኑ በፊት የልጁን ዕድሜ ማጤን ያስፈልጋል። የልጁ ዕድሜ ከሁለ ት ዓመት ያነሰ ከሆነ እርዝመቱን /እስተኝቶ/ መለካት ያስፈልጋል። የልጁ ዕድሜ ሁለት ዓ መትና ከዚያ በላይ ከሆነ ቁመቱን /አቁሞ/ መለካት ተገቢ ይሆናል። የልጁ ዕድሜ በትክክ ል የማይታወቅ ከሆነና ቁመቱ ከ85 ሳ.ሜ ያነሰ ከሆነ አስተኝቶ /ዕርዝመቱን/ መለካት የሚገ ባ ሲሆን ቁመቱ ደግሞ ከ85 ሳ.ሚና በላይ ከሆነ ቁመቱን (እንደቆመ) መለካት ተገቢ ይሆና ል።

ሠ. መመዘንና መለካት ያለበት መቼ ነው ፧

ልክቶሹ መከናዎን ያለበት የግለሰብ መጠይቁ ከተጠናቀቀ በኋላ ይሆናል፡፡ ይህም የሚጠቅመው ከቤተሰቡ አባላት ጋር አስቀድሞ ለመግባባት ነው፡፡ ወዲያውኑ ከቤተሰቡ እንደ ደረሱ ልክቶሽ ማካሄድ አለመግባባትን ሊፈጥር ስለሚችል ከዚህ ተግባር መቆጠብ ይገባል፡

ረ. በአንድ ጊዜ መለካት ያለበት አንድ ልጅ ብቻ ነው፤

በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ከአንድ በላይ ለጥናቱ ብቁ የሆኑ ልጆች ከአሉ በየተራ መለካት ይኖርባቸዋል፡፡ ሁሉንም ልጆች በአንድ ላይ መለካት አይቻልም፡፡ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ከአንድ በላይ ለጥናቱ ብቁ የሆኑ ሴቶች ከአሉ፤ የአንደኛዋ ሴት የራሷና የልጆቹ የክብደትና የቁመት ልክቶሽ ከተጠናቀቀ በኋላ የሌላኛዋን ሴት የረሷንና የልጆቿን ልክቶሽ ማከናወን ይገባል፡፡ በዚህ መልክ ከአልተከናወነ ግን የልክቶሽ ውጤቶች በስህተት በማይገባቸው ዓምዶች ላይ ሊመዘገቡ እንደሚችሉ መታወቅ አለበት፡፡ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ያሉ ልክቶሾች ከተጠናቀ በኋላ የመለኪያ መሣሪያዎቹ በሙሉ ወዲያውኑ ወደቦታቸው መመለስ ይኖርባቸዋል፡፡

ሰ. ልጁን መቆጣጠር፤

ልጁ ሲመዘን ወይም ሲለካ መቆጣጠር ተገቢ ነው የልጆች ጥንካሬና እንቅስቃሴ፤ (በጣም ሕፃን የሆኑትን ልጆች ጨምሮ) መናቅ የሌለበት ጉዳይ ነው፡፡ ልጆችን በምንይዝበት ጊዜ ጥንካሬና የተረጋጋ መንፈስ ይጠበቅብናል፡፡ የኛ የመረጋጋትና በራስ የመተማመን ስሜት በእናቶችና በሕፃናት ላይ የመረጋጋት ስሜት እንደሚያሳድር መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

የሕፃናት ልክቶሽ በሚካሄድበት ጊዜ ሕፃኑ እንዳይጠለፍ ወይም እንዳይወድቅ በጥንቃቄ መያዝና መቆጣጠር ያስፈልጋል፡፡ ሕፃኑን ለብቻው በመሣሪያው ላይ መተው ተገቢ ተግባር አይደለም፡፡

ሸ. ፍርሃትን ማስወገድ፤

የክብደትና የቁመት ልክቶሽ በሚካሄድበት ጊዜ ሕፃናትን መንካትና መያዝ የማይቀር ተግባር ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ሂደት ላይ የሚታየው መደበኛ የሆነ ፍርሃት በቃል ብቻ መረጃ በመሰብሰብ ሂደት ላይ ከሚታየው መደበኛ የሆነ ፍርሃት ጠንከር ያለ ይሆናል፡፡

ፍርሃትንና ጭንቀትን ለማስወገድና ተቃውሞን ለመቀነስ የአለካኩን ሂደት ለእናታቸው ማስረዳት የሚያስፈልግ ሲሆን፣ ለሕፃናት ደግሞ በጥቂቱ መግለጽ ተገቢ ይሆናል፡፡ የእናቶችን ወይም የሕፃናትን የፍርሃት ደረጃ በማጤን የልክቶሹ ተግባር መቆም ያለበት መሆኑን መወሰን ያስፈልጋል፡፡ ሕፃን ልጆች ብዙ ጊዜ አይተባበሩም፣ ያለቅሳሉ፤ ይረብሻሉ፤ ይማታሉ አንድ አንድ ጊዜ ድግሞ ይናከሳሉ፡፡ ሕፃኑ በከባድ ፍርሃት የተሞላ ከሆንና በተከታታይ ከባድ ልቅሶ የሚያሰማ ከሆነ ለማባበል መሞከር ያስፈልጋል፡፡ ወይም ልክቶሹ ከመካሄዱ በፊት ወደ እናቱ መለሶ በመስጠት ማረጋጋት ያስፈልጋል፡

የሚከተሉት ሁኔታዎች ከተከሰቱ ልጁ መመዘን ወይም መለካት የለበትም፡-

ሀ. እናቱ ከተቃወመ

ለ. ልጁ በጣም ከታመመ ወይም ከተረበሸ

ሐ. ልጁ አካለጎደሎ በመሆኑ የተነሳ ልክቶሹ ሥራ አስቸጋሪ ከሆነ ወይም የተሳሳተ ል ክቶሽ የሚሰጥ ከሆነ። ለመግባባት ያህል ልጁን በመለካትና ውጤቱን በማስፈር በመጠይቁ ላይ አካለጎደሎ መሆኑን ማስታወሻ መጻፍ ያስፈልጋል።

ቀ. የልክቶሹን ውጤት መመዘገብና በጥንቃቄ መያዝ፣

በክብደትና በቁመት ልክቶሽ ጊዜ በእጅ ያሉ ነገሮች በሙሉ መወገድ ይኖርባቸዋል። እስኪራብቶ በአፍ መያዝ፣ በፀጉር ላይ መሻጥ፣ በጡት አካባቢ መሻጥ ሕፃኑንም ሆነ በልክቶሹ ተግባር ላይ የተሰማራውን ሰው ከጉዳት ላይ ሊጥል ስለሚችል ማስወገድ ያስፈልጋል። እስ ኪራብቶ በምትጠቀምበት ጊዜ ወደ ቦታው መመለስ ያስፈልጋል ወይም በመጠይቁ ውስጥ ማስ ቀመጥ ይገባል። እረጅም ጥፍርና ሌሎች በሥራው ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ እንደ ቀለበት፣ ሰዓት ...ወዘተ የመሳሰሉትን አስቀድሞ ማስወገድ ያስፈልጋል።

በ. ለመሻሻል ጥረት ማድረግ፣

የመሻሻል ፍላጐት ያለው ሰው የተገለጹትን የአለካክ ቅደም ተከተሎች ጠንቅቆ በመ ተግበር ሊሻሻል ይችላል። የልክቶሹ ጥራትና ፍጥነት በልምድ የሚዳብር ይሆናል። የምትለ ካው የሴትና የሕፃናት ክብደትና ቁመት ቢሆንም እንደ ቀላል ነገር በመውሰድ ያለአግባብ በ ራስ መተማመን ተገቢ አይደለም። ሥራችንን ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ ከአልተገበርነው በ ቀላሉ ስህተት እንደምንሰራ መታወቅ አለበት። ማንኛውም ቅደም ተከተል ማለፍ ተገቢ አይ ደለም። ለምትሰራው ሥራ ሁሉ ትኩረት ይኑርህ።

II. **የቁመት ልክቶሽ ማጠቃለያ ቅደም ተከተል**

ሀ. **<u>የሕፃኑ ቁመት (ሥዕል 1)</u>**

1. **ለኪ ወይም ረዳት፡-** የመለኪያውን ጣውላ ጠንካራና ጠፍጣፋ በሆነ ግድግዳ፣ ጠረጴዛ፣ ዛፍ፣ ... ወዘተ ላይ አስቀምጥ። ጣውላው በትክክል የተቀመጠ መሆኑን አረጋግጥ።

2. **ለኪ ወይም ረዳት፡-** የልጁን ጫማ እንድታወልቅና በቁመቱ ልክቶሽ ላይ ችግር የሚያመመጣ ነገር ከአለው እንድ ታስተካከል እናቱን መጠይቅ። ልጁን ወደ መለኪያ ጣውላው እንድትወስደው መጠየቅና ከ ልጁ አጠገብ ቁጢጥ እንድትል (እረዳት ካልሆነች) አድርግ።

3. **ረዳት**፡- መጠይቁንና እስክራብቶውን መሬት ላይ አስቀምጥ (ቀስት 1)። በልጁ አካል ቀኝ በ ኩል ተንበርከክ (ቀስት 2)።

4. **ለኪ፡-** ለመንቀሳቀስ እንዲያመችህ በልጁ እካል የግራ አካል በኩል በቀኝ ጉልበትህ ተንበርከ ክ (ቀስት 3)።

5. **ረዳት**፡- ልጁ እግሮቹን በመግጠምና ጫማውን በትክክል እንዲረግጥ፣ በመለኪያ ጣውላው መሀል ላይ እንዲቆምና በመለከያ ጣውላው ላይ ወደኋላ ተጠግቶ እንዲቆም አድርግ። የቀኝ እጅህን ከልጁ ተረከዞች በላይ በአሉት የእግሮቹ አገዳ ላይ አስቀምጥ (ቀስት 4)፣ የግራ እጅህ ን ደግሞ ከልጁ ጉልበቶች በታች አስቀምጥ (ቀስት 5) እና ወደ መለኪያ ጣውላው ገፍተህ ያዘው የልጁ እግሮች ቀጥ ብለው የቆሙ መሆኑን፣ የእግሩ ተረከዝና ባቱ ወደ መለኪያ ጣው

ላው የሆኑ መሆኑን አረጋግጥ (ቀስት 6 እና 7)። የልጁን የጫማና የእግር አቀማመጥ እንደ ጨረስክ ለለኪው ተናገር።

6. **ለኪ:-** የልጁ እናት ከፊት ለፊቱ ተቀምጣ ከሆነ ልጁ ፊት ለፊት ወደ እናቱ እንዲመለከት ንገረው። የልጁ የዓይን እይታ መስመር ከመሬቱ ጋር የተስተካከለ መሆኑን አረጋግጥ (ቀስት 8)። የግራ እጅህን በመክፈት በልጁ አገጭ ላይ አስቀምጥ። ቀስ በቀስ ዝጋው (ቀስት 9)። የልጁን ጆሮና አፍ እንዳትሸፍን ተጠንቀቅ። የልጁ ትከሻዎች ቀጥ ብለው የተስተካከሉ መሆኑን (ቀስት 10)፣ እጆቹ በጐኑ በኩል ያሉ መሆኑን (ቀስት 11) እና ራሱ፣ የትከሻ የመጋጠሚያ አጥንቶችና መቀመጫዎቹ ወደ መለኪያ ጣውላው የተጠጉ መሆኑን (ቀስት 12፣ 13 እና 14) አረጋግጥ። በልጁ ራስ ላይ የምታርፈውን መለኪያ በልጁ አናት ላይ አሳርፍ። የልጁን ፀጉር የተጫንክ መሆንህን አረጋግጥ (ቀስት 15)።

7. **ለኪና ረዳት:-** የልጁን አቋቋም መርምር (ቀስት 1-15) አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ማንኛውም ተግባር በድጋሚ አስተካክል።

8. **ለኪ:-** የልጁ አቋቋም ትክክል ከሆነ ልክቶሹን ወደ 0.1 ሳሜ አጠጋግተህ በማንበብ ተናገር። ከልጁ እናት ላይ ያረፈውን መለኪያ፣ እና የግራ እጅህን ከአገጩ ላይ አስወግደህ ልክቶሹ ብሚመዘገብበት ጊዜ ልጁን ደግፍ።

9. **ረዳት:-** የልክቶሹን ውጤት ወዲያውኑ በመመዝገብ ለለኪው አሣይ። <u>ማስታወሻ</u>:- ረዳቱ ያልሰለጠነ ከሆነ ለኪው ውጤቱን መመዝገብ አለበት።

10. **ለኪ:-** የልክቶሹ ውጤት በመጠይቁ ላይ በትክክል የተመዘገበና የሚነበብ መሆኑን አረጋግጥ። ስሕተቶች ከአሉ እንዲያስተካክል ለረዳቱ መመሪያ ስጠው።

ለ. <u>**የልጁ እርዝመት**</u> (*ሥዕል* 2)

1. **ለኪ ወይም ረዳት:-** የመለኪያ ጣውላውን ጠንካራና ቀጥታ በሆነ ቦታ ላይ በመሬት ላይ፣ በወለል ላይ፣ በማይንቀሳቀስ ጠረጴዛ ላይ ...ወዘተ ላይ አስቀምጥ።

2. **ረዳት:-** መጠይቁንና እስክሪብቶውን መሬት ላይ፣ ወለል ላይ ወይም ጠረጴዛ ላይ አስቀምጥ (ቀስት 1)። መሬት ላይ ከሆነ ከጣውላው በስተጀርባ ከሥር ላይ በሁለቱ ጉልበትህ ተንበርከክ (ቀስት 2)።

3. **ለኪ:-** የልጁን እግር በቀኝ እጅህ ለመያዝ እንዲያመችህ በልጁ የቀኝ አካል በኩል ተንበርከክ (ቀስት 3)።

4. **ለኪና እረዳት:-** የእናትየዋን እርዳታ በመጠየቅ በሚከተለው መንገድ ልጁን በጣውላው ላይ ለማስተኛት ሞክር:-
<u>እረዳት</u>:- የልጁን ራስ የኋላ አካል በመደገፍ ቀስ በቀስ በጣውላው ላይ አስቀምጥ።
<u>ለኪ</u>:- የልጁን ዋናውን የሰውነት አካል በመያዝ ደግፈው።

5. **ለኪ ወይም ረዳት:-** እረዳት ካልሆነች በስተቀር በጣውላው ጀርባና ከልጁ ፊት ለፊት በመንበርከክ ልጁን እንድታረጋጋው እናቱን ጠይቅ።

6. **ረዳት**:- በልጁ ጆሮዎች አካባቢ በእጆችህ በመያዝ ልጁን ደግፍ (ቀስት 4):: እጆችህን ቀጥ በማድረግና በማመቻቸት (ቀስት 5) እና የልጁን ራስ ከጣውላው ላይ በማስቀመጥ የልጁ እ ይታ ቀጥታ ወደ ሰማይ እንዲሆን አድርግ:: የልጁ የእይታ መስመር በቀጥታ መሬትን በ90° ማቋረጥ ይኖርበታል:: ራስህን ከልጁ ራስ ትይዩ ላይ በማድረግ በቀጥታ የልጁን ዓይን ማየት ይኖርብሀል::

7. **ለኪ**:- ልጁ በጣውላው መሀል ላይ ቀጥ ብሎ የተኛ መሆኑን አረጋግጥ (ቀስት 7):: የግራ እጅህን በልጁ የእግር አገዳ (ከተረከዙ በላይ) ላይ ወይም በጉልበቶቹ ላይ አስቀምጥ (ቀስት 8 ):: ወደ ጣውላው ገፉ አድርገህ ያዝ:: በቀኝ እጅህ ከሜማው ስር ያለውን ጠፍጣፋ ቁራ ጭ ነገር ወደ ተረከዙ ገፍተህ ያዝ (ቀስት 9)::

8. **ለኪና ረዳት**:- የልጁ አቀማመጥ ትክክል መሆኑን አረጋግጥ:: አስፈላጊ ከሆነ ማንኛውንም የተከናወኑ ተግባራትን ድገም::

9. **ለኪ**:- የልጁ አቀማመጥ ትክክል ከሆነ ልክቶሹን ወደ 0.1 ሳሜ አጠጋግተህ በማንበብ ተና ገር:: በእግሩ ስር ያለውን ነገር አንሳ፣ ከልጁ የእግር አገዳ ወይም ጉልበቶቹ ላይ ያለውን የ ግራ እጅህን አንሳና ውጤቱ በሚመዘገብበት ጊዜ ልጁን ደግፍ::

10. **ረዳት**:- ወዲያውኑ የልጁን ራስ ልቀቅ፣ ውጤቱን መዝግብና ለለኪው አሣይ::
<u>ማስታወሻ</u>:- ረዳቱ ያልሰለጠነ ከሆነ ውጤቱን ለኪው መመዝገብ አለበት::

11. **ለኪ**:- ውጤቱ በመጠይቁ ላይ በትክክልና በሚለይ መልኩ መመዝገቡን አረጋግጥ:: ስህተ ት ከአለ እንዲያስተካክል ረዳቱን አግባባ::
<u>ማስታወሻ</u>:- ረዳቱ ያልሰለጠነ ከሆነ (ለምሣሌ እናት) በእርዝመት ልኩቶሹ ጊዜ ለኪው ረዳቱ ን የማገዝ ግዴታ አለበት::

**III. የክብደት ልክቶሽ ማጠቃለያ ቅደም ተከተል፣**

ሀ. <u>መሣሪያ</u>

1. <u>**ዲጂታል እስኬል (Digital Scale) (ዩኒሲኤፍ ኤሌክትሮኒክ እስኬል ወይም ዩኒእስኬል)**</u>:- ይህ መሣሪያ ልጆችና ትልልቅ ሰዎችን ለመመዘን ያገለግላል:: የመታጠቢያ ገንዳ የመሰለና ቁጥሮች ያሉበት መሣሪያ ነው: : እስኬሉ በ0.1 ኪ.ግ (0.2 ፓውንድ) የተስተካከለ ሲሆን ያለምንም የሂሳብ ስሌት በቀላሉ የልጁን ክብደት ለማንበብ የሚያስችል መሣሪያ ነው:: ዩኒ ስኬል በፀሐይ ብርሃን የሚሰራ ሲ ሆን የሚቀየሩ የባትሪ ድንጋዮች አያስፈልጉትም:: (ተጨማሪ መመሪያዎችን በዩኒስኬል ማስታ ወሻ ላይ ያለውን ተመልከት)::

2. <u>**ከእንጨት የተሰራ የድጋፍ ጣውላ ይህ ጣውላ**</u>:- ከመለኪያው ሥር የሚቀመጥና ከመለኪያው ጋር አብሮ መያዝ ያለበት ዕቃ ነው:: ይህ ጣውላ ከሌለህ የተስተካከለ ወለል ወይም መሬት ላይ ማስቀመጥ ይገባል ወይም የቁመት ልክቶሹን የላይኛው ክፍል መጠቀም ያስፈልጋል::

ለ. <u>**ለኪ**:- **የልክቶሹን ቅደም ተከተል ለመልስ ሰጭዋ ወይም ለእናቲቱ አስረዳት፣**</u>

1. ልጆቹን ለመለካት መመዘኛ መሣሪያ እንዳለህና ልጆቹ ሲለኩም በእናታቸው ተይዘው መሆኑ ን እንዳለበት ለሴትየዋ ገለፃ አድርግላት:: በተጨማሪም የመልስ ሰጭዋን ክብደት እንደምትለካ ግለጽላት:: ትልቅ ልጆች በሚዛኑ ላይ ቆመው መለካት እንደሚችሉ መታወቅ ይኖርበታል::

2. እናቲቱ ስስ የሆኑ ጨርቆችን እንድትለብስ ጠይቃት:: ወፍራም ጨርቅ ወይም ሌላ ማንኛ ውንም ከባድ ነገር ከሰውነቷ ላይ እንድታስወግድ ግለጽላት::

3. የልጁን ልብስ እንድታወልቅለት እናትየዋን ጠይቅ:: ሴትዮዋ ከተቃወመች በጣም ስስ የሆነች ትንሽ የውስጥ ሱሪ /ፖንት/ እንዲለብስ አድርግ:: ልጆች በጭራሽ ጌጣ ጌጥ ያለባቸው ልብ ሶች መልበስ የለባቸውም:: እናቲቱ ብርዱን የምትፈራ ከሆነ እስከሚመዘን ድረስ ማንኛውን ም ልብስ ወይም ብርድ ልብስ ለብሶ እንዲቆይ አድርግ::

4. ልጁን በሚዛኑ ላይ ለማስቀመጥ የሚመቻችን ቦታ አስክትይዝ ድረስ ልጁን ሌላ ሰው እንዲይዝላት ጠይቃት ወይም ራስህ ልጁን ያዝላትና እሷ ተመቻችታ ትቁም::

5. በመጀመሪያ እናቲቱ ከተለካች በኋላ በመቀጠል የመጨረሻ ትንሹ ልጅ፣ ከዚያም ቀጥሎ ያለው ትንሹ ልጅ፣ ...ወዘተ እንደሚለኩ ለእናቲቱ አስረዳ::

**ሐ. ለኪ:- ሚዛኑን ማዘጋጀት፣**

1. አየሩ በጣም ሞቃት ከሆነ ሚዛኑ በትክክል ላይሰራ ይችላል:: ስለዚህ ለማንበብ የሚያስችል በቂ ብርሃን እስካለ ድረስ ልክቶሹን ጥላ በአለበት ቦታ (በቤት ውስጥ) ማካሄድ ይገባል:: የእንጨት ድጋፉን ጠፍጣፋ በሆነ መሬት ላይ አስቀምጥ:: ማንኛውም ሰው ቢቆምበት የማይንቀሳቀስ መሆኑን ደግሞ አረጋግጥ::

2. ሚዛኑን በድጋፍ እንጨቱ ላይ አስቀምጥና በትክክል የተቀመጠ (ያልተጣመመ) መሆኑን አረጋግጥ::

3. ሚዛኑ በትክክል ያለተቀመጠ ከሆነ ወይም ሚዛኑና የሚደገፈው የእንጨት ድጋፍ በደንብ ያልተያያዙ ከሆነ የጣውላውን (የእንጨቱን) ቦታ በማዘዋወር ወይም በስሩ ድጋፍ በማስቀመጥ ችግሩ እንዲወገድ አድርግ::

4. ጣውላው በትክክል (Horizontal) የተቀመጠ፣ የተረጋጋ መሆኑንና የማይንቀሳቀስ መሆኑን አረጋግጥ:: ሚዛኑ ጠንካራና ጠፍጣፋ በሆነ ቦታ ላይ መቀመጥ ይኖርበታል:: ለስላሳና ያልተስተካከለ ቦታ በክብደት ልክቶሹ ላይ ስሕተት ያመጣል::

5. መጠይቁንና እስክሪብቶህን በእጅህ በመያዝ ተዘጋጅ::

**መ. ለኪ:- በራሳቸው ኃይል ከሚዛኑ ላይ መቆም የሚችሉ ሴቶንና ሕፃናትን ለካ**

1. በፀሐይ ብርሃን የሚሰራውን በትሪ ከአንድ ሰኮንድ ያነሰ ያሀል በመሸፈንና "ON" የሚለውን ቁልፍ በመንካት ሚዛኑን ክፈተው (በፀሐይ ብርሃን የሚሰራው ባተሪ ለረጅም ጊዜ ከተሸፈነ ሚዛኑ አይነሳም):: ሚዛኑ ውዲያውኑ እንደተነሳ "188.8" የሚል ያሳይና በመቀጠልም "0.0" የሚል ያሳያል:: "0.0" ሲያሳይ ሚዛኑ ለሥራ የተዘጋጀ መሆኑን ያመለክታል::

2. ሴትየዋ በሚዛኑ መሐል ላይ በፀጥታ እንድትቆም ጠይቃትና የሚዛኑ ቁጥሮች መቀያየር እስከ ያቆሙ ድረስ እንድትቆይ አድርግ:: በፀሐይ የሚሰራው ባተሪ በተለያዩ ነገሮች (በሴትየዋ እግር፣ በጨርቅ፣ ...ወዘተ) ያለተሸፈነ መሆኑን አረጋግጥ::

3. የሴትየዋ ክብደት በሁለት ሰኮንድ ውስጥ ስለሚታይ የሴትየዋን ክብደት ወደ 0.4 ኪ.ግ በማ ጠጋጋት በመጠይቁላይ "መልስ ሰጪዋ" በሚለው ዓምድ መዝግብ (ይህ ክብደት የመልስ ሰጭዋ ነው):: (ክብደቱን የሚናገሩ ቁጥሮች የሚነበቡበት አካባቢ በሙሉ የሚነበብና ሁሉንም ቁጥሮች ለማንበብ የሚያስችል ሁኔታ መኖሩን አረጋግጥ::

4. ልጁን ለመለካት የሚያስችል ዝግጅት እስክታደርግ ሴትየዋ በሚዛኑ ላይ ቆማ እንድትቆይ ጠይቃት::

ሠ. <u>ለኪ:- የልጁን (ልጆቹን) ክብደት ለካ</u>

<u>ማስታወሻ:-</u> ብርድ ከሆነና እናቲቱ ልጇ ሲመዘን ጨርቅ እንዲለብስ ከፈለገች የራሷን ክብደት መዝግበህ ከአበቃህ በኋላ የሚለበስ ነገር (ብርድልብስ፣ ጋቢ፣ ወይም ሌላ ነጠላ ነገር) እንድታለብሰው ስጣት (ይህ ተግባር የሚከናወነው መ.3 ከተጠናቀቀና ሠ.1 ሳይተገበር መሆን ይኖርበታል)::

1. <u>ልጁን እንድታለብሰው ለእናቱ ጨርቅ ያልተሰጣት ከሆነ:-</u>

ሀ. እናቲቱ በሚዛኑ ላይ እንደቆመች የክብደት ተናጋሪ ቁጥሮች የማይቀያየሩ መሆኑን አረጋግጥ:: በመቀጠል (እናቲቱ በሚዛኑ ላይ እንደቆመች) ከአንድ ሰኮንድ ላነሰ ጊዜ በፀሐይ ብርሃን የሚሰራውን ባተሪ ሸፍነው:: ሚዛኑ "0.0" ያነባል:: እናቲቱ ልጇን እንደታቀፈች የሚያሳይ ሥዕል ይታያል:: ይህም ማለት ሚዛኑ በእናቱ እቅፍ ውስጥ እንዳለ የልጁን ክብደት ብቻ የሚያሳይ መሆኑን የሚገልጽ ነው (ይህ ዓይነቱ ተግባር <u>ታሪንግ</u> ይባላል):: ሚዛኑ ልጁ በእናቱ ክንድ ላይ እንዳለ ለመለካት ዝግጁ ይሆናል::

ለ. <u>ልጁን እንድታለብሰው ለእናቲቱ ብርድ ልብስ ወይም ሌላ ጨርቅ የተሰጣት ከሆነ:-</u> እናቲተ ከሚዛኑ ላይ እንድትወርድ አድርግ:: ብርድ ልብሱን ወይም ጨርቁን ስጣትና እንደገና ከሚዛኑ ላይ እንድትወጣ አድርግ (ብዙ ጊዜ ብርድ ልብስና ሌሎች ጨርቆች ከ2 ኪ.ግ. ያነሰ ክብደት ስላላቸው ሴትየዋ ከሚዛኑ ወርዳ እንደገና መውጣት ይኖርባታል:: ከታች ሽ.2 ተመልከት):: ሴትየዋ ከሚዛኑ ላይ እንደቆመች ቁጥሮች የማይቀያየሩ መሆኑን አረጋግጥ፣ በመቀጠል (ሴትየዋ በፀጥታ ከሚዛኑ ላይ ብርድልብሱን ወይም ጨርቁን ይዛ እንደቆመች) በፀሐይ ብርሃን የሚሰሩትን ባተሪዎች ከአንድ ሴኮንድ ላነሰ ጊዜ ሸፍን:: በዚህ ጊዜ ሚዛኑ "0.0" ያሳያል:: እናቲቱ ልጇን እንደታቀፈች የሚያሳይ ምስል ይታያል ይህም ማለት ሕፃኑ በእናቱ ክንድ ላይ እያለ የልጁን ክብደት መመዘን እንደሚቻል የሚገልጽ ነው:: (ይህም <u>ታሪንግ</u> ይባላል):: ሚዛኑ ሕፃኑ በእናቱ ክንድ ላይ እያለ ክብደቱን ለመለካት ዝግጁ ይሆናል::

2. የመጨረሻ ትንሹን ልጅ እናቱ እንድትታቀፈው አድርግና የሚዛኑ ቁጥሮች መቀያየር እስኪያቆሙ ጥብቅ::

3. የልጁን ክብደት ወደ 0.1 ኪ.ግ በማጠጋጋት በመጠይቁ ላይ በአለው የልጁ ስም በተፃፈበት ዓምድ አቅጣጫ ፃፍ:: (እናቲቱ ልጁን በክንዷ ላይ እንደታቀፈችው የተመዘኑ ቢሆንም ሚዛኑ የልጇን ክብደት ብቻ ነጥሎ ያሳያል)::

ረ. <u>ለኪ:- ከአንድ ልጅ በላይ ያላትን መልስ ሰጭ ልጆች መመዘን:-</u>
ለእያንዳንዱ ልጅ ከላይ በ"ሠ" ላይ የተገለጹትን ተግባራት በቅደም ተከተል መፈጸም ያስፈልጋል:: በዚሁ መሠረት የመጨረሻው ትንሹ ልጅ ተመዝኖ ሲያበቃ ከሱ ቀጥሎ ያለውን የመ

ሐ. በፀሐይ ብርሃን የሚሰራው ባተሪ ከአንድ ሴኮንድ ለበለጠ ጊዜ ሲሸፈን፣ ከአንድ ሴኮንድላነስ ጊዜ ለመሸፈን ሞክር፣

መ. በጣም ጨለማ ከሆነ፣ ሚዛኑን ብርሃን በአለበት ቦታ አስቀምጥ፣

ሠ. 120 ኪ.ግ በላይ ክብደት ሲመዘንበት፣ ቀላል ክብደት ተጠቀም።

6. ሚዛኑ የሚከተሉትን ምልክቶች ሲሰጥ ምን ማድረግ አለብን።

E.O1:-

ሚዛኑ ራሱን ማስተካከል አለበት ማለት ነው። በዚህ ጊዜ ሚዛኑን አጥፍተህ E.O1 እስክትጠፋ ጠብቅ።

E.O2 እና በራሱ ጊዜ ሲጠፉ:-

በሚዛኑ ላይ ክብደት የሌለ መሆኑን አረጋግጥና ሚዛኑን እንደገና ለማስነሳት ሞክር።

E.O3 እና በራሱ ጊዜ ሲጠፉ:-

ሚዛኑ በጣም ቀዝቅዟል ወይም ሞቋል ማለት ነው። በዚህ ጊዜ የአካባቢው ሙቀት በ0° ሴ እና በ45° ሴ መካከል ወደ ሆነ ቦታ ቀይረህ አስቀምጠው። ሚዛኑ ራሱን ከአካባቢው ሙቀት ጋር እስ ኪያስተካክል ለ15 ደቂቃ ጠብቀህ እንደገና አስነሳው።

ከልክቶሽ በኋላ E.O4:-

ክብደቱ በጣም ከባድ (ከ150 ኪ.ግ በላይ) መሆኑን ያመለክታል። በዚህ ጊዜ ሚዛኑን አጥፍ ተህ ክብደቱን ቀንስ።

ታር ለማድረግ ከተሞከረ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ E.O5

ታር ለማድረግ ክበደቱ በጣም ከባድ (ከ120 ኪ.ግ በላይ) መሆኑን ያመለክታል። በዚህ ጊዜ ሚዛኑን አጥፍተህ ክብደቱን ቀንስ።

7. ዩኒስኬልን ለመጠቀም፣ ለማጽዳትና ለማሸግ ማስታወሻ

ሀ. በጣም ሙቀት ከሆነ ሚዛኑ በትክክል አይሰራም፣ በፀሐይ በርሃን ለሚሰራው ባተሪ በቂ ብርሃ ን እስካለ ድረስ ሚዛኑን በቤት ውስጥ ወይም ጥላ በአለበት ቦታ መጠቀም ይገባል። ሚዛኑ በጣም በመሞቁ የተነሳ በትክክል የማይሰራ ከሆነ ከመጠቀምህ በፊት ቀዝቃዛ ቦታ ላይ ለ15 ደቂቃ ማስቀመጥ ያስፈልጋል።

ለ. ተለዋዋጭ ለሆነ የአየር ፀባይ ሚዛኑ መስተካከል አለበት። የተለየ የአየር ፀባይ ወደ አለው ቦ ታ ሚዛኑ ሲዛወር ለ15 ደቂቃ ጊዜ መጠበቅ ያስፈልጋል።

ሐ. ሚዛኑ መወርወር ወይም መገፋት የለበትም።

መ. ሚዛኑን የፀሐይ ብርሃን በሚደርስበት ቦታ ወይም ሙቀት በሆነ ቦታ አታስቀምጥ። ለምሳሌ በፀሐያማ ቦታ ላይ በቆመ መኪና ውስጥ ሚዛኑ መቀመጥ የለበትም።


ሠ. ሚዛኑን እርጥበት ከአዘለ አየርና እርጥብ ከሆነ ቦታ ጠብቅ።

ረ. የአየር ሙቀቱ ከ0°ሴ በታችና ከ45°ሴ ብላይ በሆነበት ሚዛኑን አትጠቀም።

ሰ. ሚዛኑን ለማጽዳት እርጥብ በሆነ ጨርቅ ተጠቀም። በፍጹም በውሃ ማጠብ አይገባም።


## ሥዕላዊ መግለጫ 1

## የሕፃናት ቁመት አለካክ



# ሥዕላዊ መግለጫ 2

## የሕፃናት ርዝመት አለካክ



ዕዝል - 2

<u>ዋና ዋና ታሪካዊ ድርጊቶች ዝርዝር</u>

| ተራ ቁጥር | ታሪካዊ ድርጊቶች | ድርጊቱ የተፈጸመበት ዓመተ ምሕረት | ድርጊቱ ከተፈጸመበት እስከ 2000 ዓ.ም ያሉት ዓመታት ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የተወለዱበት | 1884 | 116 |
| 2 | ዝዋይ የተወረረበት/ከጅቡቲ እስከ አዲስ አበባ ያለው ባቡር መስመር የተዚጋበት | 1886 | 114 |
| 3 | የወላሞ ዘመቻ የተደረገበት | 1887 | 113 |
| 4 | ራስ መንገሻና ራስ አሉላ ከኢጣሊያ ወታደር ጋር በኩዓቲት ላይ ጦርነት የገጠሙበት | 1887 | 113 |
| 5 | ራስ መንገሻ በኩዓቲትና በሰንዓፌ ላይ በኢጣሊያ ድል የሆኑበት | 1887 | 113 |
| 6 | የዓድዋ ድል የተገኘበት | 1888 | 112 |
| 7 | ንጉስ ተክለሃይማኖት ያረፉበት | 1893 | 107 |
| 8 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጋራ ሙለታ ደጃዝማች ተብለው የተሾሙበት | 1897 | 103 |
| 9 | ልዑል ራስ መኮንን ያረፉበት | 1898 | 102 |
| 10 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሲዳሞ የተሾሙበት | 1900 | 100 |
| 11 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሐረርጌ የተሾሙበት | 1902 | 98 |
| 12 | አጼ ምኒሊክ ያረፉበት/ልጅ እያሱ የነገሱበት | 1906 | 94 |
| 13 | ራስ ሚካኤል በወሎ በትግራይና | 1907 | 93 |


| | | | |
|---|---|---|---|
| | በጎጃም የነገሡበት | | |
| 14 | ንግስት ዘውዲቱ የነገሡበት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አልጋ ወራሽ የሆኑበት | 1909 | 91 |
| 15 | የሰገሌ ጦርነት የተካሄደበት | 1909 | 91 |
| 16 | እቴጌ ጣይቱ ያረፉበት | 1910 | 90 |
| 17 | የሕዳር በሽታ የነበረበት | 1911 | 89 |
| 18 | ልጅ እያሱ የተያዙበት | 1913 | 87 |
| 19 | ኢትዮጵያ የዓለም መንግሥታት ማኅበር አባል የሆነችበት | 1916 | 84 |
| 20 | የባሪያ ነጻነት ደንብ የወጣበት | 1916 | 84 |
| 21 | ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት የተቋቋመበት | 1917 | 83 |
| 22 | ፊታውራሪ ኃብተ ጊዮርጊስ ማተሚያ ቤት የተቋቋመበት | 1918 | 82 |
| 23 | አቡነ ማቲዎስ ያረፉበት | 1919 | 81 |
| 24 | ንግስት ዘውዲቱ ያረፉበት | 1922 | 78 |
| 25 | ራስ ጉግሳ ወሌ በጎንደር የሞቱበት | 1922 | 78 |
| 26 | ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ የነገሡበት | 1923 | 77 |
| 27 | የወልወል ግጭት የተደረገበት | 1927 | 73 |
| 28 | የማይጨው ጦርነት የተካሄደበት ኢጣልያ ወደ ኢትዮጵያ የገባችበት | 1928 | 72 |
| 29 | የኢትዮጵያ ሰማዕታት ቀን | 1929 | 71 |
| 30 | በጅማ ገነቴ ላይ በአርበኞች ውጊያ የተደረገበት | 1930 | 70 |
| 31 | እንግሊዝ ኢጣልያን ከኢትዮጵያ ለማስወጣት የመጣበት | 1933 | ~~77~~ 67 |
| 32 | ኢጣልያን ድል የተመታችበት | 1933 | ~~77~~ 67 |
| 33 | ለኢትዮጵያ ሰማዕታት ሀውልት የተሰራበት | 1937 | ~~73~~ 63 |
| 34 | አቡነ ባስሊዎስ ሊቀ ጳጳስ የሆኑበት | 1943 | 57 |
| 35 | ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን የተዋሃደችበት | 1943 | 57 |
| 36 | የሸንቁጤ ረሃብ በቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ዘመን የገባበት | 1950 | 50 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 37 | እንጂኔራል መንግሥቱ ነዋይ የቀዳማዊ ኃ/ሥላሴን መንግሥት ለመገልበጥ ሙከራ ያደረጉበት | 1953 | 47 |
| 38 | ኤርትራ ከኢትዮጵያ የተዋሃደችበት | 1955 | 45 |
| 39 | የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የቋቋመበት | 1955 | 45 |
| 40 | ኮሌራ በሽታ የገባበት | 1963 | 37 |
| 41 | የኢትዮጵያ አብዮት የፈነዳበት | 1966 | 34 |
| 42 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከሥልጣን የወረዱበት | 1967 | 33 |
| 43 | የዕድገት በኅበረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ በዓል የተከበረበት | 1967 | 33 |
| 44 | የገጠርን መሬት የመንግሥት ያደረገው አዋጅ የታወጀበት | 1967 | 33 |
| 45 | የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት የመንግሥት ያደረገው አዋጅ የታወጀበት | 1967 | 33 |
| 46 | ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ያረፉበት | 1967 | 33 |
| 47 | የእናት አገር ጥሪ የተደረገበት | 1969 | 31 |
| 48 | ኢ.ሠ.ፓ.አ.ኮ የተመሰረተበት | 1972 | 28 |
| 49 | የመጀመሪያው የሕዝብና ቤት ቆጠራ የተካሄደበት | 1976 | 24 |
| 50 | የኢ.ሠ.ፓ. ምሥረታና የ10ኛው የአብዮት በዓል የተከበረበት | 1977 | 21 |
| 51 | የግንቦት 8 መፈንቅለ መንግሥት | 1981 | 19 |
| 52 | ኢህአዴግ አዲስ አበባን የተቆጣጠረበት | 1983 | 17 |

## የዋና ዋና ቋንቋዎች ስምና ኮድ ዝርዝር (የቀጠለ ... )

| | ቋንቋ | ኮድ | | ቋንቋ | ኮድ | | ቋንቋ | ኮድ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| K | ኮንሶኛ (ካራ·ቴኛ፣ ኮምሶኛ፣ ጋራ·ቴኛ) | 46 | M | መሩሌኛ | 63 | S | ሱርማኛ (ሱሪኛ፣ ቲርማኛ፣ ዳማኛ፣ ቺማኛ) | 78 |
| | ኮሬኛ | 47 | N | ናኦኛ (ናሆኛ፣ ቶሎኛ) | 64 | | ሺኛ | 79 |
| | ኮይጎኛ (ሙጉጂኛ) | 48 | | ኑዌርኛ (አቢጋርኛ) | 65 | | ሺታኛ (ሲታኛ፣ ላንጎኛ) | 90 |
| | ኮይሪኛ (አማሮኛ፣ አማሪቾኛ፣ ባዲቲኛ) | 49 | | ኛንጋቶምኛ (ቱርካናኛ፣ ብ·ሜኛ፣ መን፣ ቡም፣ ሮጌጌኖ፣ ቶቦላ) | 66 | T | ትግርኛ | 80 |
| | ኩናምኛ | 50 | O | ኦሮምኛ | 67 | | ጠምባሮኛ | 81 |
| | ካሮኛ | 51 | | ኦይድኛ | 68 | | ፀማይኛ (ፃማኛ፣ ኩዌሊኛ) | 82 |
| | ኩሱሜኛ | 52 | Q | ቀቤንኛ | 69 | U | ኡፖ | 83 |
| M | ማሌኛ | 53 | | ቀጨምኛ (ቀጨኖኛ፣ ጋፃምኛ፣ ሀሩሮኛ) | 70 | W | ወላይትኛ | 84 |
| | ማኦኛ (አንፊሎኛ፣ ገዋሚኛ፣ ማባንኛ፣ ኮማኛ) | 54 | | ቀዋሚኛ | 71 | | ወርጂኛ | 85 |
| | ማረቆኛ (ሊቢዶኛ) | 55 | S | ሸካቾ (ሞቻኛ) | 72 | Y | የምሳኛ (የምኛ፣ ያንጋሮኛ) | 86 |
| | ማሸሌኛ | 56 | | ሸኮኛ (ሀኮኛ) | 73 | Z | ዘይሴኛ | 87 |
| | ሜርኛ | 57 | | ሺናሻኛ (ቦሮኛ፣ ሺኒቾኛ፣ ደንገቦኛ) | 74 | | ዝልማምኛ (በሌ) | 88 |
| | መኤንኛ (መኤንትኛ፣ መቂንኛ፣ ዳሚኛ) | 58 | | ሲዳምኛ | 75 | | ሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋዎች | 91 |
| | መስንጎኛ (ማጃንግኛ፣ ኡጃንግኛ) | 59 | | ስልጢኛ (አዘርነት፣ በርበሬ፣ እነቆርኛ፣ አሊቾና ወሪሮ፣ ወራቤኛ) | 76 | | እንግሊዝኛ | 92 |
| | መዥንግርኛ | 60 | | ሶማሌኛ | 77 | | ሌሎች የውጭ አገር ቋንቋዎች | 93 |
| | ሞሲኛ (ቡሳኛ) | 61 | | | | | | |
| | ሙርሲኛ (ሙንኛ፣ ሙርዙኛ፣ ሙርዲ፣ ኚካላቦንግኛ) | 62 | | | | | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ክልል | ኦሮሚያ | የሊቀመንበር ስም | አባ ማመ አባገር |
| ዞን | ጂማ | የቤተሰብ ብዛት | 195 |
| ወረዳ | ማና | የቆጠራ ቦታ ቁጥር | 031-03- |
| የገ/ማህበር ስም | በበላ ሽመመዳ | ግምታዊ ስፋት | 7.25 ስ.ኪ.ሜ |




መስፈርት 1:50.000

**መግለጫ**

- - - - የወረዳ ክልል
- · - · የገ/ማህበር ክልል
- —— የቆጠራ ቦታ ክልል
- - - - የእግር መንገድ
- ~ የማያቋርጥ ወንዝ
- መንደር
- ከተማ
- ቤተ ክርስቲያን
- ቆርቆሮ ቤት
- ሣር ቤት

| | ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|
| ሌ.ካርታ ሠራተኛ | ዓለማየሁ ሀ/ጊዮርጊስ | [signature] | 18-7-85 |
| ተቆጣጣሪ | ፓውሎስ ጸጋዬ | [signature] | 07-8-85 |

CENTRAL STATISTICAL AUTHORITY

DESCRIPTION FORM FOR RURAL ENUMERATION AREA

FORM R-5

PART I: AREA IDENTIFICATION

| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| --- | --- | --- | --- | --- |
| REGION [illegible] | AWRAJA H3- | WEREDA | PA/SD NAME | E.A CODE |
| [illegible] | 5-09 | 095 | [illegible] 031 | 03 |

PART 2: E.A DESCRIPTION

DESCRIBE THE IDENTIFIABLE BOUNDARIES FROM NORTH AND COMPLETE IN CLOCKWISE DIRECTION

በሰሜን:- [illegible]

በምሥራቅ:- [illegible]

በደቡብ:- [illegible]

በምዕራብ: [illegible]

NB:-USE ADDITIONAL FORM IF NEEDED

ATTACH THIS FORM TO E.A MAP

NAME OF E.A [illegible] SIGNATURE [signature] DATE 18-07-85

NAME OF SUPERVISOR [illegible] SIGNATURE [signature] DATE 18-7-85